

# ኦሮማራ
## ምስማር ወይስ ምሳር ?



**እንኳን ለብርሃነ ትንሳኤው አደረሳችሁ**

መለያችን ኢትዮጵያዊነታችን!

# ግዮን

በየሳምንቱ ቅዳሜ

ግዮን ቅጽ 1 ቁጥር 53 ሚያዚያ 2011 ዓ.ም

ዋጋ 14.99

**ከአሜሪካ እስከ አሜሪካ**

**ለቅሶአችንን አልቅሳችኋል፡ ህመማችንን ታማችኋል**

**ጋዜጠኛ መሳይ መኮንን**

## አኖሌ ፈርሷል!!

"ምን ዓይነት ሁኔታዎችን ነው ይሄ የለውጥ ሃይል የተረከበው?"



# "በአጋዚ ፕሮጀክት የኤርትራን ደጋማ ክፍል ወደ ትግራይ ለመጠቅለል ታስቧል"

**አምባሳደር ካሳ ከበደ**

ግዮን

# “አሁንም የሕወሓት ትግራይን የመገንጠል ዓላማ አልከሰመም”

“መን ዓይነት ሁኔታዎቅን ነው ይሄ የለውጥ ሃይል የተረካበው?”

“በአፓዚ ንቅናቄ ፕሮጀክት የኤርትራን ጸገማ ክፍል ወደ ትግራይ ለመጠቅለል ታስቧል”

አምባሳደር ካሳ ከበደ

14






ቁጥር 52 ዕትም

ግዮን
ቀጣይ ዕትም
ቅዳሜ ሚያዚያ 26
ይጠብቁን!


7 ጥቁር አንበሳን ወደ ቀደመው ክብሩ መልሱልን!

8 የአዴፓና ኦዴፓ “ሽርክና” ብቻውን መፍትሄ አይሆንም ! ! !

9 የትንሳኤው ትርጉም “ትንሳኤ” ለሚያስፈልጋት ሀገር
ታዴዎስ ግርማ

11 አንደበትና ቅምሻ

12 ህዝብ ከህዝብ? የቱ ጋር ነን? !
ፍቅርተ ተሾመ

13 <<አንተ ጎዳና አንተ መንገድ፤ ሰው እንዳይሄድ፤ ዋ! ሰው እንዳይሄድ!>>
በኃይሉ ገ/እግዚአብሔር

18 ሥጋት! . . . እልህ! . . . ወይስ መብት
መለስ ሽኔ

19 የአዲስ አበባን ነገር . . . የሰው ልጅ ያላለፈበት አዲስ ፈተና አልገጠመንም
ከናፍቆት ገላው አሜሪካ

21 የአበሻው የሙዚቃ ንጉሥ ትውስታ

23 የተበላሹና ያላገናኟቸው እውነቶች
ከሽዋፈራሁ ኩራቱ ዶ/ር አሜሪካ

ዜና 2

## ከአሜሪካ እስከ አሜሪካ

ለቅሶአችንን አልቅሳችኋል፡ ህመማችንን ታማችኋል
ጋዜጠኛ መሳይ መኮንን
3

25 አኖሌ ፈርሷል ! !

27 ማህበራዊ

## ኦሮማራ ምስማር ወይስ ምሳር ?

መላክ ቢ.

4

# ዛሬም ጌድኦ ተመልካች አጥቷል

ላለፉት ሦስት ወራት ከመኖሪያ አካባቢያቸው በተፈጠረ የጎሳ ግጭት ተፈናቅለው ህይወትን በአስከፊ መልኩ እየገፉ የሚገኙት የጌድኦ ነዋሪዎች ችግሮቻቸው ከዕለት ወደ ዕለት እየተባባሱ መምጣታቸውንና መፍትሄ የሚሰጣቸውም አካል ማጣታቸውን ለዝግጅት ክፍላችን በድጋሚ አስታውቀዋል፡፡

በስልክ ያነጋገርናቸው የጌድኦ ተወላጆች እንደሚናገሩት የሁለቱም ክልሎች ማለትም የደቡብና የኦሮሚያ ምክትል መስተዳሮች በስፍራው ተገኝተው ወደ አካባቢያችን መመለስ ስለሚቻልበት ሁኔታ ተነጋግረናል፡፡ ይህም የሆነው አስቀድመን ማመልከቻ አስገብተን ስለነበረ ነው፡፡ ወደ ቀድሞው ቀያችን መግባት እንፈልጋን፤ ነገር ግን መተማመኛ ያስፈልገናል፤ ይህንን ደግሞ መንግስት ሊያመቻችልን ይገባል ባልነው መሰረት የሁለቱም ክልል ባለስልጣናት ሚያዝያ 16 ቀን 2011 ዓ.ም መጥተው በዚሁ ጉዳይ ላይ ከተፈናቃዩ ጋር ስብሰባ አካሂደዋል ብለውናል፡፡

በዚሁ እለት ህዝቡ ከዚህ በፊት ያነሳቸውን ጥያቄዎች በድጋሚ ያቀረበ ሲሆን፤ ወደ አካባቢያችን ለመመለስ ከዚህ በፊት ቤት ንብረታችንን ያቃጠሉትና ያወደሙት ሰዎች ተይዘው ለህግ እንዲቀርቡ፤ የተቃጠለብን፣ የተዘረፈብን ንብረትም ተገምቶ ካሳ እንዲከፈለን፣ይህንንም የሚያጣራ ገለልተኛ ኮሚቴ አረንዲቋቋም፤ ከዚህ በተጨማሪም የማንነት ጥያቄ አንስተው ህዝቡን እርስ በርስ እንዲጋጭና እንዲገዳደል ያደረጉት ባስልጣናትም ለህግ የሚቀርቡበት አግባብ እንዲፈጠር እንፈልጋለን የሚሉ ጥያቄዎች ማንሳታቸውን ተናግረዋል፡፡

ተፈናቃዮቹ በ1990 ዓ/ም ተመሣሣይ የሆነ ችግር ተፈጥሮ የገበሬዎች የቡና ማሳና ምርት በሙሉ መውደሙን አስታውሰው አሁንም የተፈጠረው ይሄ ድርጊት ላለመቀጠሉ፤ በህይወትና በንብረት ላይ የሚደርሰው ጉዳት ለመቆሙ እርግጠኞች አይደለንም፤ በዚህ ሁኔታ ውስጥ ወደቀዬአችን የመመለሱ ነገር ከጥቅሙ ጉዳቱ ያመዝናል፡ ፡ የተረጋገጠና መሬት የወረደ የሚተገበር ቃል ያስፈልገናል ይላሉ፡፡

ሚያዚያ 16 ቀን 2011 ዓ.ም ወደ ስፍራው መጥተው የነበሩት 8 የካቢኔ አባላት ጥያቄዎቹን ተቀብለው "ጥያቄያችሁ አግባብነት ያለውና ህገ-መንግስትን መሰረት ያደረገ ነው፤ ፍፁም ሰላማዊ በሆነ መንገድ ላቀረባችሁት ጥያቄ ምላሽ እንሰጣለን" ማለታቸውንና ይሄንን በተመለከተም የዞኑ አመራር ጋዜጣዊ መግለጫውን ይሰጣል ብንባልም የዞኑ አመራር ግን ምንም ዓይነት መግለጫ አልሰጥም፤ እንደውም ጉዳዩ አይመለከተኝም የሚል ምላሽ መስጠቱን ተፈናቃዮቹ በምሬት ይናገራሉ፡፡

የዞኑን አመራር ምላሽ ያደመጡት ተፈናቃዮች እንደገና በስጋት መዋጣቸውን፤ ተመልሰን ወደ ሌላ ብጥብጥና ግጭት እንገባ ይሆን? የአመራሮቹ ፍላጎት ምን እንደሆነ ሊገባን አልቻለም የሚሉ ጥርጣሬዎች ላይ መውደቁን ከስፍራው በስልክ ያነጋገርናቸው ተፈናቃዮች ይገልፃሉ፡፡

አቶ ሲሳይ ማሞ ጉዳዩን አስመልክተው ያለውን ሁኔታ እንዲያስረዱን ከጠየቅናቸው መካከል አንዱ ናቸው፡፡

"ወደቀዬአችን ለመመለስ እንፈልጋለን፤ ነገር ግን ያሉት ሁኔታዎች አስተማማኝ አይደሉም፤ ወደ ነበርንበት ለመመለስ የሚያስፈልጉት ነገሮች አልተሟሉም፡፡ ለምሣሌ መጠለያ ዋናው ነገር ነው፡፡ በግለሰብ ደረጃ እስክንጠናከርና ጎጆአችንን መልሰን እስክንሰራ የምንቆይበት በቆርቆሮ የተከለለና በሲሚንቶ የተነጠፈ ወለለ ቢዘጋጅልን መልካም ነበር፤ ነገር ግን የተሰጠን ምላሽ መንግስት አቅም የለውም የሚል ነው፡፡ ሌላው ችግራችን ደግሞ ከበጎ አድራጊዎች የተሰጠንም ሆነ መንግስት አቅርቤያለሁ የሚለውን ዕርዳታ በአግባቡ እያገኘን አይደለም፡፡ ባለጉዳዮቹ እኛ ሆነን ሳለ በፍቃዳቸውና በፍላጎታቸው ያሻቸውን እያደረጉ ያሉት የዞኑ አመራሮች ናቸው፡፡ ይሄ አግባብ አይደለም፡፡ ለጌድኦ ተፈናቃዮች ተብሎ የመጣውን እርዳታ የጉጂ ሰዎች ስለሆኑ የሚቆጣጠሩት የማሠቃየትና የማንከራተት ችግሮች ይታያሉ፤ ይህ እንዲሆን የሚያደርጉት ሠዎች ከተግባራቸው እንዲቆጠቡና በህግ እንዲጠየቁ እንፈልጋለን" ሲሉ ሀሳባቸውን ሠንዝረዋል፡፡

ረቡዕ ሚያዝያ 16 ቀን 2011 ተፈናቃዮች ያለውን ሁኔታ ለማስረዳትና በተለይም ከመንግስት ይልቅ ለችግሮቻቸው ቀድመው የደረሱላቸውን ግለሰቦችና በጎ አድራጊዎች በይፋ ለማመስገን፤ እንዲሁም አሁንም ቢሆን ያልተፈቱ ችግሮቻቸውን በሠላማዊና በተገቢው መንገድ ተጠቅመው ጥያቄ ለማቅረብ የሚያስችል ሠልፍ አዘጋጅተው እንደነበረና በተለያዩ ጉዳዮች ምክንያት ቀኑን ለማራዘም እንደወሰኑ ከስፍራው የደረሰን ሪፖርት ያስረዳል፡፡

## ሞዴል ፈትያ መሐመድ በላስ ቬጋሱ ውድድር ትካፈላለች

| ባለትዳር እና የሁለት ልጆች እናት የሆነችው ኢንተርናሽናል ሞዴል ፈትያ መሐመድ ኢትዮጵያን ወክላ በአሜሪካ ምድር ለንግስና እንደምትወዳደር ታውቋል፡፡

በላስ ቬጋስ ከአፕሪል28 እስከ ሜይ 4 በሚካሄደው MRS WORLD 2019 (የወይዘሮ ዓለም የቁንጅና ውድድር) ላይ ለመሳተፍ ኢንተርናሽናል ሞዴል ፈትያ መሐመድ አርብ ሚያዚያ 18ቀን (ትናንት ምሽት) ወደ ላስ ቬጋስ ኔቫዳ ተጉዛለች፡፡

በዚህ ውድድር ላይ ለመሳተፍ መስፈርት ሆኖ የተቀመጠው ባለትዳርና የልጆች እናት መሆኑን ለዝግጅት ክፍላችን የገለጸችውና 2018 በማሌዢያ በተካሄደው የሚስስ ቱሪዝም ኢንተርናሽናል ፒጀንት ውድድር ላይ "ሚስስ ቱሪዝም አፍሪካ" አሸናፊ የነበረችው ኢንተርናሽናል ሞዴል ፈትያ መሐመድ በላስ ቬጋሱ ወድድር ላይም ከተሳካላት ሀገሯን ለማስጠራት የቻለችውን ሁሉ እንደምታደርግ አስታውቃለች፡፡ "የኢትዮጵያ እናት" ፈትያ መሐመድ ኖቬምበር 2018 በቡልጋሪያ በተካሄደው ሚስስ ፕላኔት የቁንጅና ውድድር ላይ ተካፍላ ሁለተኛ መውጣቷ አይዘነጋም፡፡

## ድምጻዊ አቤል ሙልጌታ በአዲስ አልበም መጣ

ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ከተገኙ ምርጥ ወጣት ድምጻውያን መሀል አንዱ የሆነው ድምጻዊ አቤል ሙልጌታ "እንነጋገር" በተሰኘ አዲስ አልበሙ ከአድናቂዎቹ ጋር ተገናኝቷል፡፡

በ1999ዓ.ም አካባቢ ባወጣው የመጀመሪያ አልበሙ ዕውቅና ለማግኘት የቻለው አቤል ሙለጌታ ከድምጹ ባሻገር በሚሰራቸው ግጥምና ዜማዎች ተወዳጅነትን አትርፏል፡፡ ከሙዚቃው በተጨማሪ የፊልሙን ኢንዱስትሪ ተቀላቅሎ የነበረው ወጣቱ ድምጻዊ አቤል ሙልጌታ፤ በቅርቡ "እንነጋገር" የተሰኘ ሶስተኛ አልበሙን በጃምሮክ ሪከርድስ አሳታሚነትና አከፋፋይነት ለገበያ ያቀረበ ሲሆን፤ በዚህ አዲስ አልበሙ ላይም የተለያዩ ስመ ጥር የሙዚቃ አቀናባሪዎች በቅንብሩ ረገድ የተካፈሉ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡

# የAIFF የፊልም ፌስቲቫል ግብዣ

በኢኒሼየቲቭ አፍሪካ በየአመቱ የሚካሄደው 13ኛው የአዲስ ኢንተርናሽናል ፊልም ፌስቲቫል ከሚያዚያ 22-27 ቀን 2011 ዓ.ም በሠብዓዊ መብት ሳምንትነት እንደሚካሄድ ተነገረ፡፡ በየአመቱ ከ60 በላይ ዘጋቢና አጫጭር ፊልሞች ተመርጠው ለዕይታ የሚቀርቡ ሲሆን፤ በዘንድሮው ፌስቲቫል ላይ ከሚቀርቡት ዘጋቢ ፊልሞች መካከልም በአገራችን ጉዳዮች ላይ የተሰሩ "My Name is Gennet" እና "Hairat" የተሰኙ ፊልሞች ለዕይታ እንደሚበቁ ለመረዳት ተችሏል፡፡

አለም አቀፋዊ ዝናን ያተረፈው አዲስ ኢንተርናሽናል ፊልም ፌስቲቫል አገራችንን ጨምሮ ከመላው አለም የተመረጡና ማህበራዊ ፋይዳ ያላቸው ተራኪ ፊልሞችን በመምረጥ ለእይታ የሚያበቃ ሲሆን፤ ከፌስቲቫሉ በተጨማሪም የአገራችን ጀማሪ ፊልም ሠሪዎች ልምድ እንዲቀስሙ ለማድረግ ታላላቅ የፊልም ዳይሬክተሮችን በመጋበዝ ስልጠናዎችና የፓናል ውይይቶች በማድረግ ለውጥ ለማምጣት እየሰራ መሆኑን አስታወቋል፡፡ በዚህ አመትም አስር (10) የሚሆኑ ዳይሬክተሮች ለዚሁ አላማ አዲስ አበባ መግባታቸው ታውቋል፡፡ ከነሱም ውስጥ የ`Bias` ዳይሬክተር ሮቢን ሀውዘር፤ የ`The Desert of the Desert` ዳይሬክተር ሰሚር አቡጃማሪ፤ ይገኙበታል፡፡

የአዲስ ኢንተርናሽናል ፊልም ፌስቲቫል ዳይሬክተር አቶ ክቡር ገና በመግለጫው ላይ እንደተናገሩት የኢትዮጵያን ፊልምና የዳይሬክተሮችን ብቃት ለማሳደግና ለማበረታት የሚቻልበትን መንገድ በስፋት እንደሚያጠናክሩ ገልፀው ተቋሙ ሥራውን የሚያከናውንበትን ‹‹ድማሙ›› የተሰኘ ህንፃ ለመገንባት አቅዶ ከታዳሽ ሀይልና ከአረንጓዴ ልማት ጋር የተያያዘ የህንፃ ዲዛይን ስራው የተጠናቀቀና ለግንባታ በሚውለው ቦታ ዙሪያም ከአዲስ አበባ መስተዳድር ጋር መግባባት ላይ መደረሱን አስረድተዋል፡፡

ፌስቲቫሉ በተለያዩ ቦታዎች የሚከናወን ይሆናል፤ የመክፈቻው ፕሮግራም ሚያዚያ 22 ቀን 2011 ዓ/ም በጣልያን የባህል ማዕከል የሚካሄድ ሲሆን፤ የመዝጊያው ፕሮግራም ሚያዚያ 27 ቀን 2011 ዓ.ም በቫምዳክ ኢንተርቴይመንት ይካሄዳል ተብሏል፡፡ ህብረተሰቡ ፌስቲቫሉን ያለምንም ክፍያ በሁሉም ቦታዎች እየተገኘ እንዲከታተልም ግብዣ ቀርቦለታል፡፡

## ከአሜሪካ እስከ አሜሪካ

# ለቅሶአችንን አልቅሳችኋል፡ ህመማችንን ታማችኋል



ጋዜጠኛ መሳይ መኮንን



### ክፍል አራት

ከሚሌኒየሙ አዳራሽ ውስጥ ነን፡፡ የኢሳት ቀን ለመጀመሪያ ጊዜ በኢትዮጵያ ምድር ላይ እየተከበረ ነው፡፡ ይህ በራሱ ታሪክ ሆኖ ተመዝግቧል፡፡ በስደት በሚኖሩ ሀገር ወዳድ ኢትዮጵያውያን የተጸነሰው ኢሳት ለስምንት ዓመታት በባህር ማዶ እድገቱን ከቀጠለ በኋላ ዘጠነኛ ዓመት ልደቱን በሀገሩ ማክበሩ ዕለቱን ለኢሳትና ቤተሰቦቹ ልዩ የሚያደርግ ነው፡፡ አብረነው ውጣ ውረዱን ላየነው ጋዜጠኞቹ ደግሞ ደስታው እጥፍ ድርብ ሆኗል፡፡ በህዝባችን ፊት ክብርና ሞገስ አገኘን፡፡ ለሰራናት ትንሽዬ ስራ በትልቁ ተመሰገንን፡፡ ሀገር ቆሞ አከበረን፡፡ ህዝብ ፍቅሩን ሳይሰስት በአደባባይ ገለጸልን፡፡ የዚህ የታሪክ ክስተት አካል መሆን ትርጉሙ ቀላል አይደለም፡፡ የኢሳት ቀን በተለያዩ ስነስርዓቶች ቀጥሏል፡፡

ከሰገነቱ ላይ ቁልቁል ወደ ህዝቡ መመልከት አንዳች ስሜት ይሰጣል፡፡ ከመድረኩ የሚተላለፉት መልዕክቶች ልብ ያሞቃሉ፡፡ ዙሪያዬም መቃኘት ጀመርኩ፡፡ ከአሜሪካና አውሮፓ የመጣን የኢሳት ባልደረቦች አንድ ጠረጴዛ ከበን ተቀምጠናል፡፡ በስተቀኛችን ባለው ጠረጴዛ ደግሞ የአርበኞች ግንቦት ሰባት አመራሮች ይገኛሉ፡፡ የምንጊዜም ጀግናዬ አቶ አንዳርጋቸው ጽጌ ከመሃላቸው አሉ፡፡ ሳየው ደስ አለኝ፡፡ ከእስር ከተፈታ በኋላ ለሁለተኛ ጊዜ ስንገናኝ ነው፡፡ የእሱ ነገር አይሆንልኝም፡፡ ልዩ ሰው ነው:: አንዲ! አንጋፋው ጋዜጠኛ ጋሽ ሙሉጌታ ሉሌ የአንዳርጋቸውን የተለየ ስብዕና ይገልጽልኛል በሚል ለጻፋት አንዲት ማስታወሻ የሰጣትን ርዕስ መቼም አልረሳትም "የኢትዮጵያ ልዩ አፈር"፡፡ እውነት አንዲን ይገልጸው ይሆን? እኔንጃ፡፡ አንዲ በእውነት የወኔ ስንቄ ነው፡፡ የተስፋ ምርኩዜ ነው፡፡

በረሃ ከገባበት ጀምሮ በቅርበት አገኘዋለሁ፡፡ በኢትዮጵያ ፖለቲካ የገዘፈ ስም ካላቸውና ፖለቲካን ለትርፍ ጊዜ መደበሪያነት ሳይሆን ሀገር ለመለወጥ ከሚጠቀሙት ጥቂት ሰዎች በፊት መሪነት የሚቀመጠው አንዳርጋቸው ነው፡፡ እሱ ይለያል፡፡ የመን ላይ በህወሀት ታፍኖ ከተወሰደ ጊዜ ጀምሮ ደግሞ ለእሱ ያለኝ አክብሮት ቃላት ከሚገልጹት በላይ ሆነብኝ፡፡ ለኤርትራ ጉዞ መነሻዬ፣ መድረሻዬም የአንዳርጋቸው መያዝ ነው፡፡ እልህ ውስጥ ገብቼአለሁ፡፡ በእሱ መያዝ ውስጤ የተፈጠረው የሞራል ስብራት ሳይሆን ቁጭት ነው፡፡ አንገቴን አልደፋሁም፡፡ ተስፋ አልቆረጥኩም፡፡ ይልቅስ በፊት በነበረኝ ቆራጥነት ላይ አቅም የጨመረብኝ፤ በተሰለፍኩበት የሙያ ዘርፍ ዘረኛውን የህወሀት አገዛዝ ለመታገል ተጨማሪ ጉልበት ያገኘሁበት አጋጣሚ ነው፡፡ እሱ የረገጣትን በረሃ መርገጥ ቢያንስ ውለታውን ዋጋ እንደመስጠት ቆጥሬዋለሁ፡፡ የምዕራቡን ዓለም ህይወት ትቶ፣ ጭው ካለው፣ እግዜር የረገመው ከሚመስለው፣ ስጋን በቁም ከሚጨርሰው የኤርትራ በረሃ የወረደው አንዳርጋቸው ጽጌ እየከፈለ ያለውን ዋጋ ክብር ለመስጠት በሚል በህወሀቶች ታፍኖ በተወሰደ በስድስተኛው ወር ወደ ኤርትራ ለመሄድ ወሰንኩ፡፡ አደረኩትም፡፡

የአቶ አንዳርጋቸው መያዝ ለህወሀት ትልቅ ኪሳራ አድርሶበታል፡፡ አንዳርጋቸውን በማፈን ከተገኘው ጥቅም ይልቅ ያመጣው ጉዳት ህወሀትን ሰብሮታል፡፡ ሚሊዮኖች የአንዳርጋቸው የመንፈስ ልጆች ነን ብለው መነሳታቸው ህወሀትን ክፉኛ ጎድቶታል፡፡ እኔም አንዱ የአንዳርጋቸው የመንፈስ ልጁ ሆኛለሁ፡፡ አርአያነቱን ለመከተል ለራሴ ቃል በመግባት በትግሉ ላይ ተጨማሪ እልህና ወኔ እንድሰንቅ አድርጎኛል፡፡ ሲፈታ አላመንኩም፡፡ የጠቅላይ ሚኒስትር አብይ አህመድ መንግስትን ከጥርጣሬ ወጥቼ በትክክልም ለኢትዮጵያ የሚበጃት መስመር ነው ከሚል ድምዳሜ ላይ እንድደርስ ያደረገኝ የአቶ አንዳርጋቸው መፈታትና በአፈታቱ ላይ የነበረው ግብግብ ነበር፡፡ ከዋሽንግተን ዲሲ ከኢሳት ቢሮ የኢሳት ባልደረቦች የአቶ አንዳርጋቸውን መፈታት በቀጥታ ስርጭት ስንመለከት የነበረውን ስሜት መቼም አልረሳውም፡፡ በህይወት አገኘዋለሁ ብዬ በእውኔም በህልሜም ያልጠበኩት ነገር ሲሆን ፈጽሞ ለማመን አልቻልኩም፡፡ በእምባ ተራጨን፡፡ ከሁለት ወራት ቆይታ በኋላ ወደ ዋሽንግተን ዲሲ ሲመጣ በአካል አገኘሁት፡፡ እስካየው መፈታቱን አላመንኩም ነበር፡፡ በእርግጥም አቶ አንዳርጋቸው የትግል አባቴ ነው፡፡ የመንፈስ ምርኩዜ፡፡ የወኔ ስንቄ፡፡ የኢትዮጵያ ማህጸን እንደሱ ዓይነት ልጅ መፍጠሩ በእውነት የተባረከ ነው፡፡

ወደ ሚሌኒየም አዳራሹ ልመለስ፡፡ ከመድረኩ ኢትዮጵያን የሚያነግሱ ዜማዎች እየተሰሙ ነው፡፡ ህዝቡ በደስታ መቦረቁን ቀጥሏል፡፡ ዙሪያዬን እየቃኘሁ ነው፡፡ ከአቶ አንዳርጋቸው ጋር ሌሎች የአርበኞች ግንቦት ሰባት አመራሮች ተቀምጠዋል፡፡ ሊቀመንበሩ ፕ/ር ብርሃኑ ነጋም አሉ፡፡ ትንሽ ቆየት ብሎ ማዳም እና ጎሜዥርና ጋዜጠኛ እስክንድር ነጋ ተያይዘው ገቡ፡፡ ማዳም እና ጎሜዥ ከኢትዮጵያውያን በላይ ኢትዮጵያዊ የሆኑ የትግል አጋራችን ናቸው፡፡ የኢትዮጵያን ጉዳይ ከኢትዮጵያዊ እኩል አንዳንድ ጊዜም ከዚያ ባለፈ የሚከታተሉና የህወሀትን ዘረኛ ስርዓት በአደባባይ የሚጋፈጡ ባለውለታችን ናቸው፡፡ ስለኢትዮጵያ በአውሮፓ ምድር ባገኙት መድረክ ላይ ያልጮሁበት ጊዜ አላስታውስም፡፡ ሃና ጎበዜ በሚል ኢትዮጵያዊ ስም ኢትዮጵያውያን ሲጠሯቸው ያለምክንያት አልነበረም፡፡ ኢትዮጵያ በየዘመናቱ ባለውለታ የሚሆኑላት የውጭ ሰው አታጣም፡፡ ከሲልቪያ ፓንክረስት ቤተሰብ ጀምሮ አያሌ የባህር ማዶ ሰዎች ኢትዮጵያ ክፉ ቀን በገጠማት ጊዜ ከጎኗ ሆነው ታድገዋታል፡፡ የዘመኑ ባለውለታ ደግሞ ማዳም እና ጎሜዥ ናቸው፡፡

እኚህን ሴት በአንድ አጋጣሚም ሳስታውሳቸው እኖራለሁ፡፡ ኢሳት የአቶ መለስ ዜናዊን ሞት ቀድሞ ይፉ ባደረገበት ጊዜ ማረጋገጫ ካገኘባቸው ቁልፍ ሰዎች አንዱ ማዳም እና ጎሜዥ ነበሩ፡፡ የህወሀት ሚዲያዎች በሰልፍ የአቶ መለስን ሞት ለማስተባበል በሚረባረቡበትና ኢሳት ብቻውን እውነትን ይዞ በቆመበት ወቅት ማዳም እና ጎሜዥ የአቶ መለስ ዜናዊ ሞትን በማረጋገጥ ኢሳት በአቋሙ እንዲጸና ያደረጉ ብርቱ ሴት ናቸው፡፡ አቶ መለስ ህይወታቸው ባለፈበት ብራስልስ የነበሩት እና ጎሜዥ በወቅቱ መረጃው ሊኖራቸው እንደሚችል ጥርጥር የለውም፡፡ አውሮፓውያንና አሜሪካውያን ሚስጢር እንዲሆንና በጊዜው የህወሀት አገዛዝ ድንገት ስብር ብሎ እንዳይወድቅ በሚል የአቶ መለስ ዜናዊ ሞት መደበቃቸውን የተረዱት ማዳም እና ጎሜዥ በውስጥ መስመር ለኢሳት መረጃውን አረጋግጠዋል፡፡ ኢሳትም በአቋሙ ጸንቶ ተአማኒነቱን በኢትዮያውያን ዘንድ ያስመሰከረበት አጋጣሚ ሆኖለታል፡፡ ለኢሳት አሻራ ከሆኑና በህዝብ ዘንድ ተቀባይነት ካስገኙለት ዘገባዎች የአቶ መለስ ዜናዊ ሞትን የሚያክል የለም፡፡ ያን ዘገባ በማቅረብ ደግሞ እኔ ከታሪኩ ጋር አብሬ መነሳቴ አልቀረም፡፡

በአጭሩ እኚህ ሴት ባለውለታችን ናቸው፡፡ ኢሳት በአዲስ አበባ ልደቱን ሲያከብር ከአውሮፓ ድረስ መጥተው ታድመዋል፡፡ በደስታና በሀዘናችን የማይለዩን ድንቅ ሴት ናቸው፡፡ በደስታ ሲፈለቀለቁ ይታዩኛል፡፡ ፈገግታቸው ከርቀት ያበራል፡፡ ከአጠገባችን መጥተው ሰላምታ አቅርበውልን ትንሽ አውግተውንም ነበር፡፡ አድናቆታችንን ገልጸን ለውለታቸው ምስጋናችንን በየተራ አቀረብልናቸው፡፡ ማዳም እና በኋላ ላይ በመድረኩ ሲወዛወዙ ተመለከትኳቸው፡፡ ዳንሱን ይችሉበታል፡፡ በአከባቢው ያለውን ሰው በሙሉ ትኩረት ወሰዱት፡፡ በእውነት የሚገርሙ ሴት ናቸው፡፡ ንግግር ሲያደርጉ በጥሞና ነበር ያዳመጥኳቸው፡፡ መልዕክታቸው ድንቅ ነው፡፡ ምንም አይወጣለትም፡፡ ኢሳትን አመሰገኑት፡፡ ትግላችሁ የዲሞክራሲና ፍትህ መረጋገጥ እስኪመጣ ድረስ ይቀጥል ብለውም የአደራ መልዕክት አስተላለፉ፡፡

ቀጣዩን በገጽ 26 ይመልከቱ

# ኦሮማራ ምስማር ወይስ ምሳር?

መላክ ቢ.

## ‘ኦሮሞ ወ አምሃራ’ ቅጽመ ታሪክ

ኦሮሞ እና የኢትዮጵያ ታሪክ ተሰናስሎ ሲወሳ በበጎ የሚነገር እልፍ ጀብዱና እልፍ አዕላፍ ትውልድ ተሻጋሪ ታሪኮች እንዳሉ ሁሉ፤ በተቃራኒ ጎን ይህንን ታላቅ ህዝብ የካቡ መስለው የሚያፈርሱ፣ ያወደሱ መስለው የሚያኮስሱ ብዙ የሴራ ፖለቲካ ትርክቶችም አሉ። በጎው ታሪክ ተደብቆ ክፋቱ በዘመን ላይ እንዲዘምን ግዙፍ ሚና የተጫወቱ ፣ ታስቦበት የተፈተለ መሰሪ ሴራ ነዝተው ኦሮሞን ከወንድም እህት ኢትዮጵያዊ ብሄሮች ፣ በተለይም ከአማራ ጋር ለመነጠል የተጉ፣ በዚህም ለዓመታት ሞልቶላቸው የስራቸውን ፍሬ ቁጭ ብለው ያጣጣሙ ብዙ ተንኮሎችም አሉ። ከነዚህ በርካታ የሴራ ፖለቲካ ውልዶች መካከል ቀንደኛው ሴራ የተስፋዬ ገብረዓብ ብዕር የወለዳቸው ፈጠራዎች ናቸው።

በዘሩ ኤርትራዊ የሆነው፣ በአንደበቱ ግን ‘ኦሮሞ ነኝ’ ባዩ ተስፋዬ ገብረዓብ በወያኔ/ኢህአዴግ ዘመን፣ የስርዓቱ የዘመን ሴራ ጠንሳሽ እና ጠማቂ ነው። ተስፋዬ በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ ታሪክን አዛብተው ዘመን ተሻጋሪ መርዝ ከቀበሩ ፣ በዚህም ሁለት ዋና ዋና ኢትዮጵያዊ ብሄሮችን ኣባልተው ሃገሪቱን ያለተቀናቃኝ በብቸኝነት ለማስገበር ለታተሩ ቡድኖች ቀኝ እጅ የነበረ ከእጅግ ጥቂት ‘ምርጥ’ የስርዓቱ ሴረኞች መካከል ቀንደኛው ሰው ነው።

የወያኔ /ኢህአዴግ የከፋፋይ ሴራ አሰናጅ እና አስፈጻሚ የነበረው ተስፋዬ ገብረአብ “የደራሲው ማስታወሻ” በተሰኘ መጽሃፉ ውስጥ “ደስተኛ ዝይ” በሚለው ትረካው ዮዲት መላኩ የተባለች ልጅ እና ቀስቶ የተባለ የሰፈሩ ሌባ የነበረ ልጅ ጥሩ ገልጸውታል።

ቀስቶ “እባብ” ብሎት ነበር። ዮዲት የተባለች የቀድሞ ሰፈሩ ልጅ ደግሞ ሄልስንኪ ውስጥ አግኝቷት ሳለ ሲያወሩኝ “አላምንህም ትረካ እንዲጣፍጥልህ ብለህ ነው በራስህ አስመስለህ የምትጽፈው።በደንብ አውቅሃለሁ።ያኔም እንዲህ በትንሽ መነሻ አስፋፍተህ ትጽፍ ነበር” እንዳለችው ተናግሯል።

ሁለቱም እውነተኛ ማንነቱን ነግረውታል። ተስፋዬ እንደ እባብ ከለሰለሰ ቆዳ ውስጥ ብቅ ብሎ መርዝ የሚተፋ፣ በተባ ብዕሩ ማር በእሬት ለውሶ የሚያጎርስ ከባድ ሴረኛ ሰው ነው። ውሸታምም ነው።አጋናኝ ነው።ሳያውቀው በነዚህ ሁለት ሰዎች የርሱን ማንነት ቁልጭ አድርጎ ተናግሯል።

ተስፋዬ ገብረዐብ “የቡርቃ ዝምታ” በተሰኘ መጽሃፉ ቀዳሚውን የተንኮል መርዝ በእያንዳንዱ የኦሮሞ ወጣት ላይ ሊቀባ አሀዱ ብሎ ስራውን ሲጀምር በጊዜው ህልሙ ከሚፈልገው በላይ ተሳክቶለት ነበር። ተስፋዬ በዚህ መጽሃፉ ውስጥ ይህንን ታላቅ ህዝብ ኦሮሞን ያሞገሰ አስመስሎ በቂም እየለወሰ፣ ከፍ ያደረገ አስመስሎ ወደጎጠኝነት እያጠበበ፣ ያጎላ መስሎ እያኮሰሰ ከአማራ እና ከቀሪ ኢትዮጵያዊ ወንድም እህቶቹ ጋር የሚለያይ የጊዜ ቦምብ ቀብሮ ነው ከሃገር የሸሸው።

ተስፋዬ ገብረአብ የኦሮሞን ሰፊ ህዝብ “ቡርቃ” በተባለ ትልቅና ከጊዜ ብዛት መሬት ውስጥ ሰርጎ ቀረ በሚለው ግዙፍ ወንዝ መስሎ ፣ መሬት ውስጥ ተቀብሮ ዝም ያለው ቡርቃም ተበድሎና ተረግጦ የኖረው የኦሮሞ ህዝብ ነው ብሎ፣ ያ ወንዝ ድንገት ከተቀበረበት እና ዝም ካለበት መሬት ውስጥ ፈንቅሎ ሲወጣ የሚያጠፋውን ሁሉ ከፊቱ ስሎለት ህዝብን ከህዝብ ጋር ለእልቂት የመለመለ ሰው ነው። በቡርቃ ዝምታ ውስጥ አኖሌ ብሎ በሰየመውና የተበደለ አባቱን ቂም እንዲወጣ በሾመው የፈጠራ ገጸ ባህርዩ ውስጥ በሌላ ብሄር ላይ ቂምን ሊቀብር፣ በአኖሌ ውስጥ ደግሞ በቀልን ሊዘራ ሲታትር እናየዋለን።

ተስፋዬ በዚህ በስነጽሁፍ ምጥቀቱ ወደር በሌለው፣ ነገር ግን በዚህ ውብ ስነጽሁፍ ውስጥ የማይታይ የሚመስል መርዝ በተቀበረበት “የቡርቃ ዝምታ” ጽሃፍ ውስጥ የአዲሱ የኦሮሞ ትውልድ ወኪል ለሆነው አኖሌ በአባቱ አማካኝነት አገሩም ምድሩም ሰማዩም የኦሮሞ ብቻ መሆኑን እየሰበከለት ነው ከምዕራፍ ምዕራፍ የሚጓዘው። በተስፋዬ ቀመር መሰረት ኦሮሞ አንድ ቀን ሲነሳ የበደሉትን ሁሉ እንደሚጨርስ፣ከርሱ ሌላ ሃያል ብሄር እንደማይኖር፣ አማራ ጠላቱና ገዢው መሆኑን አውቆ አማራ ጠል እንዲሆን፣ የኢትዮጳያ ታሪኳም ማንነቷም የርሱ አለመሆኑን ይልቅስ ኦሮሞ የራሱ ታላቅ ታሪክ ያለው ህዝብ መሆኑን በመስበክ በመጨረሻው የበደሉትን ሁሉ እንዲያጠፋና የገዛ ሃገሩን እንዲመሰርት ያዘዘበት መጽሃፍ ነው የቡርቃ ዝምታ።

ተስፋዬ ከቡርቃ ዝምታ በኋላ በደራሲው ማስታወሻ ውስጥ ባካተተው “ጫልቱ እንደ ሄለን” በሚል ልብወለድ ስራው ውስጥ የፈጠራት ጠንካራ እና ሃይለኛ የነበረች የኦሮሞ ወጣት ሴት እንዴት በራስ አለመተማመን ህይወት ስትገፋ እንደነበር፣ ስሟ ከጫልቱ ወደ ሄለን እንዴት እንደተቀየረባት እና ማንነቷን እንዴት እንዳጣች፣ እንዴት በዚህ ከባድ ጫና እና በደል ምክንያት ወድቃና ተጥመልምላ እንደቀረች፤ በመጨረሻም እንደሞተች በመተረክ የኦሮሞ ህዝብ እንደጫልቱ በራስ መተማመኑን ያጣ፣ በበደል ብዛት ጫንቃው የጎበጠ፣ወድቆ የቀረ ህዝብ መሆኑን በመመሰል ቁጭት ሊግት ሞክሯል። ታሪክ አዛብቶ አለቆቹ የሰጡትን ተልዕኮ በሚገባ አሳክቶም ዛሬም አይኑን ከዚህች ሃገር እና ከዚህ ህዝብ ላይ ማንሳት አልተቻለውም። ጫልቱን የኦሮሞ ወኪል አድርጎ በማቅረብ እንዴት ተሰባብራ፣ተንኮታኩታና ተጥመልምላ እንደወደቀችና በመጨረሻም እንደሞተች ሲናገር በውስጡ “ምን ትጠብቃላችሁ ሞታችሁ እኮ” እያለ ነው።

ተስፋዬ ገብረዓብ በተጠየቀ ቁጥር አኖሌ “ጭፍጨፋ ነበር” ብሎ አፉን ሞልቶ የሚናገርለት ፣ የወያኔ/ኢህአዴግ ስርዓትም ይህንኑ ተቀብሎ በአማራ እና ኦሮሞ ብሄሮች መካከል በገነባው የጥላቻ ሃውልት በሁለቱ ህዝቦች መካከል የማይታረቅ ቂም መኖሩን እንዲዘክር ብሎ ያስቀመጠው የሴራ ፖለቲካ መገለጫ ሃውልት ነው።

ወያኔ/ኢህአዴግ ተስፋዬን ፊት አውራሪ አድርጎ በዚህ መልክ የቀመረው የኦሮሞ እና አማራ የቂም ፖለቲካ ሲመነዘር አማራው የኢትዮጵያዊነትን ጥብቅና ይዞ ‘አንድነት ያለኔ ላሳር ነው ብሎ እንዲኮፈስ፣ “የአንድነት ቋሚ ተሚጋች ያለኔ ማንም የለም” በሚል ኩራት ውስጥ እንዲኖር፤ በአንጻሩ ደግሞ ኦሮሞው በመለየት እና በመገንጠል ፖለቲካ ላይ ብቻ ▶



እንዲሰራ እና እንዲደራጅ የማጥ መንገድ አመቻችቶ ተንዠ ሲጠብቅ የባጀ ሰው ነው። ተስፋዬ ገብረዓብ በህዝቦች የቁስል ስንጥቅ ውስጥ ቃሪያ ጨምሮ በሽታ የሚያጋግል እና በህመምና ስቃዩም ፌሽታ ሲያደርግ፣ አስመራ ኮምቤሽታቶ ገብቶ ፓራዲዞ ቡና ቤት ተቀምጦና የቆነጃጅት ወገብ አንቆ ቢራ የሚጠጣ ሰው ነው።ለዚህ ነው አማራና ኦሮሞን ለመለየት ሆን ተብሎ የተሸረበው ሴራ ዋና አስፈጻሚ የሆነው ተስፋዬ ገብረዐብ፤ ከሰሞኑ የኦሮማራ ጥምረት ክፍል ሁለት ጉባዔ ላይ የመነጋገሪያ አጀንዳ መሆኑ ብዙ የማይደንቀው።

አቶ አዲሱ አረጋ አምቦ ላይ በተዘጋጀው ቁጥር ሁለት የኦሮማራ ጥምረት ላይ እንደመሰከሩትም ከፍተኛ በጀት ተመድቦ ፣ ሰፊ ዝግጅት ተደርጎ ታሪክ በማዛባት እና የሃሰት ታሪክ በመፍጠር የሁለቱን ትልልቅ ህዝቦች ግንኙነት ለመበጠስ በርካታ ስራዎች ተሰርተዋል፣ ሴራዎችም ተሸርበዋል። ከነዚህ መካከልም የተስፋዬ ገብረአብ ልብወለዶች ዋኖቹ ናቸው ።

## የ" ኦሮማራ" ፎቢያ

## መለስ ዜናዊ እና ጌታቸው ረዳ

የአማራ እና ኦሮሞ ነገር ሲነሳ የቀድሞው የሕወሓት ሊቀመንበር እና የሃገሪቱ ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊ የተናገሩት ነገር ለሁሉም ሰው የማይረሳ ነው። "አማራ እና ኦሮሞ አንድ የሆኑ 'ለታ ድርጅቴ ሕወሓት አበቃላት " ነበር ያሉት። ከዘመናት በኋላ የቀድሞው ሕወሓት መሪ ኢህአዴግ ፈራርሶ፣ አዲሱ የለማ ቲም አገር መምራት ከጀመረ በኋላ ባህርዳር ላይ በተካሄደውና ብዙዎች "የኦሮማራ ጥምረት" በሚሉት የኦዴፓ እና አዴፓ አባላት ስብሰባ ወቅት የታየው አንድነት ያብከነከናቸው የሕወሓት ማዕከላዊ ኮሚቴ አባል አቶ ጌታቸው ረዳ ሙፈሪያት ካሚል በተገኙበት የራዲዮ ስቱዲዮ ውይይት ላይ የቀድሞ አለቃቸውን መለስ ዜናዊን ሃሳብ በሌላ አማርኛ ደገሙት። "አማራና ኦሮሞ አንድ ሆነ ማለት እሳትና ጭድ ተስማምተው ኖሩ እንደማለት ነው" አሉ። ቃል በቃል የአቶ ጌታቸው ንግግር ይህ ነበር።

" ግን እንደ መፈክር እነዚህ ሰዎች [የአማራ እነ ኦሮሞ ልሂቃን] ደፍረው የሚወጡበት ሁኔታ መፈጠር አልነበረበትም?። እንዴት ነው ተጨማሪ ቤንዚን ሳያስፈልግ ለከባድ ቃጠሎ ምክንያት ሊሆኑ የሚችሉት? [እሳትና ጭድ] "

## የሕወሓት አማራን እና ኦሮሞ ጠልነት ለምን?

ይህ ጥያቄ የብዙዎች ጥያቄ ነው። ሕወሓት ለምን አማራን የመደብ ጠላት አደረገው? ለምን ሁሌም በጥርጣሬ እና በፍርሃት ያየዋል? ለምንስ የዚህን ህዝብ ውድቀት እና ሰላም ማጣት ይመኛል? ለብዙዎች ግራ የሆነ ነው። ሕወሓት ከምስረታው መነሻ የትግል ስልቱ እና የማታገያ ስትራተጂው አማራ ጠል የሆነ ትግራዋይን መፍጠር እና ይህንን ህዝብ "ታሪካዊ ጠላት" ብሎ መመረዝ ነው። ሕወሓት በነአረጋዊ በርሽ በተጻፈው እና ከስድስት ወራት በኋላ በተቀየረው (በተሻሻለው) ማኒፌስቶው ሁለት ዋና ጉዳዮች ላይ አትኩሯል። ቀዳሚው የትግራይ መገንጠል ሲሆን ተከታዩ የአማራ ታሪካዊ ጠላትነት ነው። ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ተጠራርተው ደደቢት ለከተሙት 'ቀለም ቀመስ' የሕወሓት መስራቾች አማራ የትግራይ ህዝብ ጠላት እንዳልሆነ መስካሪ አያሻቸውም። በትግራይ ገጠራማ ክፍሎች ለሚኖረው ተራው ትግራዋይ በተመሳሳይ አማራ ጎረቤት ወንድም እህቱ እንጂ ታሪካዊ ጠላቱ መሆኑን አስቦም አያውቅም። በዘመነ መሳፍንትም ይሁን በአጼ ቴዎድሮስ ዘመን እንዲሁም በምኒሊክ ጊዜ እስከጣሊያን መምጫና መውጫ የአማራው ገዥ መደብ በተዋጋበት ጦርነት ለደረሰበት ሽንፈት ሁሉ የትግራይ መሳፍንቶችን ተጠያቂ ማድረጉ እሙን ነው። በጊዜው የውጭ ጠላት ሲመጣ በር ከፍተው፣ ቦታ መርተው በጊዜው የኢትዮጵያን ስልጣን ይዞ ለነበረው የብሄረ አማራ ገዥ ጠላትን ደጁ ድረስ ይዘውት የገቡት የትግራይ መሳፍንቶች ናቸው ይላል ታሪክ። በዚህ ሳቢያ መስፍንና ንጉሱ እርስ በርሱ ባንዳና ጀግና ሲባባልና ሲናቆር ቢኖርም፤ በሁለቱ ብሄር ህዝብ መካከል ግን የተቀሰቀሰ ቁርሾም ይሁን የተካሄደ ግጭት በታሪክ አልተመዘገበም። የዘመነ ወያኔ ልጆች ግን መሳቢያ ውስጥ ተቆልፎ ለጊዜው ከአይን ዘወር ያለውን 'የታላቋ ትግራይ ሪፐብሊክ' ምስረታ እውን ለማድረግ ከዚህ ጎረቤት ህዝብ ላይ ለም አፈር መሬቶችን ወደትግራይ ማጠቃለል ግን መሆኑ ታምኖበታል።ለዚህ ይረዳ ዘንድም አቶ አዲሱ አረጋ የልሂቃን ተረክ ያሉት እና በትክክልም ህዝቡን የማይወክለው ጸረአማራ ፖለቲካ ሊነዛ ግድ ሆነ ።

በአንድ ወቅት የኦሮሞ ልሂቃን የሆኑት ዶ/ር ነጋሶ ጊዳዳ በአኖሌ ሃውልት የቆመለት የኦሮሞ እና አማራ ከፋፋይ ፖለቲካ ላይ አስተያየታቸውን ሲሰጡ እንዲህ ብለው ነበር። "እኔ እስካሁን ምኒልክ እጅ ቆርጠዋል፣ ጡት ቆርጠዋል የሚል የፅሁፍ መረጃ አላገኘሁም"።



ፕ/ር መረራ ጉዲና በበኩላቸው በዚሁ ጉዳይ ላይ ከዶክተር ነጋሶ ጋር ተመሳሳይ አቋም እንዳላቸው ነው በሰጡት አስተያየት መገንዘብ የሚቻለው። "እኔ ስለ አኖሌ ታሪክ ወያኔ ሃውልት ሰርቶ ሲያስመርቅ እንጂ በኦሮሞ ታሪክ ሰምቸው አላውቅም" ነበር ያሉት።

ታዲያ ይህንን ታሪክ ሕወሓት/ኢህአዴግ ከየት አምጥቶ ፈጠረው? ዶክተር ነጋሶ "ኦሮሞ ከዛሬ 50 እና 40 አመታት በፊት ምሁር የለውም (ዘገምተኛ እና ጨለምተኛ) ነው ብል ስህተት አይደለም" ይላሉ።እንደአባባላቸው ኦሮሞ የራሱ ልሂቅ ኖሮት ቢሆን ኖሮ [የሕወሓት መሪዎች] እንደፈለጉ እና እንደ አመቻቸው የኦሮሞን ህዝብ በፈጠራ እና በውሸት ታሪክ ውስጥ ዘፍቀው አዕምሮውን ባላጠዙት ነበር። ምክንያቱም ይላሉ ዶክተር ነጋሶ። " የኦሮሞን የ 100 ታሪክ ያውም የውሸት ታሪክ ፅፈው የሰጡትና የሚተርኩለት በደማቸው ኤርትራዊ የሆኑ ባንዳዎችና ወያኔዎች ናቸው" በማለት ተስፋዬ ገብረአብን በዘወርዋራ ለመጥቀስ ሞክረዋል።

" ይህንን ልል የቻልኩት ኦሮሞ ምሁር የለውም ለማለት ሳይሆን ከእራሱ ከኦሮሞ አብራክ የፈለቁ የእውነተኛ ልጆቹን እውነተኛ ታሪክ ከማድመጥ ተቆጥቦ በባንዳዎች የተፃፈ የሐሰት ታሪክ ተሸክሞ የሙጥኝ ማለቱ ነው። እውነት እናውራ ከተባለ የወያኔዎች አላማ እና ምኞት አማራን እና ኦሮሞን በአገኙት አጋጣሚ እርስ በእርስ ማጫረስ ነው።" ብለዋል።

በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የታሪክ መምህር የሆኑትና በአሁኑ ወቅት የኢትዮጵያ ቅርስ ጥበቃ ባለስልጣን ምክትል ዋና ዳይሬክተር ረ/ፕ/ር አበባው አያሌው፤ በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ በአኖሌ ጡት ተቆርጧል ለሚለው ማረጋገጫ የሚሆን የታሪክ ሰነድ የለም ባይ ናቸው። አፈታሪኩ ከብሔርተኝነት ጋር ተያይዞ የተፈጠረ መሆኑንና አፈታሪክን መነሻ አድርጎ ሃውልት መገንባት ደግሞ የሴራ ፖለቲካ ውጤት መሆኑን ገልጸው ሃውልቱ

ጥላቻና ቂም በቀልን ከማንፀባረቅ የዘለለ ፋይዳ እንደሌለውም ተናግረዋል።

ዶ/ር ነጋሶ ጊዳዳ የሃውልቱን መገንባት ባይቃወሙም ነገር ግን ከአፈ ታሪክ የዘለለ ማረጋገጫ ሰነድ ባይኖርም ከታሪክ የመረጃ ምንጮች መካከል አንዱ አፈ ታሪክ በመሆኑ በጉዳዩ ላይ ጥናት ማድረግ ያስፈልጋል ባይ ናቸው።

" እኔ ይሄ ሃውልት የኦሮሞዎች ፍላጎት ያለበት ነው ብዬ አላምንም። የፖለቲካ ድርጅቶች ያሰሩት ነው የሚል እምነት አለኝ። በአጠቃላይ ግን ሃውልቱ ሁለቱ ትላልቅ ብሄር ብሄረሰቦች- አማራና ኦሮሞው እርስ በእርሳቸው ተጋጭተው ትልቅ የነበሩት ትንሽ እንዲሆኑ ታልሞ የተደረገ ሴራ እንጂ የኦሮሞን ህዝብ ለመጥቀም የተደረገ ስራ አይደለም። ሃውልቱ ለኦሮሞ ህዝብ ጥቅም ሳይሆን ጉዳት ነው የሚያመጣው። ከሌላው ብሄር ጋር ቅራኔ ውስጥ ይከተዋል። ከፍተኛ ጉዳትም ያስከትላል። ዛሬ የኦሮሞን ህዝብ እየበደሉ ያሉት እነሱ ናቸው " የሚሉት የኦፌኮ አመራር ፤ ዶ/ር ሞጋ ፍሪሣ ናቸው ለአዲስ አድማስ ጋዜጣ በሰጡት መግለጫ።

## የኦሮማራ ውልደት

እነሆ ለውጥ መጥቶ ያለፈው የሕወሓት/ኢህአዴግ አስተዳደር ቀንዱ ተመትቶ የጊዜው ፖለቲካ ዘዋሪዎች ወደአንድ ክለል ተሰባስበው እንዲሄዱ ዋናው ምክንያት የሁለቱ ብሄሮች ልሂቃን ደባውን ሰንጥቀው፣ በህቡዕ ያደረጉት የጋራ ትግል ውጤት ነው። በአማራ እና በኦሮሞው እምቢኝ ባይነት ሕወሓት ሲፈራው የኖረው ቁርጥ ቀን መጣበትና ሊቋቋመው ከሚችልበት አቅም በላይ ሆኖ 'ፋውል' ገባ። በዚህም ቁማሩን በራሱ መደብ ላይ ተበላ።

ሁለቱ ብሄሮች ሕወሓትን ወደጎን ዞር አድርገው ለዘመናት የተሰራባቸውን ደባ በመገንዘብ የጋራ አንድነት እንደሚያሻቸው ያመኑበት ሲመጣ፤ የኦሮማራ ጥምረት በይፋ ተቀናጀ። አስቀድሞ ኦሮሞ ያነሳው የኦሮሞ እምቢተኝነት ጎንደር ካነሳው የአማራ እምቢተኝነት ጋር ተዳምሮ ሕወሓትን ጨርቁን ሲያስጥለው፣ በውስጥ በኩል ደግሞ ሁለቱ ልሂቃን በጋራ ተቀናጅተው ቦረቦሩት። የውጭና የውስጡ ትግል ፍሬ አፈርቶ ሕወሓትን ሲሰነጣጥቀው፤ በራሱ ቀመር ተሸነፈ። የሕወሓት አስተዳደር በኢሬቻ እና መሰል የኦሮሞ ትግል ላይ የወሰደውን እርምጃ በመቃወም አማራው በጎንደር "የኦሮሞው ደም የኔም ደም ነው" የሚል መፈክር ይዞ የወጣ ጊዜ ነው የሁለቱ የተራራቁ ህዝቦች ጥምረት በገሃድ የታየው። ከዚያም በተረጋጋው ዘመን የእንቦጭ አረምን ለማረም ከኦሮሞ የተውጣጡ ልጆች ባህርዳር ሲዘምቱ "የእምቦጭ ፖለቲካ" ተብሎ ተሹፎበትም ነበር። በብዙ ስም ማጠልሸት መካከል እነዚህን ታላቅ ህዝቦች መለየት ከባድ ሆኖ ዛሬ የፖለቲካው መንበር በነርሱ ጽናት ላይ ተከትቦ ይታያል።

በዚህ ስሜት የተጠነሰሰው ኦሮማራ ከውልደቱ ዳዴ እስከመባያው ድረስ ጉዞው መልካም ቢመስልም፤ በሌላ በኩል ግን ከሁለቱም ወገን ይህንን አንድነት የተገዳደሩ እሳቤዎችም አልጠፉም። መኖሩ መልካም መሆኑ ብቻ ሳይሆን ግድ መሆኑም በሚገባው መጠን ትኩረት ስለማግኘቱ ጥያቄ አለ።

ኦሮማራ በቀደመ ጊዜው ባህርዳር ያደረገው የጥምረቱ አንደኛ ይፋዊ ማብሰሪያ ፕሮግራም ከቲም አባላቱ የአማራው ክንፍ ዋና ሰው የነበሩት አቶ ገዱ አንዳርጋቸው ከስልጣን እስኪለቁ ድረስ ሞቅታው አልበረደም ነበር። አቶ ገዱ ከኦሮሞ ህዝብ ጋር አማራውን ለማቀራረብ እና ጠንካራ ሃይል ለመመስረት ያደረጉት ጥረት ከሟቹ የአዴፓ ሰው አቶ ተስፋዬ ስራ ጋር ተዳምሮ ትልቅ ውጤት ላይ ደርሶም ነበር። በመሃል የተቀዛቀዘ ሊመስል ያለው የአቶ ገዱ ስልጣን መልቀቅ በራሱ ዶክተር ዐቢይን ክፉኛ አስተክዞ አንደነበር በስነስርዓቱ ላይ በነበረ ፊታቸው ተንጸባርቋል።

ያም ሆኖ ዶክተር አምባቸው ሲተኩ የመቀዛቀዝ ስጋቱ ተቀርፏል። ዶክተር አምባቸው "ሊያባሉን የሚሰሩ፣ እልቂት የሚደግሱልን አሁንም አሉና እንጠንቀቅ" ባሉበት የደሴው ህዝባዊ ስብሰባቸውን ተከትሎ፤ በከሚሴ እና አጣዬ ላይ "ኦነግ" ናቸው በተባሉ ሰዎች የደረሰው ውድመት እና ጥቃት ለዚህ ሴራ አንድ ማሳያ ነውም ተብሏል። የዚህን ጥምረት እውነት የማይፈልጉ አካላት ይህንን በማጉላት "አማራ በኦሮሞ ተጨፈጨፈ" በማለት በማህበራዊ ሚዲያው ላይ የነዙት ሴራ ብቻ ሳይሆን በኦሮምኛ ተናጋሪ ሰዎች ጥቃት እና ዝርፊያ ሲፈጸም በተግባር ያሳዩት ተንቀሳቃሽ ምስል አስገራሚና ከባድ ሴራ ስለመጎንጎኑ ማመልከቻ ነውም ተብሏል። ይህ ሁሉ ሆኖም አሁን ድረስ የዚህን ሁለት ታላቅ ህዝብ ማባላት ሴራ ከልሂቃን ቋንቋ ወርዶ ህዝብ ላይ አልገባም።

በቅርቡ ታሪክ በሚገባ የተገነዘቡ ናቸው የተባሉት አዲሱ የኦሮሚያ ክልል ፕሬዚዳንት እንደተሾሙ አዳማ ላይ ታስቦ የነበረው ክፍል ሁለት የኦሮማራ ጥምረት ማወጃ አምቦ ሲሆን የአማራ ክልል ፕሬዚዳንት ዶክተር አምባቸው የመሩት ቡድን በስፍራው ተገኝቶ ውይይቶች ተካሂደዋል። ይህንን አንድነት ለማጠልሸት በዶክተር አምባቸው ላይ ሴራ ቀመስ ስም ማጥፋት ተነዝቷል። በአማራ ክፍለሃገር "የኦሮሞ አምባሳደር" የሚል ቅጽል እየተሰጣቸው፣ ስለአዲስ አበባ ልዩ ጥቅምም ሆነ ስለኦሮሞ ህዝብ ማን ተናገር አለህ? ተብለዋል። ዶክተር አምባቸው ቀድሞም በደሴው ጉባዔ ላይ አዲስ አበባ የሁሉም ህዝብ መናኸሪያ መሆኗን እና ኦሮሚያ በአዲስ አበባ ላይ ያላት የልዩ ጥቅም መብት ሊከበር እንደሚገባው፤ ከዚያ ያለፈ ግን ባለቤትነት የሚባለው ጉዳይ እንደሌለ ለአማራ ህዝብ ይፋ አደርገው ነበር። በአምቦም ከዚህ የተለየ የተናገሩት ነገር የለም። ነገር ግን ይህ ንግግራቸው በሌላ ተተርጉሞ የአማራን ህዝብ ለኦሮሞ ጥቅም ሸጡ ሲባሉ የሚያስገርም እንጂ የሚገርም ነገር የለውም። ምክንያቱም ብዙዎች የዚህ ጥምረት አመክንዮአዊ አስፈላጊነት ላይ የሚስማሙ ወገኖች ወደፊትም ጥምረቱ ገና ብዙ ፈተና ሊጠብቀው እንደሚችል ይናገራሉና ነው።

## የጥምረቱ እንቅፋቶች

አዲስ አበባ ለሴረኛ ፖለቲከኞች የዚህ ጥምረት ማፍረሻ የጨዋታ ሜዳ ሆና የቀረበች መስላለች። በዚህ በኩል አማራው የአዲስ አበባ ነዋሪነት መብቱ በኦሮሞ ሊቀማ መሆኑን በመንገር፣ በዚያ በኩል ኦሮሚያ የአዲስ አበባ ዋና ከተማ ብቻ ሳትሆን የግል ርስት ናት በማለት የማይተማመን ህዝብ እንዲፈጠር እየሰሩ ነው። በህዝቦቹ መካከል መጠራጠር ተፈጥሮ ሽኩቻ እንዲነሳ የየብሄሩ ልሂቃን የሚናገሩትን እያጦዙ እና እያናሩ ለማዛባት እየሞከሩም ነው። በግልጽ እንደሚታወቀው እና የሕወሓት መሪ መለስ ዜናዊ እንደተነበዩት የሁለቱ ህዝቦች አንድነት የሕወሓት መጥፊያ መርዝ በመሆኑ ላለመጥፋት የሚካሄድ ማናቸውም መንፈራገጥ ለዚህ ጥምረት ስጋት እንደሚሆን ማሰብ አይገድም።

በሌላ በኩል በዚህ ሴራ የተወናበዱ የየብሄረሰቡ አባላት በጥምረቱ ላይ የሚያነሱት ጥያቄ ብቻ ሳይሆን ተቃውሞ ጥምረቱን ባያከስመውም እንደተፈለገው እንዳይራመድ እንቅፋት ሊፈጥርበት እንደሚችል ማሰብ ተገቢነት ላይ ያተኩራል። አ.ብ.ን የተባለው ፓርቲ ከወዲሁም ጀምሮ የሁለቱን ጥምረት በአይነቁራኛ የሚመለከት አካል ነው። ሲጥመው አልታየም። በዚያ ወገን ኦነግ ይህንን ጉዳይ የሚፈልገው አይደለም። ከነዚህ ሁለት ድርጅቶች ጀርባ ማን አለ የሚለው ደግሞ በብዙዎች የሚገመት ነው። አቶ አዲሱ አረጋ ተስፋዬ ገብረአብን ተችተው "ጡት ቆራጭ" የሴራ ትርክትን አሂሰው አምቦ ላይ ቢናገሩ፤ በማግስቱ እዚያው አኖሌ ሃውልት አካባቢ ያሉ ወጣቶች የአቶ አዲሱን ፎቶ "ነፍጠኛ" ከሚል ጽሁፍ ጋር ይዘው ወጡ። ቀጠሉና ተስፋዬ ገብረአብን ፎቶ ይዘው እና የአቶ አዲሱን ፎቶ በቀይ ቀለም ሰርዘው አኖሌ የታሪካቸው መገለጫ መሆኑን በሰልፍ ተናገሩ። ብዙዎቹ የቡርቃ ዝምታንም ሆነ ተስፋየ ገብረአብን አያውቋቸውም። የተነገራቸውን ይዘው፣ የተሞሉትን አየር የሚተነፍሱ ናቸው። ይህ ከራስ የሚመጣ ተግዳሮት በስሌት የተሰራ ሴራ ውጤት ነው።

በሌላ በኩል ዶክተር አምባቸው ለስነስርዓቱ የተቀዳላቸውን ጠጅ ሲቀበሉ ሲታይ "በጠጅ የተጀመረ ማህበር አይዘልቅም" ከሚል ፌዝ ጋር የሁለቱን ታላላቅ ህዝቦች የጥምረት ፍላጎት ማንኳሰስ እና ዶክተሩ በንግግራቸው የጠቀሱትን የኦሮሚያ በአዲስ አበባ ላይ ያላት ጥቅም ጉዳይ እንደማይመለከታቸው አድርጎ ማቅረብ፤ እንዲሁም በአማራ የኦሮሞ ጉዳይ አስፈጻሚ አድርጎ ስም ማጥፋት በዚያ ወገን ከራስ የተሰነዘረ ሴራ ውጤት ነው።

## ምስጣር ወይስ ምሳር

ይህ የዘመናችን የቅርርብ ፖለቲካ ነዳፊ ኦሮማራ እንዲህ እንዲህ ብሎ የግርግሩን ዘመን ሲሻገር እና ከኋላ ያለው ጎታች ሃይል ተመትቶ ሲዳከም ግን በርግጥም ነጥሮ መውጣቱ እና ማንጸባረቁ አይቀሬ መሆኑን ብዙዎች ይተነብያሉ። በእንቅፋቶች ተጎትቶ ከተሰነካከለ ግን አማራ እና ኦሮሞ ዳግም በእሳት ውስጥ ተማግደው ስጋቸው ለጅቦች መጫወቻ የማይሆንበትን እድል ማየት ከባድ ይሆናል። የዚህ ለውጥ መስመር እየተንገዳገደ እና እየተንጋደደም ቢሆን ወደቀጥታ መስመሩ መግባቱ አይቀርም እና ኦሮማራ እንደብዙዎቹ የትብብር ፖለቲካ ደጋፊዎች የለውጡ ማጥበቂያ ምስማር እንጂ የለውጡ መቁረጫ ምሳር እንዳልሆነ ለመመስከር በዙ ጊዜ አይፈጅም። ጥቂት አመት ብቻ መጠበቅ የዚህችን ሃገር ለውጥ ቆሞ ለመታዘብ በቂ ይሆናል።

# ጥቁር አንበሳን ወደ ቀደመው ክብሩ መልሱልን!




ከቅርብ ጊዜያት ወዲህ በተለያዩ የአለም ክፍሎች በተለይም በታዳጊ አገራት ውስጥ የሚገኙ የህክምና ባለሙያዎች ከመንግስታቶቻቸው ጋር እሰጥ አገባ ውስጥ እየገቡ ቀርቶብናል ያንሰናል ወይም ደግሞ ጭራሹኑ አልተሟሉልንም የሚሏቸውን የመብት ጥያቄዎች በማንሳት የስራ ሰዓት ላይ አድማና ግፋ ሲልም ሙሉ የስራ ማቆም አድማ በማድረግ ጫና ሲፈጥሩ ማስተዋል የተለመደ ሆኗል። መብቶቻቸውንና የስራ ቦታ ላይ ደህንነትና ዋስትና አለመከበርን፤ እንዲሁም የደሞዝ ማነስን ተንተርሰው ከአገራቸው ለመውጣትና ለመሠደድ እንደሚገደዱም የሚታይ ሲሆን፤ በዚህ ዓይነት ችግር ውስጥ ከሚገኙት ተጠቃሽ አገራት አንዷ አገራችን ኢትዮጵያ መሆኗ ይታወቃል። በተለያየ ግዜ ከላይ የተጠቀሱትን ጥያቄዎች በማንገብ መንግስትን የተማፀኑ ቢሆንም፤ ይህ ነው የሚባል ምላሽ ባለማግኘታቸው አሁንም ቢሆን እየተነሱ ናቸው።

ሚያዝያ 14 ቀን 2010 ዓ.ም በጥቁር አንበሳ ስፔሻላይዝድ ግቢ የጤና ሳይንስ ዕጩ ዶክተሮችና ተዛማጅ ሙያተኞች ተመሳሳይ የሆነ ሠላማዊ ሠልፍ አካሂደዋል። ከሣምንት በፊት በጅማ ዩኒቨርስቲ በሁለት የመጨረሻ አመት የህክምና ተማሪዎች ላይ በተጨማሪም አርሲ ላይ መብቶቻቸውን ለማስከበር የተለያዩ ጥያቄዎችን አንግበው በመውጣት በሠላማዊ መንገድ ሀሳባቸውን እየገለፁ ሳለ በፌደራልና በፖሊስ ሠራዊት መደብደባቸውንና ሲያክሙ የነበሩ ሀኪሞች ታካሚ ሆነው በሆስፒታል ህክምና ላይ መሆናቸውን የጠቀሱት እነዚሁ ሰልፈኞች "ሙያችን ተደፍሯል መብቶቻችን እየተጣሱ ነው፤ የምንወደውን የህክምና ሙያ እንድንጠላ አታስገድዱን" የሚሉ መፈክሮችን እያሰሙ በነጭ ጋዋናቸው አሸብርቀው ወደ ፋና ብሮድካስት ሰርቪስ ቅጥር ግቢ በመንዝ በራፍ ላይ ሆነው በተደጋጋሚ ድምፃቸውን አሰምተዋል።

"በየትኛውም ቦታ በህክምና ባለሙያዎች ላይ እየተፈፀሙ ያሉት የመብት መከልከሎችና አደጋዎች መቆም አለባቸው፤ በጅማ፣ በአርሲም ሆነ በሌሎች ቦታዎች ላይ የተደረጉት ሠላማዊ ሰልፎች ፍፁም ሠላማዊ የነበሩ የመብት ማስከበር ጥሪዎች ነበሩ፤ ነገር ግን በህክምና ባለሙያዎቹ ላይ ተጨማሪ የመብት ጥሰት ደርሶባቸዋል፤ ስለዚህ ይህ እኛንም እንደሚመለከተን ለማሳየት ነው ሠልፍ የወጣነው" የህክምና ተማሪዎቹ።

ሠልፈኞቹ ጉዳያቸውን ወደሚመለከተው አካል ሄደው ከማቅረብ ይልቅ ወደ ፋና ብሮድካስት ቢሮ የሄዱበትንም ምክንያት ‹‹ ጥያቄያችንን ለሚመለከታቸው አካላት አቅርበን ምላሽ አላገኘንም። ስለዚህ የሚዲያ ሽፋን አግኝተን ህዝቡ በምን ዓይነት ችግር ውስጥ እንዳለን እንዲያውቅልን ነው። እስከመጨረሻው ድረስ መብቶቻችንን ለማስከበር ተጠናክረን እንሰራለን፤ ሁሉም ሠው ችግራችንን እንዲሠማንና ከጎናችን እንዲቆም በማሰብ ነው ብለዋል።

ሙያተኞቹ እንደሚሉት በየትኛውም ደረጃ ላይ ያለ የህክምና ባለሙያ በቂ ገንዘብ እንደማይከፈለውና ለረጅም አመታት በትምህርት እና በልምምድ ከመቆየታቸው አንፃር የማይመጣጠን፤ ድካማቸውንም ከግንዛቤ ያላስገባ መሆኑ ለጥያቄዎቻቸው መነሻ ሆኗል።

በእርግጥም የህክምና ሙያ ከመደበኛ የሥራ ሰዓቶች በተጨማሪ በድንገትና በትርፍ ሰዓት ጭምር ህይወትን ለመታደግ የሚሰራ ሥራ በመሆኑ በሙያተኞች ላይ ከአካላዊ እስከ ስነልቦናዊ ድካም ያስከትላል። በተለይ እንደ ኢትዮጵያ ባሉት አገራት አንድ ሀኪም በጣም የብዙ ሰውን ህይወት ለመታደግ የቆመ በመሆኑ ተገቢውን እንኳ ባይሆን ተመጣጣኝ ክፍያ ሊኖረው እንደሚገባ አያጠራጥርም።

በሌላም በኩል አሁን ባለው ሁኔታ ከስራ ሰዓት ውጪ በሚሰጡት ግልጋሎት ላይም ቅሬታ እንዳላቸው በሰልፉ ላይ ተሳታፊ ነየነበሩ የህክምና ባለሙያዎች ይናገራሉ። በዚህ አሰራር አንድ ባለሙያ ተጨማሪ ሰዓቶችን በመስራት ያለውን አቅም አሟጦ እንዲሰራ ከመገደዱ ውጭ በእንቅልፍ እጦት እንደሚሰቃይ ገልፀው ቢያንስ ህብረተሰቡን አገልግለን እንኳ ተመጣጣኝ ክፍያ ለትርፍ ሰዓት ሊከፈለን ይገባ ነበር፣ ሆኖም አሁን እንደ እጩ ዶክተር እየተሰጠን ያለው ገንዘብ እጅግ አነስተኛ ነው ብለዋል።

በቀን አንድ መቶ ሀያ ብር እንደሚከፈላቸው የሚናገሩት ሀኪሞች ገንዘቡን በወር ሲያሰሉት ሦስት ሺ ስድስት መቶ ብር መሆኑን ጠቅሰው ይህም አነስተኛ ክፍያ እንደሆነና የትርፍ ሰዓት ክፍያ ያለመኖሩ ደግሞ ሌላው ችግር ነው ይላሉ።

ሀኪሞቹ በመፈክራቸው ሲያሰሟቸው ከነበሩት ጥያቄዎች ሌላኛው በስራቸው ላይ ሆነው ለሚገጥሟቸው የጤና መታወኮች ማካካሻ የሚሆን ክፍያ (Risk payment) ያስፈልጋል የሚልም ይገኝበታል። ጥያቄውንም እንዲህ በማለት ያብራሩታል። ‹‹Risk payment የምንለው የህክምና ባለሙያው ታካሚዎቹን በሚረዳበት ወቅት የተለያየ አይነት የጤና መታወኮች ሊገጥሙት ይችላል። ለምሳሌ ተላላፊ የሆኑ በሽታዎችን ማንሳቱ ይበቃል፡፡ ኤች.አይ.ቪ፣ ቲቢ፣ ወይም የጉበት በሽታና የመሳሰሉት በብዙ ሠዎች ላይ የሚከሰቱ በመሆናቸውና ሀኪሙም ቀጥተኛ ግንኙነት ስለሚኖረው ለዚሁ ማካካሻ የሚሆን ታሳቢ ክፍያ ሊደረግልን ይገባል። ይሄ አሰራር ደግሞ በየትኛውም አለም የተለመደና የታወቀ ነው፤ በተጨማሪም አንድ የህክምና ባለሙያ ባለው ጊዜ ሁሉ በመቶ ሺህና በሚሊዮን የሚቆጠሩ ህመምተኞችን አክሞ ሊያድን ይችላል፡፡ ይረዳልም። ነገር ግን እሱ የህመም ችግር ቢያጋጥመው ምናልባትም ታክሞ ለመዳን እንኳ የሚቸገርበት አጋጣሚ ይከሰታል በመሆኑም ራሱ ሀኪሙ የጤና ዋስትና ሊሰጠው ግድ ይሆናል ሲሉ ለሪፖርተራችን ተናግረዋል።

በዕለቱ የተደረገውን ሠላማዊ ሠልፍ ካስተባበሩት ሀኪሞች አንዱ እጩ ዶ/ር አገሩ ዘለቀ ሌሎችንም የሙያ አጋሮቹን በመወከል ‹‹እኛ ላይም ሆነ የቀደሙት ሀኪሞች ላይ ብዙ ችግሮች አሉ። ለምሳሌ አሁን ሀኪሞች የብቃት ማረጋገጫ እንዲይዙ የሚል መመሪያ ወጥቷል። በመሰረቱ የህክምና ባለሙያ ግማሽ በግማሽ የሚሆነው ትምህርቱ በተግባር የተደገፈና ቀጥተኛ የሆነ የህክምና አገልግሎት የታከለበት፤ በየጊዜው የሚፈተንበትና በየዕለቱ ሙያውን የሚያረጋግጥበት ሂደት ነው። ነገር ግን አሁን ሌላ ፈተና ተዘጋጅቷል የብቃት ማረጋገጫም ማግኘት አለባችሁ ተብሏል። በመሆኑም የምንወደውን የህክምና ሙያ እጅግ እንድንሸሽውና በራስ መተማመናችንን እንድናጣ እየተደረገ ስለሆነ ፈተናውን ፈፅሞ የማንቀበለው ነው፤ ሙያችንም ሊከበር ይገባዋል›› ብሏል።

በጥቁር አንበሳ ጤና ሳይንስ ኮሌጅ የመጨረሻ አመት እጩ ተመራቂዎችና ሌሎች ሙያተኞች ያሳተፈው ሠላማዊ ሠልፍ ላይ ሀኪሞቹ የግቢያቸውንም አሰራር በተመለከተ ‹‹የጥቁር አንበሳ ሆስፒታል በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ስር የሚተዳደር በመሆኑ የሚመደብለት በጀት እጅግ አነስተኛ ነው። ነገር ግን በጠቅላላ አገሪቱ ውስጥ ካሉ ሆስፒታሎችና ጤና ጣቢያዎች ሁሉ በሪፈር የሚመጡ ታካሚዎችን የሚያስተናግድ በመሆኑ ከፍተኛ የሆነ የቁሳቁስና የህክምና መገልገያ መሳሪያዎች እጥረት ያጋጥመዋል። ሌሎቹ በከተማዋ የሚገኙ ሆስፒታሎች ያላቸውን ያህል በጀት እንኳ ስለሌለው ለህክምና ባለሙያዎች ከባድ ፈተና ሆኖ ይታያል። በሌላ በኩል አብዛኛው ታካሚ በነፃ የሚታከም በመሆኑ በገንዘብ ራሱን የመደገፍ አቅሙ አነስተኛ ነው፤ ተቋሙ የበጀት እጥረት እንዳለበት ግልፅ ቢሆንም የሀኪም ዋነኛ ስራው ታካሚውን በአግባቡ መርዳት በመሆኑ የመርጃ መሳሪያዎችን ካላገኘንና ህመምተኛውን ማከምይከብዳል፤ስለዚህ አሁን ባለው ሁኔታ ታካሚዎቻችንን ማርካት አልቻልንም›› ብለዋል፡፡ በሆስፒታሉ አስተዳደርና በአቅርቦት በኩል ያለው ችግር ስመጥር የነበረውን ማዕከል ሥምም እያጠፋ እንደሆነ የሚናገሩት ሠልፈኞች በሠልፉ መሀልም ‹‹ጥቁር አንበሳን ወደ ቀደመው ክብሩ መልሱልን! ›› የሚል መፈክር ማሰማታቸውን ታዝበናል።

# የአዴፓና ኦዴፓ “ሽርክና” ብቻውን መፍትሄ አይሆንም ! ! !

የአማራና የኦሮሞ ሕዝቦች ለዘመናት ተጋብተውና ተዋልደው፣ ተፈቃቅረውና ተከባብረው ኖረዋል፡፡ በኢትዮጵያ ካሉ ብሔር ብሔረሰቦች ሁሉ በላቀ መልኩ አብዛኛውን የሕዝብ ብዛት ቁጥር የሚሸፍኑት እነዚህ ሕዝቦች፤ ከብረት የጠነከረ አንድነታቸውን ለመስበር ብዙ ተደክሟል፡፡ ከ”አፈ ወሬነት” ያልዘለሉ፣ አንዳችም ለእውነታነት የቀረቡ ማስረጃዎች ሊገኙ ያልቻሉባቸው “እንቶ ፈንቶዎች” እየተነገሩና እየተፃፉ የአማራና የኦሮሞ ተወላጆች ቅራኔዎችን ለማስፋት፣ ደም ለማቃባት ያለመታከት መሰራቱንም ታዝበናል፡፡

በተለይም ባለፉት ሀያ ሰባት ዓመታት ሕወሓት መራሹ መንግስት፤ ለራሱ “የተደለዳለ ስልጣን” ሲል ሁለቱን ብሔሮች በማቃቃር ረገድ ዓይነተኛ ሚና ተጫውቷል፡፡ ሕወሓት “ኦሮሞና አማራ አንድ ከሆኑ ለእኛ አደጋ ናቸው፤ የኢትዮጵያዊነትን መንፈስም በእጅጉ ያሳድጋሉና ሁለቱ ሕዝቦች ፈፅሞ ፍቅር መሆን የለባቸውም” የሚል መመሪያን ይከተል ነበር፡፡ ይህን እሳቤ የ”ጫካው ቡድን” ስልጣን ከያዘም በኂላ ባልተፃፈ ህግ ውስጥ አካቶት ሲሰራበት ቆይቷል፡፡

“የከፋፍለህ ግዛ” ስርዓቱ 4 ኪሎ ቤተ መንግስት በደረሰ ማግስት በበደኖ፣ በወለጋና በተለያዩ አካባቢዎች ብሔር ተኮር ግጭቶችን በመቀስቀስ (ጭፍጨፋ ጭምር በማካሄድ) ያሰበውን በተግባር ከማሳየቱ ባሻገር፤ እንደ “አኖሌ ሐውልት” የመሰሉ ትውልድ የሚሻገሩ የበቀል ማሳያዎችን በመገንባት፣ ከእውነተኛ ታሪክ ባፈነገጠ መንገድ ሰዎች በጥላቻና በክፋት ስሜት እንዲበረዙ ትኩረት ሰጥቶ ሰርቶበታል፡፡ ሕወሓት ይህንን የቤት ስራውን ባማረ ሁኔታ እንዲያከናውን ደግሞ በአምሳልና በቅርጹ “ጠፍጥፎ የሰራቸው”፣ ሲጠራቸው “አቤት” ሲላኩ “ወዴት” ከማለት ውጪ “እንወክለዋለን” ለሚሉት ሕዝብ አንዳችም በጎ ነገር ያልሰሩት የኦህዴድና ብአዴን (አሁን ኦዴፓና አዴፓ) አመራሮች በእጅጉ ረድተውታል፡፡

ከእነዚህ ሁለት የወያኔ አስፈፃሚ ከነበሩ ድርጅቶች ባሻገር፤ በተለይም የኦሮሞ ተወላጅ የሆኑ ምሁራን፣ የፖለቲካ ፓርቲ መሪዎችና አክቲቪስቶች፤ የመለስ ዜናዊ ቡድን የተከለውን “የዘረኝነትና የጥላቻ መርዝ” በእጥፍ በማሳደግ፣ ችግሮቹ እየተባባሱ ከመሄድ ባሻገር አንዳችም መፍትሄ እንዳያገኙ የበኩላቸውን አስተዋፅኦ አድርገዋል፡፡ በቅርቡ በከሚሴ፣ በአጣዬ፣ በማጀቴና አጎራባች አካባቢዎች በተመሳሳይ ቀንና ሰዓት የደረሰው፤ “ማንነትን የተመረኮዘ ጥቃት” ከላይ በጠቀስናቸው መልኮች ለዘመናት ሲስተጋቡ የኖሩ፣ በሰዎች አዕምሮ ውስጥ የሥረፁ መጥፎ የጥላቻና የበቀልተኝነት ስሜት የወለዷቸው ውጤቶች ናቸው፡፡ በሀሰት አንዱን ብሔር አጥፊ፣ ሌላውን ተጎጂ አድርጎ የሚቀርብ ትረካ፤ ጊዜውን ጠብቆ ከዚህ ላለፈ ወደ ለየለት ዕልቂትና የብሔር ግጭት ማምረቱ እንደማይቀር ሰሞነኛው ክስተት አመላካች ነው ማለት ይቻላል፡፡

ባሳለፍነው ሳምንት በአማራና በኦሮሞ ሕዝቦች መሀከል የተፈጠረውን ውጥረት የማርገብ መንፈስ ያነገበ የሚመስል ውይይት በአምቦ ከተማ ያደረጉት የሁለቱ ፓርቲዎች(የአዴፓና ኦዴፓ) የጋራ እንቅስቃሴ፤ በራሱ የሚሰጠው የተስፋ ጭላንጭል መኖሩ ባይካድም፣ አስቀድሞም ቢሆን ችግሩ የተፈጠረው በሁለቱ ድርጅቶች መሀል አለመግባባት በመኖሩ ወይም የእነርሱ እርስ በርስ ግጭት የወለደው አለመሆኑ ሊታወቅ እንደሚገባም መረዳት ያስፈልጋል፡፡

እንደ ድርጅት ሁለቱ ፓርቲዎች ግንኙነታቸውን ይበጀናል ባሉት መንገድ ሊያስኬዱት ይችላሉ፡፡ ሀቁ ግን ከዛ ከፍ ማለት አለበት፡፡ ኦዴፓ እና አዴፓ በአዳራሽ ተወያይቶ ከመለያየት በዘለለ፣ ብዙ ጊዜ ችግር በሚፈጠርባቸው፣ በተለይም ዜጎች በተፈናቀሉባቸው የኦሮሚያ ከተሞችና መንደሮች ድረስ ዘልቀው በመግባት፤ ከታች የሚገኘውን ማህበረሰብ ማወያየት፣ ማንቃትና ማስተማር፣ ከዘረኝነት አስተሳሰብ ማላቀቅ ይጠበቅበቸዋል፡፡ የኦሮሞና የአማራ ሕዝብ እንደ ጥንቱ ተፋቅሮና ተከባብሮ፣ ሁሉም በነፃነት የመኖር መብት እንዳለው ብሎም ከአጥፊ ፖለቲከኞችና አክራሪ ብሔረተኞች አስተምህሮት መራቅ እንዳለባቸው ጭምር ሕብረተሰቡን የማስረዳት ኃላፊነት የእነዚህ ፓርቲዎች ግዴታ መሆኑ ፈፅሞ መዘንጋት የለበትም፡፡

የዛሬ አንድ ዓመት ገደማ በጣና ሀይቅ ላይ የተከተሰተውን የእንቦጭ አረም ለማስወገድ፤ የኦሮሚያ ልዑካን ቡድን ወደ ባህርዳር በመጓዝ ያደረገው ድጋፍና እንቅስቃሴ፤ የሁለቱን ሕዝቦች አንድነት ጥንት ወደ ነበረበት አስተማማኝ መንፈስ ይመልሰዋል ተብሎ በተነገረ የሳምንት ዕድሜ ውስጥ በርካታ የአማራ ተወላጆች “መሬታችንን ለቃችሁ ውጡ” በሚል ሀብት ንብረታቸውን ተዘርፈው፣ የባህርዳር አስፋልቶችና አብያተ ክርስቲያናት በተፈናቃዮች የተሞሉበት ትዕይንት መመልከት በእጅጉ አንገት የሚያስደፋ ተግባር ነበር፡፡

ያኔ የተጀመረው የማፈናቀል ሂደት፤ ዛሬ ወደለየለት ብሔር ተኮር ጥቃት በተሸጋገረበት ወቅት አዴፓና ኦዴፓ በአዳራሽ ውይይት የብዙ ሚሊዮኖችን ችግር ለመፍታት መሞከራቸው ጉዳዩን የበለጠ ከማወሳሰብና ከማሳደግ ባሻገር “ጠብ” የሚል መፍትሔ ስለማይኖረው፣ ከአክራሪ ብሔርተኛ የፖለቲካ ፓርቲ አመራሮች፣ እስከ አክቲቪስትና ልሂቃን ነኝ ባዩ፤ እንዲሁም በቡድን እየተደራጀ በዝርፊያ፣ በአስገድዶ መድፈርና የሰው ሕይወት እስከ ማጥፋት ድረስ የከፋ እርምጃ እየወሰደ የሚገኘው አካል ላይ በተከታታይ ጠንከር ያሉ ዕርምጃዎች እስካልተወሰዱ ድረስ ልዩነቱን ማጥበብ አይቻልም ብለን እናምናለን፡፡


**ግዮን መጽሔት**

**ኢትዮ ሐበሻ ኅትመትና ማስታወቂያ ኃ/የተ/የግ/ማኅበር በየሳምንቱ ለኅትመት የምትበቃ መጽሔት**

**ማኔጂንግ ዳይሬክተር**
ፍቃዱ ማ/ወርቅ

**ዋና አዘጋጅ**
ሮቤል ምትኩ
አድራሻ፡- የካ ክ/ከተማ ወረዳ 2 የቤት ቁጥር 475

**ተባባሪ ዘጋቢያችን**
ቶማስ አያሌው(**ከአሜሪካ**)

**ከፍተኛ አዘጋጅ**
ብሩክ መኮንን
መለስ ሽኔ

**አምደኞች**
ፍቅሩ ኪዳኔ (**ከሲውዘርላንድ**)
ዶ/ር ዘሪሁን ሙላቱ
መስፍን ጌታቸው
አስማማው ኃ/ጊዮርጊስ(**ከአሜሪካ**)
ተስፉ (ኢትዮጵያ) አልታሰብ
ታምራት መርጊያ

**ጸሐፊ**
ሠላም ግርማ

**ክርኤቲቭ ዲዛይን**
ባሳዝነው ወንድምነህ

**የዝግጅት ክፍሉ አድራሻ**
አራዳ ክ/ከ ወረዳ 09 የቤት ቁጥር 552/1
አምባቸው ህንፃ 2ተኛ ፎቅ ቢሮ ቁ. 207
ፖስታ ቁ. 676 ኮድ 1029
ስልክ ፡ +251 911 227661
+251 912 165606
+251 118 12 2333
ኢ-ሜይል፡
enqu2013@ gmail.com
Ghion2011meg@gmail.com
Facebook
Gihon-meg Fekadu
www. facebook.com/enqu2013

**አታሚ**
ቴዎድሮስ ገብሩ ማተሚያ ቤት ፤ አራዳ ክፍለ ከተማ
ወረዳ 10 የቤ.ቁ. 066/ሀ


በዚህ መጽሔት ላይ የሚወጡ ጽሑፎች በሙሉ ማተሚያ ቤቱን አይመለከትም



ታዴዎስ ግርማ

# የትንሳኤው ትርጉም "ትንሳኤ" ለሚያስፈልጋት ሀገር



ቅድስት ቤተ ክርስቲያን ከትንሣኤ በፊት ያለውን አንድ ሳምንት "ሰሙነ ሕማማት" /የሕማማት ሳምንት/ በማለት ትዘክረዋለች፡፡ "ሕማማት" የሚለው ቃል "ሐመ፤ ታመመ" ከሚለው የግእዝ ግስ የወጣ ሲሆን፤ የጌታችንና የመድኀኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሕማምና ሞቱ የሚዘከርበት ሳምንት ነው፡፡ በዚህ ልዩ በሆነ ሳምንት ካህናትና ምእመናን በነግህ፣ በሠልስት፣ በቀትር፣ በተሰዓትና በሠርክ ወደ ቅድስት ቤተ ክርስቲያን በመጓዝ ስለ ጌታችን ኢየስስ ክርስቶስ ሕማማተ መስቀል የሚያዘክረውን ምዕራፍ ከቅዱሳት መጻሕፍት በማንበብና በመጸለይ ሕማሙንና ሞቱን ያዘክራሉ፤ አብዝተው ስግደትን ይሰግዳሉ፡፡ ሰሙነ ሕማማትን ከሌሎች የዐቢይ ጾም ሳምንታት ልዩ የሚያደርገው ሥርዓት ምንድነው? ስንል፤ በኦርቶዶክስ ተዋሕዶ አብያተክርስቲያናት ሥርዓትና ደንብ መሠረት በሰሙነ ሕማማት ከጸሎተ ሐሙስ በስተቀር ቅዳሴ አይቀደስም፣ ስብሐተ ነግህ አይደረስም፣ ጸሎተ ፍትሐት አይጸለይም፣ ጸሎተ አስተስርዮም አይደረግም፡፡ እንዲሁም ጥምቀተ ክርስትናም አይፈጸምም፡፡

ከላይ የተዘረዘሩት የቤተ ክርስቲያን ሥርዓቶች አስቀድሞ በዕለተ ሆሳዕና ይከናወናሉ፡፡ ስለዚህ በዚህ ሰሞነ ህማማት የታመመች ሀገር ፈውስ የምታገኝበት ወቅት ነበር፤ ምን ዋጋ አለው? ሀኪሙም፣ ታማሚውም በዚህ ዘመን ሁሉም ታሟል:: ታማሚዋ ሀገር በዘረኝነት በሽታ አልጋ ከያዘች ከራረመች፡፡ ማን ይፈውሳት? የእምነት ተቋማት? መንግስት? ሁሉም ታመዋል፡፡ ሰው ሲታመም ወደ ጤና ባለ ሙያ ይሄዳል፤ ከባለ ሙያውም ምክር መድሃኒት ይታዘዝለታል:: ትእዛዙን ጠብቆ ተጠንቅቆ መድሃኒቱን ከወሰደ ይድናል:: እኛ የታመመች ሀገራችንን የትኛው ዶክተር ጋ ሄደን ምን መድሀኒት በጥብጠን አጠጥተን እንደምናድናት ግራ የገባ ጊዜ ላይ እንገኛለን፡፡ሁሉም ይህችን ሀገር ለማዳን ዶክተሯ እኔነኝ፣ አውቅላታለሁ እፈውሳታለሁ ባዩ በዛባት፣ "ዶክተር ሲበዛ በሽተኛ ይሞታል" ሆነና ነገሩ የሀገሬ ህመሟ ጸና፡፡ የታመመች ሀገር በሰሞነ ህማማት ካልተፈወሰች መቼ ትፈወስ?

## የሰሙነ ሕማማት ሃይማኖታዊና ትውፊታዊ ክንዋኔዎቹ

1. **አለመሳሳም፡-** በሰሙነ ሕማማት የኦርቶዶክስ ተዋህዶ እምነት ተከታዮች መስቀል እንደማይሳለሙት ሁሉ መጨባበጥ፣ መሳሳምን የትክሻ ሰላምታ መለዋወጥን አይፈጽሙም፡፡ ሰላምታ የማንለዋወጥበት ምክንያት አይሁድ ጌታን ለመስቀል ሰኞ እና ማክሰኞ መከሩ፣ አልስመረላቸውም፡፡ ምክራቸው የተፈጸመው ረቡዕ ነው፡፡ ስለዚህ አይሁድ እያንሾካሾኩ እንስቀለው ፤እንግደለው ብለው ይማከሩ ነበር፡፡ በዘመነ ፍዳ ወቅት ሠላምና ፍቅር አለመኖሩን የሚገልፅልን በመሆኑ ያንን ለማስታወስ ስላምታ አንለዋወጥም፡፡

2. **ሕፅበተ እግር፡-** ጌታ በፍጹም ትህትና የደቀ መዛሙርቱን እግር ያጠበበት፣ ከሐዋርያት ጋር ግብር የገባበትና የክርስትና ህይወት ማሕተም የሆነውን ምስጢረ ቁርባን ያከናወነበት ዕለት ነው ጸሎተ ሐሙስ ሕፅበተ እግር ጌታችን በዚህ እለተ እናንተ ለወንድማችሁ እንዲሁ አድርጎ ለማለት የደቀ መዛሙርቱን አግር በማጠቡ ምክንያት የተሰጠ ምሳሌ ነው፡፡

3. **አክፍሎት፡-** በሰሙነ ሕማማት እለተ ዓርብ ከስግደት በኂላ ምእመናን በየቤታቸው ጥቂት ነገር ለቁመተ ሥጋ ቀምሰው እስከ እሁድ /የትንሳኤ በዓል/ ይሰነብታሉ፡፡ ይህ አክፍሎት ይባላል፡፡ ከዓርብ እስከ ቅዳሜ ሌሊት ለእሁድ አጥቢያ ማክፈል የብዙዎች ነው፡፡ አንዳንዶች ግን ከሐሙስ ጀምረው ያከፍላሉ፡፡ ይህም እመቤታችን ያዕቆብ እና ዩሐንስ የጌታን ትንሳኤ ሳናይ እህል ውኃ አንቀምስም ብለው እስከ ትንሳኤ መቆየታቸውን ተከትሎ የመጣ ትውፊት ነው፡፡

4. **ጉልባን እና ቄጠማ፡-** ጉልባን ከባቄላ ክክ፣ ከስንዴ ወይንም ከተፈተገ ገብስ ጋር አንድ ላይ ተቀቅሎ የሚዘጋጅና የጸሎት ሐመስ እለት የሚበላ ንፍሮ ነው፡፡ የጉልባን ትውፊት እስራኤላውያን ከግብጽ ተሰደው በሚወጡበት ጊዜ በችኮላ ስለነበር አቡክተው ጋግረው መብላት ያለመቻላቸውን ሁኔታ ያመለክታል፡፡ ያን ጊዜ ያልቦካው ሊጥ እያጋገሩ ቂጣ መብላት፣ ንፎሮም ቀቅለው ስንቅ መያዝ ተግባራቸው ነበር፡፡ ይህን ለማሰብ በሰሙነ ሕማማት ቂጣና ጉልባን በማዘጋጀት በዓል ይታሰባል፡፡

5. **ጥብጠባ፡-** በሰሙነ ሕማማት እለተ ዓርብ ስቅለቱ መታሰቢያ ነው፡፡ ምእመናኑ በሰሙነ ሕማማት የሰሩትን ይናዘዛሉ፡፡ ካህናቱን በወይራ ቅጠል ትከሻቸውን እየጠበጠቡ ቀን ከሰገዱት ስግደት በተጨማሪ ሌላ ስግደት ያዟቸዋል፡፡ ጥብጠባው የተግሳፅ ምሳሌ ነው፡፡ ጥብጠባው የሚደረግለት ሰው በህማማቱ ወቅት የፈጸመው በደል ወይም ኃጢአት ካለ ይህንኑ በመናገር የስግደቱ ቁጥር ከፍ እያለ እንዲል ያደርጋል፡፡

6. **ቄጠማ(ቀጤማ)፡-** በቀዳም ስዑር ቀሳውቱን ዲያቆናቱ ቃጭል /ቃለ አዋዲ/ እየመቱ "ገብረ ሰላመ በመስቀሉ ትንሳኤሁ አግሃደ" የሚለውን ያሬዳዊ ዜማ በመዘመር፤ ጌታ በመስቀሉ ሰላምን እንደሰጠ እና ትንሳኤውንም እንደገለጠልን በማብሰር ቄጤማውን ለምእመናን ይሰጣሉ፡፡ ምእመኑም ለቤተክርስቲያን አገልግሎት የሚውል ገጸ በረከት ያቀርባሉ፣ ቀጤማውንም በራሳቸው ያስራሉ፡፡ ይህም አይሁድ ጌታችንን እያሰቃዩ ሊሰቅሉት ባሉ ጊዜ የእሾህ አክሊል ጭንቅላቱ ላይ ያሰሩበትን ድርጊት የሚያስተውስ ነው፡፡ በዚህ እለት ልብሰ ተክህኖ የለበሱ ካህናትና ዲያቆናትን ቄጠማ ተሸክመው፣ ቃጭል ሲቃጭሉ መታየታቸው እለተ ትንሳኤውን ለሚናፍቅ ምእመን ትልቅ ብስራት ነው፡፡

ሰሞነ ህማማቱ ሲፈጸም ትልቁን በአል ትንሳኤውን እናከብራለን፤ ትንሳኤ ማለት "ተንሥአ" ከሚለው የግዕዝ ግሥ የተወረሰ ሲሆን ትርጉሙም መነሣት አነሣሥ ማለት ነው፡፡"ትንሳኤ ማለት መነሳት፡መቆም፡ማለት ነዉ፡፡ እስራኤል ዘስጋ ያከብሩት የነበረው በዓለ ፋሲካ ከባርነት ቀንበር ወደ ነጻነት የተላለፉበት፣ ከኀዘን ወደ ደስታ የተሸጋገሩበት በዓል ነበር ፡፡ የሐዲስ ኪዳን በዓለ ትንሣኤ ግን እሥራኤል ዘነፍስ ወደ ከኃጢአት ጽድቅ የተመለስንበት፣ ከሐሳር ወደ ክብር፣ ከአሮጌው ወደ ሐዲስ ሕይወት የተሸጋገርንበት መንፈሳዊ የነጻነት በዓል ነው ፡፡ፋሲካ በዐረብኛ ፓስኻ ማለት ሲሆን ትርጉሙም "ማዕዶት፣ መሸጋገሪያ" ማለት ነው ፡፡ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሞትና ትንሣኤ በቀደምት ነቢያት የተነገሩና የተጻፉ አንቀጾች ብዙ ናቸው፡፡ የሞቱና የትንሣኤ ምሥጢር በቅዱሳን መጻሕፍት ሰፊ ቦታ ያለው ነው፡፡

ኢየሱስ ክርስቶስ ስለሱ በተጻፈው መሠረት የመስቀልን ፀዋትወ መከራ ተቀብሎ በመስቀል ►

በቀዳም ስዑር ቀሳውስቱን ዲያቆናቱ ቃጭል /ቃለ አዋዲ/ እየመቱ “ገብረ ሰላመ በመስቀሉ ትንሳኤሁ አግሃደ” የሚለውን ያሬዳዊ ዜማ በመዘመር፤ ጌታ በመስቀሉ ሰላምን እንዳሰጠ እና ትንሳኤውንም እንዳገለጠልን በማብሰር ቄጤማውን ለምእመናን ያሰጣሉ። ምእመኑም ለቤተክርስቲያን አገልግሎት የሚውል ገጸ በረከት ያቀርባሉ፣ ቄጤማውንም በራሳቸው ያስራሉ።

ላይ ሞቶ፥ ሞትን ይሽረው ዘንድ ሙታንን በሞቱ ሕያዋን ያደርጋቸው ዘንድ ሞተ። በዕለተ ዓርብ የፈጠረውን አዳም በፈጸመው በደል ከተፈረደበት የሞት ፍርድ ነፃ ይሆን ዘንድ፥ በባሕርዩ ሞት የሌለበት አምላክ በዕለተ ዓርብ በመስቀል ላይ ዋለ። ወዳጆቹ የአርማትያሱ ዮሴፍና፥ አስቀድሞ በሌሊት ወደ ጌታ የሄደው ኒቆዲሞስ በመስቀል ላይ የዋለውን ሥጋውን አውርደው፥ ለመቅበር፤ ከገዥው ከጲላጦስ ለምነው እንዲቀብሩ ተፈቀደላቸው። ከምሽትም ከመስቀሉ አወረዱት፤ እንደቤተ አይሁድ የአቀባበር ሥርዓትና ልማድ የደቀቀና መዓዛው የጣፈጠ ሽቱ አዘጋጅተው፥ ከጥሩ ሐር በተሠራ በፍታ ገንዘው ዮሴፍ ለራሱ አስወቅሮ ባሳነፀው አዲስ መቃብር ቀበሩት። ታላቅ ድንጋይም አገላብጠው ገጠሙት፤ ማቴ 27፥57-58፣ ዮሐ19፥38-42 ይህ ሁሉ ለአይሁድ ሊቃናትና ሕዝብ ደስ የሚያሰኝ አልበረም፡ ፡ ስለጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የሚደረገው ጥንቃቄና የሚሰጠው ክብር ሁሉ፥ በነሱ ዘንድ ተቀባይነት አልነበረውም። “ያ በሕይወተ ሥጋ ሳለ በሦስተኛው ቀን እነሣለሁ ብሏልና ደቀ መዛሙርቱ በሌሊት ሰርቀው፥ ወስደው ከሙታን ተለይቶ ተነሣ ብለው ሕዝቡን እንዳያስቱ መቃብሩ ይጠበቅ” በማለት ወስነው ነበር። በእያንዳንዱ አራት አባል የሚገኝበት በሦስት ፈረቃ የሚጠብቅ የጭፍራ ቡድን ተመድቦ መቃብሩን በንቃትና በጥንቃቄ እንዲጠብቅ ተደርጓል።

ባለሥልጣኖችም ጭፍራው ባለበት መቃብሩን አስቆልፈው በየቀለበታቸው (ማኅተማቸው) አትመውት ነበር። ማቴ 27፥62-66 ይህ ሁሉ በሚፈጸምበት ዕለትና ጊዜ እነ ማርያም መግደላዊት፣ ማርያም ባወፍልያና እና ሰሎሜ ከእግረ መስቀሉ ሳይለዩ ከመቃብሩ ፊት ለፊት ቆመው በኀዘን፣ በተሰበረ መንፈስ የነገሩን ፍጻሜ የሚመለከቱ የዓይን ምስክሮች ነበሩ። ማቴ 27፥61 ይሁን እንጂ ሰውን ለመዳን በፈቃዱ ባደረገው የቸርነት ሥራ፥ በሥጋ ቢሞትም በባሕርዩ ሞት የሌለበትን ጌታ ሞትና መቃብር ይዘው ሊያስቀሩት የማይቻላቸው በመሆኑ፤ ኃጢአትን፣ ሞትንና መቃብርን ደምስሶ፥ መቃብር ክፈቱልኝ፣ መግነዝ ፍቱልኝ፣ ሳይል በሦስተኛው ቀን በሌሊተ እሑድ ከሞት ተነሥቷል። በመቃብሩ ላይ ተገጥሞ የነበረው ታላቅ ድንጋይ ተገለባብጦ የተጠቀለለበት የከፈን ጨርቅ በአፈ መቃብሩ ተቀምጦ ተገኝቷል። የአይሁድ ኀመድ ሁሉ አልነበረም። ለጥበቃ ተመርጠው ልዩ መመሪያና ማስጠንቀቂያ ተሰጥቶአቸው የነበሩ ጭፍሮችም ራሳቸውን እንኳ መጠበቅ ተስኗአቸው በያሉበት ወድቀው እንደ በድን ሆነው ነበር።

ትንሣኤውን ለማየት ወደ መቃብሩ ሲመላለሱ ያነጉት ቅዱሳት አንስት ከሞት የተነሣውን ክርስቶስን ለማየት ቀዳሚ ዕድል ነበራቸው። አስቀድማ ለማየት የበቃችው ማርያም መግደላዊት መሆኗን ቅዱስ ወንጌል አስቀምጦታል፡ ፡ ከሷ በማስከተል፥ ሁሉም ሴቶች አይተዋል፡ ፡ ጌታችን በተነሣ ጊዜ፥ መልአኩ እንደ ፀሐይ በሚያበራ ልብስ፣ እንደ በረዶ በነጣ ግርማ፣ ርእየቱ በሚያስፈራ ሁኔታ ተገልጦ ነበር፡ ፡ ሴቶቹንም“አይዞአችሁ አትፍሩ የተሰቀለውን ኢየሱስን እንድትሹ ዐውቃለሁ፤ እሱ ከዚህ የለም እነሣለሁ እንዳለ ተነሥቷል። ነገር ግን ኑ የተቀበረበትን ቦታ እዩ ካያችሁም በኋላ ፈጥናችሁ ሄዳችሁ ከሙታን ተለይቶ እንደተነሣ ለደቀ መዛሙርቱ ንገሩአቸው፤ በገሊላ ይቀድማችኋል (መታየትን ይጀምርላችኋል) በገሊላ ታዩታላችሁ” ብሎአቸው፥ ወደመቃብሩ እየመራ ወሰዳቸው።

ሴቶችም ፍርሃትና ድንጋጤ በተቀላቀለበት የደስታ መንፈስ ተውጠው ወደ መቃብሩ ሄዱ፡ ፡ ፍርሃት የእግዚአብሔርን መልአክ ማየታቸው፤ ደስታው ደግሞ፥ ትንሣኤውን መስማታቸው ነው። በደስታ ተሞልተው ዜናውን ለደቀ መዛሙርቱ ነግረው፥ እየተቻኮሉ ሲሄዱ ጌታችንን በመንገድ ተገለጠላቸው። “እንዴት ሰነበታችሁ! አስታረቅኋችሁ” አላቸው። ቀርበውም ሰገዱለት፤ እሱም አይዞአችሁ አትፍሩ፤ ሂዱ ለወንድሞቻችሁ ገሊላ ይሄዱ ዘንድ ንገሩአቸው በዚያ ያዩኛል” አላቸው። ዐሥራ አንዱ ሐዋርያትም ዜናውን ሰምተው ወደተባሉበት ቦታ ወደ ገሊላ ሄዱ፡ ፡ በዚያም ጌታችንን ከሙታን ተነሥቶ አዩት፤ ሰገዱለትም። ለፍቅሩ ይሳሱ፥ ይናደዱ የነበሩ ጴጥሮስና ዮሐንስም በጊዜው ወደ መቃብሩ ሄደው መነሣቱን አረጋገጡ። ዮሐ20፥1-11 የክርስቶስ ትንሣኤ በስሙ ላመኑ ክርስቲያኖች ሁሉ ትንሣኤ ነው። ክርስቶስ ለሙታን ሁሉ በኩር ሆኖ ተነሥቶአል። የሙታንን ሁሉ መነሣት የሚያረጋግጥልን የጌታ ትንሣኤ ነው።

የክርስቶስም ትንሣኤ መርገመ ሥጋ፥ መርገመ ነፍስ፤ ሞተ ሥጋ፥ ሞተ ነፍስ የተሻረበት ርደተ ገሃነም ጠፍቶ፥ በአዳም የተፈረደው ፍርድ ሁሉ ተደምስሶ፤ ፍጹም ነፃነት፣ የማይለወጥ ደስታ፣ የተገኘበት ስለሆነ ፋሲካ ይባላል፡ ፡ ፋሲካ ደስታ ነው፤ እስራኤል ከግብጽ ባርነት ነፃ የወጡበትን ቀን ፋሲካ ብለውታል። የእርቅ፣ የሰላም፣ የድኅነት ቀን ነው። ከሞት ከመነሣት፣ ከመቃብር ጨለማ ከመውጣት፣ ከዲያብሎስ ቁራኝነት ከመላቀቅ፥ ከሲኦል እስራት ከመፈታት የሚበልጥ ምን ደስታ ሊኖር ይችላል? የክርስቶስ ትንሣኤ እግዚአብሔር እኛን ምን ያህል እንደ ወደደን የምናስተውልበት፣ የፍቅሩን ጥልቀት፤ የቸርነቱን ስፋት የምናደንቅበት፤ የነፍሳችን የዕረፍት ቀን ነው።


በሰው ዘንድ በቃል ሲነገር፣ በተግባር ሲፈጸም የሚታየው ፍቅር ዘመድ ወዳጅ የሚለይበት ሰው ከሰው የሚዳላበት፤ ባለ ካባ ከባለ ካባ፣ ባለዳባ ከባለዳባ የሚበልጥበት፤ የሚወደውን የሚወዱበት፤ የሚጠላውን የሚጠሉበት ነው። ለሚጠሉት ይቅርና ለሚወዱት ተላልፎ የሚሞቱበት ፍጹም ፍቅር በዓለማችን አይታይም። መድኃኔዓለም ክርስቶስ እኛን የወደደበት ሕይወቱን እስከ መስጠት ደርሶ ቤዛ የሆነበትን ምሥጢር የሰው ሕሊና መርምሮ ሊደርስበት የሚችል አይደለም። ተነጻጻሪ ተወዳዳሪ አቻ ምስያ የሌለው ልዩ ነው፡ ፡ ከቀደምት አበው እነ አብርሃም ልጆቻቸውን በቁርጥ ሕሊና ለመሥዋዕት አቅርበዋል። እነ ሙሴ እነ ዳዊት ይመሩት ይጠብቁት ለነበረው ሕዝብ “ተላልፈን እንሙት፣ እንቀጣ፣ የሕዝቡን ቅጣት እንቀበል” ብለው እንደነበረ ተጽፎአል። ግን በቅርብ ለነበረ፣እንዲያስተዳድሩ ለተሾሙለት ለተወሰነ ሕዝብና ለወገናቸው ብቻ ነበር። ሁሉን የሚያጠቃልል ሁሉን የሚያድን አልነበረም። መድኃኒታችንን አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስ ግን በመስቀል ላይ መከራ ተቀብሎ የሞተው፥ ለመላው የሰው ዘር ለአዳም ልጆች ሁሉ ነው። ቤተሰብና ዘመድ ወዳጅና ጠላት ወንዝና አካባቢ የሚለው አልነበረም። ከሰው አስተሳሰብ ሚዛንና ግምት የራቀ የጠለቀ ነው። የወደደን፣ መከራ የተቀበለው እኛ ስለወደድነው አልነበረም። እሱ ስለ ወደደን ብቻ ነው።

እንኪንስ ቀድሞ ዛሬም ያደረገልንንና ያደለንን አስበን፥ ፍቅሩን ተገንዝበን፥ ለሰው በጎ ማድረግ፤ በፍቅሩ መመላለስ እጅግ ያዳግተናል። ከሁሉም የሚረቀውና የሚደንቀው ያጠፋን፣ የበደልን፣ በጥፋታችን ሞትን በራሳችን ላይ ያመጣን እኛ ስንሆን፥ እሱ ስለኛ በደል ተላልፎ በእኛ የተፈረደውን የሞት ፍርድ ተቀብሎ መሞቱ ይደነቃል። ለዚህም አንክሮ ይገባል።ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ “ርእዩ መጠነ ዘአፍቀረነ እግዚአብ ሔር ... ወሶበ እንዘ ፀሩ ንሕነ ተሣሃለነ በሞተ ወልዱ እግዚአብሔር ምን ያህል እንደወደደን አስተውሉ፤ ጠላቶቹ ስንሆን በልጁ ሞት ይቅር አለን ” ብሎ እንዳስተማረው ስንኳን ተላልፎ እስከ መሞት የሚያደርስ ፍቅርና ከፍርድ የሚያድን ምንም መልካም ሥራ ሳይኖረን፤ በሱ ፍቅር የተደረገልንን ቸርነት የምናስብበት የነፃነት የምስጋና ዕለት ነው።

ሮሜ 5፥6- 10 በልጁ ሞት ስለካሰልን ይቅርታን አገኘን፤ በአንድ አዳም በደል ምክንያት ኃጢኣት ወደ ዓለም እንደ መጣች፤ በዚችም ኃጢኣት ምክንያት፥ በሰው ሁሉ ሞት እንደተፈረደበት፤ ሰውን ሁሉ በደለኛ፣ ኃጢአተኛ፣ አሰኝቸው። በአዳም ኃጢአት ምክንያት የመጣ ሞት ከአዳም እስከ ክርስቶስ የነበሩትን የበደሉትንና ያልበደሉትን ሁሉ ገዛቸው። ታላቁ ሙሴ እንኳን ሌላውን ሲያድን ራሳቸውንም ከሞት ማዳን ስላልተቻላቸው ለሞት ተገዝተዋል። ነገር ግን የእግዚአብሔር የጸጋው ስጦታ በኃጢአታችን ልክ የተደረገብን አይደለም፡ ፡ ራሱን ቤዛ አድርጎ ካሰልን፤ ከዳግማዊ አዳም ኢየሱስ ክርስቶስ በተሰጠን ጸጋ በጥምቀት፣ በሃብት፣ በልጅነት ለሰው ሁሉ ሕይወት በዛለት፡ ፡ሮሜ5፥16-18 የተነሣውን ክርስቶስን ሐዋርያት አይተውታል ገጽ በገጽ ዓይን በዓይን ፊት ለፊት ተያይተዋል። ሰግደውለታል፤ አመስግነውታል፤ ደስታቸው ፍጹም ሆኖላቸዋል።

መላ የኢትዮጵያ ህዝብ ትንሳኤውን ስናከብር በሚበላና በሚጠጣ ብቻ ሳይሆን የትንሳኤውን ትርጉም በመረዳት ሊሆን ይገባል። ትንሳኤ መነሳት ስለሆነ ኢትዮጵያውያን ከወደቅንበት እንነሳ፤ ከእራስ ወዳድነት፣ ከግለኝነት፣ ከዘረኝነት፣ ከኀጠኝነት እንነሳ። የትንሳኤው ትርጉም ትንሳኤ ለሚያስፈልጋት ሀገር ወሳኝ ነው። ሀገር በመቃብር ውስጥ እንደአላዛር በጨለማ ውስጥ ተውጣለች ከመቃብር የሚያስወጣትን የጥሪ ድምጽ እንደአላዛር እየጠበቀች ነው። የሀይማኖት አባቶች በፓላሳቸው በተዘጋ መቃብር ውስጥ ላይናገሩ አፋቸው ተዘግቷል አፋቸውን የዘጋው ሰይጣን ይሁን ወይ መንግስት ይሁን አይታወቅም፡ ፡ ብቻ ሀገራችን ትንሳኤ ያስፈልጋታል። ወገኔ ተነስ ከመለያየት ሀሳብ፣ ከዘረኝነት፣ ከቋንቋ አምላኪነት፣ ከተራራና ወንዝ ቆጣሪነት፣ ተነስ ተነስ ገጀራህን ጥለህ፣ ተነስ መሳሪያህን ጥለህ፣ ተነስ የጥሉን መቃብር ደርምሰው፣ መገዳደል ይብቃ። የትንሳኤውን መብራት እናብራ፣ የፍቅር ብርሀን፣ የአንድነት ብርሀን ይብራ። ጨለማው እርሀብ ይወገድ፣ ጨለማው ወንድሙ ወንድሙን መግደል ይቁም። ስለዚህ ተነስ ተነስ ተነስ.... የትንሳኤው ትርጉም ትንሳኤ ለሚያስፈልጋት ሀገር ለኢትዮጵያ ይሁንላት።

**እንኳን ለብርሃነ ትንሣኤው አደረሰን አደረሳችሁ አሜን።**



“ሰላምና መረጋጋት የጠፋው ከብሄር አክራሪነት የተነሳ ነው:: ፅንፍ የወጣ ብሄርተኝነት ያመጣው ችግር ነው:: የብሄርተኝነት ውጤት ነው አሁን እየተመለከትን ያለነው:: ለዚህ ደግሞ ዋነኛው ተጠያቂ ሕወሓት ነው:: ሌላ ማንም አይደለም”

### አቶ አብርሃ ደስታ የአረና ፓርቲ ሊ/መንበር

አዲስ አድማስ ጋዜጣ ሚያዚያ 12 ቀን 2011 ዓ.ም



“ብዙውን ጊዜ ለውጡን ያመጡት ጠቅላይ ሚኒስትሩና ከጠቅላይ ሚኒስትሩ ጋር ያሉ ሰዎች ናቸው እያልን እንናገራለን:: ይህንን ማለታችን እውነትም፣ መልካምም ነው:: ግን ደግሞ ህዝብ ባይደግፍ ኖሮ ይህንን ለውጥ ማምጣት እንደማንችል ማሰብ ይገባናል:: ለህዝብም እውቅና መስጠት አለብን:: ብዙውን ጊዜ “ህዝቡ እኮ አይገባውም፤ ለውጡን አይቀለበውም” እያልን ህዝቡ ላይ ትችት እንሰነዝራለን:: ግን ህዝብ ባይደግፈው ኖሮ ይሄ ለውጥ አይንቀሳቀስም ነበር:: ልክ ቤተክርስቲያን ወይም መስጂድ ሄደን የሃይማኖት አባቱ ምዕመኑ ካልተቀበለው ሊቀጥል እንደማይችል ሁሉ መንግስትም ለህዝቡ ተገቢውን እውቅና ካልሰጠ ተቀባይነቱን ማጣቱ አይቀሬ ነው”

### ረ/ፕ ምህረቱ ሻንቆ

አዲስ ዘመን ጋዜጣ ሚያዚያ 12 ቀን 2011 ዓ.ም



“እንደ ቦርዱ ፍላጎት ከሆነ በፍጥነት እንዲፀድቅ ነው የምንፈልገው:: ነገር ግን ደግሞ በ”ጊዜ የለም” ምክንያት ብቻ በተዋከበ ሁኔታ የማይሆን ህግ እንዲወጣ ደግሞ አንፈልግም:: ምክንያቱም የተሻለ ህግ ካልሆነ ነገም ተመልሶ የዴሞክራሲውን ሂደት የሚያስተጓጉል ይሆናል:: ስለዚህ የተወያያንበትና ግብዓት የጨመርንበት ህግ እንዲሆን ይፈለጋል:: የጊዜ ፈተና አለብን፤ በአንድ በኩል ደግሞ ህጉ የተሻለ ሆኖ ሁሉንም ያማከለ እንዲሆን ደግሞ እንፈልጋለን:: ይህ ደግሞ ጊዜ ይወስዳል:: እንዲያም ሆኖ ግን ሪፎርም ባልተደረገ ተቋምና ህግ ውጤት ማምጣት አይቻልም:: ስለዚህ ተስፋ የምናደርገው ከፖለቲካ ፓርቲዎች የሚገኘውን ግብዓት ከወሰድን በኋላ ፈጥነን ለመሄድ እንሞክራለን እንጂ በዚህ ጊዜ ውስጥ ይጠናቀቃል የምንልበት ነገር የለም::”

### ወ/ት ሶሊያና ሽመልስ የምርጫ ቦርድ ኮሙኒኬሽን አማካሪ

አዲስ ዘመን ጋዜጣ ሚያዚያ 15 ቀን 2011 ዓ.ም



“በሌላ በኩል ደግሞ ይሄ ኅብረተሰብ ለረዥም ጊዜ የታፈነ ነበር:: ነፃነት ያልነበረው ሕዝብ ነፃነት ሲያገኝ ደግሞ የነፃነት ድንበሩን በቀላሉ የሚለየው አልነበረም:: በመሆኑም ሲለቀቅ የፈላው ቀስ እያለ መስከኑ የማይቀር ነበር:: ለዚያ ነው እጅግ ትዕግስት አድርገን ለመጠበቅ የወሰነው፤ በአዲስ አበባም ተመሳሳይ ሂደት ነው የተከተልነው:: በኦሮሚያ አካባቢ የተለየ ትዕግስት ነው ለማሳየት የሞከርነው:: በእርግጥ ያለው መንግስት የኢትዮጵያ መንግስት ነው:: የላይኛው ሰውዬ ኦሮሞ በመሆኑ ብቻ የኦሮሞ መንግስት እየተባለ ነው:: እውነቱ ግን ያ አይደለም:: ኅብረተሰቡ በበኩሉ መንግስት ህግ ማስከበር አለበት እያለ ነው:: ስለዚህ ከልክ ሲታለፍ መንግስት የዜጎችን ደህንነት ለአደጋ ማጋለጥ ስለሌለበት እርምጃ ይወስዳል:: ነገር ግን የሽግግር ወቅት እንደመሆኑ መጠን እና ህግ ደግሞ መከበር ስላለበት ሚዛኑን ሳንስት ነው እየተጓዝን ያለነው”

### ታዬ ደንደአ የኦዴፓ የህዝብ ግንኙነት ሀላፊ

ቦሌ ታይምስ ጋዜጣ ሚያዚያ 12 ቀን 2011 ዓ.ም

# ስጠቅላላ እውቀት

- ሕልም በምናልምበትና ዓይኖቻችን በርካታ ትንንሽ እንቅስቃሴዎችን የሚያደርጉበት ጭልጥ ያለ እንቅልፍ (Rapid Eyes Movements - REM sleep) የሚወስደን በአብዛኛው ከተኛን ከ90 ደቂቃዎች በኋላ ሲሆን በአንድ ሌሊት ውስጥ በአጠቃላይ ለሁለት ሰዓታት ያህል ይወስደናል።

- ዓይናችን እንዲርገበገብ የሚያደርገው ጡንቻ ከሰውነት ክፍላችን ጡንቻዎች ፈጣኑ ነው። በሰከንድ 5 ጊዜ ያህል የሚርገበገብ ሲሆን በአማካይ በቀን 15,000 ጊዜ ዓይናችንን ያርገበግባል። ሴቶች ከወንዶች በሁለት እጥፍ ፍጥነት አይናቸው ይርገበገባል።

- ፍላሚንጎ የምትባለው ወፍ ምግቧን መመገብ የምትችለው ጭንቅላቷን ወደ ላይ አንስታ ወደ ታች በመመለስ ነው።

- ሊዎናርዶ ዳቬንቺ ወደኋላም ወደ ፊትም በሁለቱም አቅጣጫ መፃፍ (dyslexic) ይችል ነበር።

- ጉንዳን እንቅልፍ የሚባል ነገር የማያውቅ ሲሆን ውሃ ውስጥ ሰጥሞ እስከ ሁለት ቀን ድረስ በህይወት መቆየት ይችላል።

- ቢራቢሮ የሰውነቷ ሙቀት ከ86 ዲግሪ ሴንቲግሬድ በታች ካልሆነ በፍፁም መብረር አትችልም።

- የባቄላ ዘር ከሰው ልጅ ሴሎች የበለጠ በእያንዳንዱ ሴል የበለጠ ዲኤንኤ አለው።

---

# ኀግግሮቹ

- የደንቆሮው ድንቁርናው ብልህ ለመሆን ሲሞክር ይገለፃል።

  ሀዲስ አለማየሁ

- ጥበብ ወደ አንተ የሚፈሰው ቀና ሆነህ ስታገለግለው ነው። ጥበብ የራሱ ፈቃድ አለውና

  አበበ ብርሃኔ

- ዘመን የአህያ ጀርባ ነው በራሱ የሚለውጠው አንዳች ነገር የለውም።

  የሺጥላ ኮከብ

- ሰውን መግደል በጣም ቀላል አልያም በጣም ከባድ ለመሆኑ ማረጋገጫ አያስፈልገውም።

  አለማየሁ ታደሰ

- በመከራና በችግር እርሾ ያልተቦካ ህይወት ወደዚህ ዓለም አምጥተው በኑሮ ምጣድ ላይ ሲጋግሩት ሁሌ አፍለኛ ይሆናል።

  ደበበ እሸቱ

- ጊዜ የማያመጣውን ጊዜ እስኪያመጣው ትጠብቃለህ እንጂ ጊዜን ልታጣድፈው አይቻልም።

  ስብሃት ገ/እግዚአብሔር

# ስምኀ ብዬ ሌባ

የሰው ልጅ ሀጢያቱ ሰንኮፉ እንዲነቀል
በቀራንዮ ላይ በሌቦቹ መሀል
ጌታችን ሲሰቀል የሾህ አክሊል ደፍቶ
ስለእኔ ሊሰዋ በደሙ ሊያፀድቀኝ
ሲኦልና ገነት ቆመው አየኋቸው በግራና በቀኝ።
በግራው መስቀል ላይ ርቃኑን ተሰቅሎ

# ህዝብ ከህዝብ?

## የቱ ጋር ነን? !



ፍቅርተ ተሾመ

በምጣኔ ሃብት፣ በማህበረሰብ ንቃት፣ በትምህርት ተደራሽነት፣ በኑሮ ደረጃ፣ በሞት እና ወሊድ ቅነሳ (ለማን ተብሎ እንደሚቀነስ ባይታወቅም) ፣በህዝብ ብዛት ማመጣጠን… በዚህ ሁሉ 'countries that are under development' እድገትን ተጭነው ያስቀሩ ሀገራት ናችሁ እየተባልን ነው። እውነት ነን? እንዴት?

### ታሪካዊ መንደርደሪያ

በቅድሚያ እነርሱ እንዴት አድገው እኛን እድገትን የተጫኑ ይሉናል? በአውሮፓ የኢንደስቱሪዎች መስፋፋት  እና የግለሰቦች ሃብት ማካበት ለአብዛኛው ህዝብ ጉልበት መበዝበዝ ምክንያት ሆነ። በዚህም ምክንያት ተበዝባገፉ መብቱን የሚያስከብርበት የካፒታሊዝም- ኮሚኒዝም እንቅስቃሴ ጥርሱን አግጥጦ ሲመጣ ብቸኛው ማምለጫ መንገድ የቅኝ ግዛት ሆኖ ብቅ አለ። እናም የአፍሪካን ሃብት፣ የሰው ሃይል እና ጥበብ ተራ ከሆነው እስከ ተወሳሰበው ድረስ ከ100 አመታት በላይ በመበዝበዝ እና በመስረቅ የራሳቸው ህዝብ ሊያነሳ ከነበረው የመደብ ጥያቄ ማምለጥ ቻሉ። ይህ ብቻም ሳይሆን ያልጠየቁትን ጭምር ቃል ገቡ፤ ሰጡም። አፍሪካ እንደ አህጉር የነበራትን ሉዓላዊነት፣ የህዝቦቿ የሰውነት ክብር ፣ የቀደመ ታሪኳን መዝገብ ሁሉ በመፋቅ በአዲስ ቅርፅ አርቴፊሻል ታሪክ እና ማንነት ሰጥተውም ሄዱ። ይሄ እውነት ነው።

ቀድሞ አንድ ክፍለ ዘመን ሙሉ በአፍሪካ ላይ የሰሩት፤ የእነርሱን የበላይነት የመቀበል ዝንባሌ እስከ አሁንም ነግሶ ይገኛል።  አሁን ደግሞ መልኩን ቀይሮ ስልጣኔ ሆኗል።

### ስልጣኔ

ስልጣኔ (Modernization) ቲዎሪ ሲሆን፤ ለምን የድሃ ድሃ ሀገራት ማደግ አልቻሉም? ለሚለው ከኮሚኒዝም አካሄድ የራቀ እና ካፒታሊዝምን የተከተለ የምጣኔ ሃብት ለውጥን ይመክራል። ለዚህ ደግሞ ምዕራባዊ ባህል እና እሴትን ማስተዋወቅ ትልቅ ሚና እንዳለው ይገልፃል።በዋናነት የሚያጠነጥነውም ወገኛ የሆኑ ማህበረሰቦችን ከእድገት የሚገታው ባህላዊ እና ኢኮኖሚያዊ መሰናክሎች ናቸው ብሎ ይደመድማል። ቀድሞ ነገር ለኃላ ቀርነታቸው ተጠያቂ እራሳቸው ናቸው ይልና። በሌላ ጎን  ምዕራባዊው ባህል ለእድገቱ ምክንያት መሆኑን በመጠቆም የበላይ መሆኑን ያስቀምጣል።

አሁን ጥያቄው እኛ በዚህ አዙሪት ውስጥ ሰጥመን መገኘታችን መቼ እና እንዴት ሆነ? የሚለው ነው። ይህ ጉዳይ ጥናት የሚያሻው ሰፊ ርዕሰ ጉዳይ መሆኑ አያጠያይቅም። ሆኖም ከአንዲት ተፅዕኖ ፈጣሪ ለውጥ ላይ ማተኮር ግን አስፈላጊ ነው:: ዘመናዊ ትምህርት በኢትዮጵያ በንጉሡ ጊዜ ከተጀመረ አንስቶ አግባብ ያለው ትምህርት የቀሰሙት የየትኛው ዘመን ተማሪዎች ናቸው? ብሎ መጠየቅ ያስገድዳል። አመፅ እና የትምህርት ጥራት እየተፈራረቁ አልያም በጋራ፤ ትውልድን በየጊዜው መበደሉ አመፅን ከጀመሩት ከንጉሡ ተማሪዎች ወዲህ ያለ እረፍት የታየ የትውልድ ቅሸባ ነው ብሎ በድፍረት መናገር ይቻላል።

ከዚህ ባሻገር ትምህርት በሌላው አለም የስራ እና የእድገት ምንጭ ነው። ታዲያ እኛ ጋር ሲመጣ ለምን የምንጠፋበት ሆነ? አፍሪካ በታሪኳ ከግዞት በፊት የዘውግ (የብሔር) ግጭት መታወቂያዋ እንዳልነበረ ታሪክ ያሳይል። ሆኖም የዘውግ እና የድንበር ግጭት ከክፍለ ዘመን ግዞት በኃላ አጨራራሽ ጉዳይ ሆኗል።

### ዘውገኝነት

ዘውገኝነት የተለያዩ ደረጃዎች አሉት። አንደኛው Objectivist የሚባለው ሲሆን ዘውገኝነት (ብሔርተኝነት) ቋሚ እና የማይቀየር እንደሆነ ያምናል፡፡ ስለሆነም ለፖለቲካዊ አመፅ ማነሳሻነት ዘውገኝነት መሰረት ነው ይለናል፡፡ የዚህ ሀሳብ አቀንቃኞች ምዕራባዊያን ተመራማሪዎች ሲሆኑ፤ የዘውግ መሰረትነት ወይም መለያነት ላይ የጥናቱን ትኩረት አድርጎ በመሃከላቸው ያለውን ውድድር እና መስተጋብር ይተነትናል።

ምናልባት በዘውግ ግጭት ምሳሌ ተደርጎ የሚነሳው የሩዋንዳው ግጭት ይሆናል። ግን ሀቁ ያ አይደለም ። ሩዋንዳ ሁለት መደቦች አሉዋት፤ እነርሱም "ሁቱ" የሚባሉት አርሶአደሮች እና "ቱትሲ" የሚባሉት ዘላን ማህበረሰቦች ናቸው። ግጭቱ በአኗኗራቸው ምክንያት የመጣን የሃብት እና የስልጣን ሚዛን አለመመጣጠን ምክንያት ያደረገው የበላይነት ጥያቄ ነው።

ለዘውገኝነት ግን ማሳያ የሚሆነው የኢህአዴግ ስርዓት ነው። ለምሳሌ ባለፈው ሳምንት ውስጥ የኦሮ አማራ የህዝብ ለህዝብ ግንኙነት ጉዳዩን ለማግለብለቢያ ሁነኛ መንገድ ነው። የዘውገኝነት ፅንሰ ሃሳብ - ልዩነትን ማስፋፋት፤ በልዩነት መወዳደርን ማጉላት ዋነኛ አላማ ያደረገ ነው። በመሆኑም አሁን የዚህ አቀንቃኝ 'ምሁራኖቻችን' አልያ ጊዜያዊ መሪዎቻችን፤ ባለን ልዩነት እንወዳደር፣ ተወዳድረን እናሸንፍ የሚሉ ናቸው። ምናልባት የሚጠቀሙት የባንዲራ ይከበርልኝ፣ ድህነት ህዝቤን ወረሰው፣ ተገደልን፣ ተዘረፍን ይሆናል፤ ቲዎሪው ግን ይላችኋል - ይሄ ሽፋን ነው። እነርሱን የዘውገኝነት "ስራ ፈጣሪዎች፤ ስራውም የዘውጋዊ ፖለቲካ" ነው ይለዋል። እናም ልዩነት ሲወራ ልዩነት ይነግሳል፤ አንድነት ሲወራ አንድነት ይነግሳል፡፡ አንድ ነን ስንል ከቅኝ ገዢዎች የአስተሳሰብ ወረራ በፊት ድንበርን በቋንቋ እና በባህል ልዩነት ከመከፈሉ በፊት የነበርነው ህዝብ ነን። ይህ ሊነገር የሚገባው፣ ግን ለህዝብ ሳይሆን ለአግለብላቢዎቹ መሆን እንደሚገባው ለጠ/ሚሩ ማን በነገራቸው? ህዝቡን በተለያዩ ምክንያቶች የተቆጣጠሩት ግለሰቦች እና ቡድኖች ሀገሪቷ እስካሁን ስትገብር የኖረችውን ወጣቶች አሁንም እየቋመጡበት ነው።

ይህን የስራ መስክ ከመነሻው እስከ መድረሻ ጥጉ ባሉት ደረጃዎች የሚይዛቸው ቅርፆች አሉ። በቅድሚያ ራሳቸውን በመደበኛም ይሁን በኢመደበኛ መልኩ ለህዝቡ ቆመናል የሚሉ በ 'ተወከለው' ህዝብ እና በመንግስት መሃል አደራዳሪ ሆነው ይመጣሉ። ከዛስ? ሊነሱ የሚችሉ ጥያቄዎችን ያበጃጃሉ፡፡ እያሉ በአንድ ሃገር ውስጥ ሳሉ ራሳቸውን ወደ ማደራጀት በመሄድ የቡድን መልክ ይዘው ይመጣሉ። ከዚያ እዳው ገብስ ነው፤ የዘውግ ፖለቲካዊ እንቅስቃሴዎች በፓርቲ ደረጃ መቀንቀን ይጀምራል።

በዚህ ሃገር እንዲህ አይነት ሁነኛ የፖለቲካ ስልጣን መነቅነቂያ ሃሳቦች ሲፈልቁ ለመተግበር ቀላል ይመስላል። ማርክሲዝም - ችግር የለም ይተገበራል፤ ዘውገኝነት - ችግር የለም እውን ይሆናል። ዘመናዊነት - እንዴ ምን ማለታችሁ ነው? እና ሳናድግ እንቅር? በሚል ከ100 ዓመታት በላይ ባርነት ያላጠረቃቸው፣ አሁንም ከዚህ በኃላ መነሳታችን የሚያሰጋቸው ምዕራባዊያን ስራ ይሰጡናል እናቀላጥፈዋለን።

ዘመኑ በንቃት ቀድሞ የመገኘት የራስን ማንነት ከመጣው የሉአላዊነት ማዕቀፍ ውስጥ አንጥሮ የማውጣት አልያም ታግሎ የማስቀረት አርበኝነትን የሚጠይቅበት ጊዜ ነው። ሚድያውም የማህበራዊ ዱር አርበኞችን እና የልዩነት አቀንቃኞችን ወደፊት ከማምጣት ይልቅ የሉአላዊነት ማሸነፊያ እቅድ የያዙ፣ ማንነትን ለሚበርዙ ሃሳቦች ማርከሻን ያነገቡ ፣ደግሞም ዘመናዊነት የሚሹ ያለማደጋችን ምክንያት እኛው ነን ብለው ለሚቀበሉ የሚያመጡትን ቅያሶች ማስተናገድ እና መምረጡን ታዝበናል።

### ዴሞክራሲ

ለራሱ የሚጨነቅ ህዝብ ከራሱ መንግስት በላይ ጠንክሮ መገኘት አለበት የሚል አባባል አለ። ይህ ካልሆነ ግን መንግስት በህዝብ ላለመራቱ ዋስትና የለም። ይህ ከሆነ ደግሞ ዴሞክራሲ የለም። በዴሞክራሲ ነፃነት - (ግዴታን የሚጨምረውን ማለት ነው) ለማግኘት ህዝብ ዴሞክራት ሆኖ መገኘት አለበት። የኔን ቋንቋ ካልተናገርክ የሚል ወንድም ሲነሳ የራስን ቋንቋ በማያጠፋ መልኩ መንገድ ለመቀየስ መነሳት አስፈላጊ ነው። ዴሞክራሲ የሃሳብ ነፃነትን ይፈቅዳላ!  ዴሞክራሲ አቀንቃኝ እና ሰባኪዋን ሶቅራጥስን የገደለች መሆኗን ማወቅ አስፈላጊ ነው። ብሶት አዝሎ የቆየ፣ ባገኘው አጋጣሚ የተነፈሰ፣ ሁሉም በዴሞክራሲ ህዘብ ነው መድሎ አይደረግበትም፡፡ በአንድ ዴሞክራሲያዊ ስርዓት ውስጥ መንግስት ሚናው ግልጽ ነው፤ በህዝቦች መካከል የያዙትን ማስቀጠል አዲስ ፍላጎት ሲኖር ለውይይት ማመቻቸት አለቀ። መንግስት ከዚህ ባለፈ እንዲህ አድርግልን ተብሎ ሊጠየቅ አይገባውም ፤ እርሱም እንዲህ አደረኩላችሁ ሊል አይገባውም።



# <<አንተ ጎዳና አንተ መንገድ፤ ሰው እንዳይሄድ፤ ዋ! ሰው እንዳይሄድ!>>

በኃይሉ ገ/እግዚአብሔር

‹‹አንተ ጎዳና አንተ መንገድ፤
ሰው እንዳይሄድ፤ ዋ! ሰው እንዳይሄድ!››

‹‹እንደጀመርን እንጨርሰዋለን!›› ያልነው ጾም እንሆ ተንከባሎ ተንከባሎ እዚህ ደርሷል፤ ሰሙነ ሕማማቱ ላይ፡፡ …እንኳን አደረሳችሁ! …ለእግዚሃር ከቀረቡ አይቀር እንዲህ ነው፤ እንዲህ እንዳኹት ሰሙነ ሕማማት ላይ ብቻ ሳይሆን፣ ዓመቱን ሙሉ በገና ሲጫወቱ መሰንበት፤ በደቦ ኾኖ፣ ‹‹ሰው እንዳይሄድ፤ ሰው እንዳይሄድ!›› ሲሉ መክረም፡፡ በገና ከመጫወት በላይ ልብን ደስ የሚያሰኝ ምን ነገር አለ? ምንም!
‹‹ጎዳና፤ …መንገድ፤
ሰው እንዳይሄድ፤ ሰው እንዳይሄድ!››

እንቅፋት አይጠፋም አይደል!? ይኸን ስብርብር ያለ እንጉርጉሯችንን የሰማ አጠገባችን ያለ አንድ ወዳጃችን እንዲኽ አለን፤
‹‹ምንድን ነው ሰው እንዳይሄድ፤ ሰው እንዳይሄድ? …ብላችኹ ብላችኹ በመዝሙር ስም አድማ መጥራት ጀመራችኹ!?››
አይ እድላችን፤ ክፉ ሰው እያለ በየት በኩል ከእግዚሃር ጋር መገናኘት ይቻላል!? ኧረ በየት በኩል!? ግራው ገባን እኮ ጎበዝ! ማን ነበር፤ ‹‹የኢትዮጵያውያን ፊኛ ነፃነት መሸከም አይችልም!›› ያለው!? (ይኼኔ፣ ‹ይኽቺን ጥቅስ ለምን ጠቀሰ?› ባይ ነገረኛ፣ ‹‹ነፃነት የምንሸከመው ደግሞ በፊኛችን ነው እንዴ!?›› ብሎ ይጠይቀኝ ይኾናል፤ ጌታዬ! ያንተን አላውቅም፤ እኔ ግን እንደ አብዛኛው ሰው ነፃነቴ ትዝ የሚለኝ ፊኛዬ ሲሞላ ብቻ ነው፡፡ …ጨረስኩ፡፡)
…ለመሆኑ ግን ፖለቲካ ምንድን ነው? …ለሚከተለው ጥያቄ ትክክለኛውን መልስ ምረጥ፤ ‹‹ፖለቲካ ምንድን ነው?››
ሸ. መብትህን ለማስከበር የሌሎችን መብት የምትደፈጥጥበት መድረክ ነው፤
ቀ. ክፍት የሥራ ቦታ ነው፤
በ. በሕዝብ ዘንድ ታዋቂ የመኾኛ አቋራጭ መንገድ ነው፤
ተ. ያለብዙ ድካም ወይም በአቋራጭ የምትበለፅግበት ተቋም ነው፤
ቸ. ደስ የሚል እና ፈታ የሚባልበት በሕዝብ ሰቆቃና ደም የምትጫወትበት ሥፍራ ነው፤
ኀ. ሸ ቀ በ መልስ ነው፡፡
ነ. ተ ቸ መልስ ነው፡፡
ኘ. ሸ ቀ በ እና ተ ቸ መልስ ነው፡፡
አ. ሸ በ ተ እና ተ ቸ መልስ ነው፡፡
ከ. ይኽንን ጥያቄ መጠየቅ ራሱ ፖለቲካ ነው፡፡
መልሱን ለቤቱ እንተወውና እስኪ ወደ በገና ጨዋታችን እንመለስ፤ ዘመነ ሕማማት ላይ ተኹኖ …አ! ይቅርታ ሰሙነ ሕማማት ላይ ተኹኖ የረባ ያልረባውን መቦትለክ ደግ አይደለምና አርፈን፣ ‹‹በአንተ ጎዳና›› ስልት በገናችንን እንጫወት፡፡

‹‹የሥጋ ቤቱ በራፍ፣
ተጨንቀ አሉ በሰው ሰልፍ፤
ይቅርብህ ሰልፉ የምር፣
ሁሌ በሥጋ አትኖር፡፡

ድንገት፤ እንዲያው ድንገት፣ ‹‹አንዳንዴ ስንኳ ስለምን ሌላ ጨዋታና የዳንኪራ ቃላት አይወጣችኹም?›› ባይ ተቺ ቢመጣ ጆሮ አንሰጥም፡፡ ለምንና ለማን ብለን!? ለመከራ የተጣፍን፤ ለእንጉርጉሮ የተፈጠርን አይደለንምን? …ባይኾን ሕመማችንን በሰሙነ ሕማማት እያሰብን እንተክዝ እንጂ፤ (‹‹እንኳን አደረሳችሁ ለሕማማት ሣምንት›› አለች ጋዜጠኛዋ! ምን የሚሉት የመልካም ምኞት መግለጫ እንደኾነ እግዚሃር ይወቀው፡፡ …ዓመቱ በሙሉ የምን ዓመት ኾነና!?)

‹‹በእርሱ ቁስል፤ በእርሱ ሕመም፤
ተፈወስ፤ ዳነ ዓለም፤
በእኛ ቁስል በእኛ ሕመም፤
ጠፉ እንጂ ዳኚ የለም፡፡

የእኛ ነገር ወለፈንዲ ነው፤ ግራ ያጋባል፤ ጥቅስ መጥቀስ ላይ ኃይለኛ ነን፡፡ ለምሳሌ፣ ከምንተኛበት አልጋ፣ ከራስጌያችን በላይ፣ ‹‹በሞት ጥላ መካከል እንኳን ብሄድ አንተ ከእኔ ጋር ነህና ክፉን አልፈራም!›› የሚል ጥቅስ ባማረ የእጅ አጣጣል አጽፈን እንለጥፋለን፡፡ ተንተርሰን የምናድረው ግን ምን የመሰለ ቆንጨራ ነው፤ ወይም የቆላ ሽመል፡፡ (…ጎበዝ እስኪ ልጠይቃችሁ፤ አንድ ሰው ውስጥ ያለው፣ ስንት ሰው ነው!?)
ልክ በምሽት ሲወጣ፣ ከአፉ ጸሎት፣ ከእጁ ድንጋይ እንደማይለየው የተጨነቀ ሰው ማለት ነው፡፡ ሰውየውን፣ ‹‹በአፍኽ ጸሎት፣ በእጅኽ መማቻ ድንጋይ ከምትይዝ አንዱ ላይ ለምን አትበረታም?›› ቢሉት አሉ፣ ‹‹ጠላት ከድንጋይ ቢያመልጥ ከጸሎት፤ ከጸሎት ቢያመልጥ ከድንጋይ ማምለጥ አይቻለውም!›› አለ አሉ፡፡ ታዲያ በየት በኩል ፈጣሪ ይታረቀን ጎበዝ!? ኧረ በየት በኩል!? …ግራ ያጋባል፡፡

‹‹እኔ ምንዝሩ ችግረኛ፤
ጠም መፍቻዬን የት አገኛ?
ሁሉ ያላችሁ ሹማምንት፤
እንደያዛችሁ ፍቱት፤
ሁሉ ያላችሁ ሹማምንት፤
እንዳሻችሁ ፍቱት!››

…ሕም! በአንዱ ቀን በተስኪያን ልሳለም ወደ አንዱ ደብር ሄድኩ፤ አንገቴን ወደ ምድር ደፍቼ መጸለይ ስጀምር፣ አንድ ሰፊ እጅ አፍንጫዬ ስር ድቅን አለ፤ ‹‹ምንድን ነው?›› ብል የእጅ መዳፉ ባለቤት እንዲህ ተማፀነኝ፤ ‹‹ማንትስ ለተባለች አዲስ ቤተ ክርስቲያን ማሰሪያ!››
ተናደድኩ፤ ‹‹ጌታዬ ያሉትንም ተሳልሜ አልጨረስኩም፤ ዘወር በልልኝ!›› አልኩ ጮኼ፤ ባለእጁ መዳፉ ገለል አለለኝ፡፡ ተገረምኩ፤ በጣም ተገረምኩ፤ ‹‹ጌታ ዝቅ ብሎ የደቀ መዛሙርቱን እግር ባጠበበት ሰሞን እንኳን ምናለ የእኛን ኪስ ለማጠብ የሚደረገው ግብግብ ቢቀንስ!›› ስልም ተከዝኩ፡፡ …እግዚኦ!
ወደ ጸሎቴ ከመመለሴ በፊት ለአፍታ ቀና ስል ደግሞ፣ ቤተስኪያኑ በር ላይ እንዲህ የሚል ማስታወቂያ አነበብኩ፤
‹‹ለውድ የሙታን ቤተሰቦች የቤተ ክርስቲያኗ መሬት ለልማት ስለሚፈለግ ሙታንን እንድታነሱ ቤተ ክርስቲያኗ ትጠይቃለች፡፡ ወስብሐት ለእግዚአብሔር››
አይ ዕድላችን፤ ‹‹ሙታችሁም በሰላም አትረፉ!›› የተባልን ሰዎች፡ ፡ በቁምህ ከመኖሪያኽ ለልማት ትነሳለህ፡፡ ከሞትህ በኋላም ለልማት ትነሳለህ፡፡ ምን ዓይነት ኩነኔ ነው? ቆመንም ሞተንም እረፍት ማጣት፡፡
‹‹መኖርም መሞትም የከበደብሽ፤
የነንጠቅ አገር ጦቢያ እንዴት ነሽ?››
…ያለው ሰውየው፣ ወድዶ ነውን? በጭራሽ! …ጌታ ኾይ፣ ‹‹አፈር ነህና ወደ አፈር ትመለሳለህ ባልከን፤ መሠረት በአግባቡ አፈር መኾን ያልቻልነው በደላችን ምን ያኽል ቢከፋ ይሆን? …ኤዲያ! እስኪ ወደ በገና ጨዋታችን እንመለስ፡፡


‹‹የእኛን በደል የምታይ፤
የእኛን ስቃይ የምታይ፤
እውነት ጌታ በመንበርኽ አለኽ ወይ?››

(* ጌታችን ‹አዎ! አለሁ› ይበለን! መልካም የፋሲካ በዓል!)

# “አሁንም የሕወሓት ትግራይን የመገንጠል ዓላማ አልነበረውም”

### “በአፃዚ ንቅናቄ ፕሮጀክት የኤርትራን ጸፃማ ክፍል ወደ ትግራይ ለመጠቅለል ታስቧል”

## አምባሳደር ካሳ ከበደ



አምባሳደር ካሳ ከበደ በደርግ ዘመን ከፍተኛ የመንግስት ስልጣን ከነበራቸው ኃላፊዎች መሀል በግንባር ቀደምትነት የሚጠቀሱ ሲሆኑ፤ ባለፉት ሀያ ሰባት አመታት በስደት በኖሩበት አሜሪካን የኢትዮጵያ ፓስፖርት እንዳያገኙ በሕወሓት ግልፅ የሆነ ተፅዕኖ ቢደረግባቸውም በእነዚህ ሁሉ ዓመታት በሀገራቸው ፖለቲካዊ ጉዳዮች ዙሪያ ከፍተኛ እንቅስቃሴ ሲያካሂዱ ቆይተዋል።

ከበርካታ ዓመታት በኋላ በለውጡ ማግስት  ወደ ሀገር ቤት የተመለሱት አምባሳደር ካሳ ከበደን ከስምንት ወር በፊት የመጽሔታችን እንግዳ በማድረግ በተከታታይ ዕትሞቻችን የስራና የህይወት ተሞክሮአቸውን ማስነበባችን ይታወሳል፡ ፡ አሁን ደግሞ የሀገራችንን ወቅታዊ ጉዳዮች አስመልክቶ የተለያዩ ጥያቄዎችን አቅርበንላቸዋል። አምባሳደር ካሳ ከበደን በሚኖሩበት አሜሪካን ሀገር  የግዮን ጋዜጠኛ ፍቃዱ ማ/ወርቅ በስልክ እንዲህ ባለመልኩ አነጋግሯቿል።

**ግዮን፡- የጠ/ሚ/ር ዐቢይ አሕመድ አንድ ዓመት የስልለጣን ዘመን በእርስዎ ዕይታ እንዴት አለፈ?**

አምባሳደደር ካሳ፡- የጠ/ሚ/ር ዐቢይ አህመድን አንድ ዓመት የምመለከተው ከመነሻቸው ጋር አያይዤ ነው:: ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ የማስተዳደሩን ስልጣን ከመረከባቸው በፊት የነበረው ሁኔታ ምን ዓይነት ነበረ? የሚለውን ማየት ያስፈልጋል:: ያንን ከረሳነው፣ ይሄንንን አንድ አመት በቅጡ መመዘን የምንችል አይመስለኝም::

ያው ሁላችንም እንደምናስታውሰው፣ ሰሞኑን ደግሞ መባል እንደጀመረው “ኢትዮጵያ አለቀላት፣ ፈረሰች” ምናምን ተብሎ  የበርካታ ሕዝብ ስሜት ተሸብሮ የነበረበት ወቅት ነው:: እርሳቸው ወደ ስልጣን ከመምጣታቸው አስቀድሞ የነበሩት ሶስት ዓመታት፤ በየሳምንቱና በየዕለቱ ሊባል በሚችል መልኩ የሐገራችን አጠቃላይ ሁኔታ ቁልቁል እየወረደ የመጣበት ጊዜ እንደነበር ይታወቃል:: ሁላችንም በከፍተኛ ስጋት ተውጠን ነበር ማለት ይቻላል::

እዛ ላይ፤ በእውነት ተአምር ሊባል በሚችል ሁኔታ፣ ፍጹም ማንም ባልጠበቀው ሁኔታ፤ ኢህአዴግ ውስጡ ባካሄደው የፖለቲካ ትግል፣ የፖለቲካ ድርድርና የፖለቲካ ሂደት ዶ/ር ዐቢይ አህመድ ሊመረጡ ችለዋል:: እርሳቸው እንደተመረጡ ኢትዮጵያዊነትን አጉልተው በመናገራቸው፣ “የኢትዮጵያን ገናነት እናድሳለን” የሚል ተስፋ በመፈንጠቃቸው፤ ነገሮች ተዓምራዊ ሊባል በሚችል ሁኔታ ሊለወጡ መቻላቸውን እናስታውሳለን::

ከዛ በኋላ እንግዲህ በተከታታይ የወሰዷቸው ዕርምጃዎች አሉ:: የፖለቲካ ዕስረኞችን መፍታት በሚመለከት፣ ፕሬሱን በሚመለከት፣ የመፃፍ የመናገር የመሰብሰብና ሌሎች መሰል ዴሞክራሲያዊ መብቶችን በሚመለከት፤ ብዙ ዝርዝር ሁኔዎችን በስልጣን ጅማሬያቸው ወቅት ወደ ተግባር መለወጣቸውን መጥቀስ ይቻላል::

**ግዮን፡- በሽብርተኝነት የተፈረጁ የፖለቲካ ፓርቲዎችና መሪዎች፤ እርስዎን ጨምሮ የተለያዩ ግለሰቦችም ወደ ሀገር ቤት ለመግባት የቻላችሁት በጠ/ሚኒስትሩ ስልጣን ማግስት ነበር::**

አምባሳደር ካሳ፡- ትክክል:: የእኔ ዓይነት የፖለቲካ ሰው ብዙ ሰው፣ ከአመታት በኋላ ለሀገር የበቃበት ሁኔታ ተፈጥሯል:: እንደዚህ ዓይነት ሁኔታዎችን በዝርዝር ሁሉም ሰው ስለሚያውቃቸው ብዙም እዛ ውስጥ አልገባም:: ጅምሩ ላይ የነበረውን ሁኔታ እናስታውስ እንደሆነ፤ እንደውም ጠ/ሚኒስትሩ አይደለም “ፋታ፣ ጊዜ ስጡኝ” የሚለው ሕዝቡ ነበር:: ምክንያቱም “ለውጡ ፈጠነ” የሚል ትችት ሁሉ ይሰማ እንደነበረ መዘንጋት የለብንም::

በዛን ወቅት፤ እኔ አንድ ቃለ ምልልስ ከኢሳት ጋር አድርጌ ነበረ:: እዛ ቃለ ምልልስ ላይ “የለውጡን ሂደት በምዕራቦቹ አይን ማየት አለብን:: ሁሉንም ነገር በአንዴ አዲሱ ጠ/ሚ/ርና ካቢኔያቸው መተግበር አለበት ማለት አንችልም፤ እሱ አያስኬድም:: እርሳቸውም ቢሆኑ የሚያከናውኑትን ነገር በምዕራባውያን ሀገሮች መልኩ ቢያዩ ጥሩ ነው” የሚል ሀሳብ አቅርቤ ነበር::

በተጠቀሰው የመጀመሪያ ምዕራፍ ሊሰሩ ይችላሉ የተባሉ ነገሮች አብዛኞዎቹ ተሰርተዋል:: ሲተገበሩም አይተናል:: የቀሩት ደግሞ በሂደት ላይ ናቸው፤ እንግዲህ ሪፎርም ነው የተባለው:: ይሄን ሪፎርም እንግዲህ ሽግግር ለማለት አስቸጋሪ ነው፤ ተሃድሶ ማለት የሚቀል ይመስለኛል:: የእዚህ ተሃድሶ ሂደት በራሱ የለውጥ ሂደት ስላለው፣ በዚህ የተሃድሶ ሂደት ውስጥ የሚደረጉት ለውጦች ደግሞ የራሳቸው የሆነ ባህሪይ አላቸው:: ስለዚህ ነገሮች አስቸጋሪ ሊሆኑ እንደሚችሉ ገና በፊት ከጅምሩ ግልፅ ነበር::

**ግዮን፡- የለውጡ ሂደት ማለት ነው?**

አምባሳደር ካሳ፡- አዎ:: ለውጡ እንግዲህ ዴሞክራሲያዊ ስርዓት ኖሮ፣ የኢትዮጵያ ህዝብ ከዳር እስከ ዳር ተሳትፎበት፣ በሙሉ ህዝብ ይሁንታ የመጣ አስተዳደር አለመሆኑን እናውቃለን:: ጅምሩ ላይ እንግዲህ ለውጡ በራሱ በኢህአዴግ ውስጥ የመጣ ለውጥ ነው ብለናል:: ከዛ በፊት ሁሉን ነገር ተቆጣጥሮ የነበረው ሕወሓት ነው፤ ሕወሓትን ለመተካት በተደረገው ትግል ጎልተው የወጡት የአሁኖቹ ኦዴፓና አዴፓ ናቸው:: እነዚህ ሁለቱ እንዴት እንደተናበቡና ውጤታማ እንደሆኑ፣ ስብስባቸውንም “ቲም ለማ” ብለን እስከማድነቅ ደርሰናል:: የቲም ለማ አባላት በአመራር ደረጃ አራት ግለሰቦች ናቸው:: አቶ ለማ መገርሳ፣ ►

አቶ ገዱ አንዳርጋቸው፣ ዶ/ር ዐቢይ አህመድና አቶ ደመቀ መኮንን እንደሆኑ ስንናገር፣ ስንመሰክር ቆይተናል::

ይሄ ቡድን የሀገሪቱን የአመራር ስልጣን ከተረከበ በኋላ፤ እንዲሁም የቡድኑ መሪ ጠ/ሚ/ር ዐቢይ አህመድ ከሆኑ በኋላም ቢሆን፤ አሁን ጠ/ሚኒስትሩም ሆኑ አቶ ደመቀ፣ እንዲሁም አቶ ለማና አቶ ገዱ በሚገባ እየተናበቡ እየሰሩ እዚህ መድረሳቸውን እናውቃለን:: እነዚህ ግለሰቦች የሚመሯቸው ድርጅቶች የብሔር ድርጅቶች ናቸው፤ ወይም ብሔር ተኮር ድርጅቶች ናቸው:: የኦሮሞና የአማራ ብሔር ማለታችን ነው:: ኦዴፓና አዴፓ በሁለቱም ብሔሮች ህዝብ ውስጥ ሙሉ ለሙሉ ተቀባይነት አላቸው ማለት ያስቸግራል:: የኢትዮጵያ አማራ ሙሉ በሙሉ የመረጠው፣ የኢትዮጵያ ኦሮሞ ሙሉ በሙሉ የመረጠው ድርጅት አለ፤ ብለን አይደለም የምንናገረው::

እነዚህን ሁሉቱንም ድርጅቶች ያየናቸው እንደሆነ ሕወሓት የመንግስት ስልጣኑን ለመያዝ በተንደረደረበት ጊዜ የፈጠራቸው ወይም የተጎዳኛቸው ድርጅቶ ናቸው:: በሕወሓት አመራሮች የተፈጠሩና የተቀረፁ ድርጅቶች ናቸው:: በርግጥ ኦዴፓ (ብአዴን) ኢህዴን የሚባል እርሾ ነበረው፤ ኦዴፓ(ኦህዴድ) ደግሞ በአብዛኛው በምርኮኛ ወታደሮች፣ በሕወሓት ተጠፍጥፎ የተሰራ ስለነበረ፤ ታሪካቸው ይለያያል:: ግን ሕወሓት የመንግስታቱን ስልጣን ከተቆጣጠረ በኋላ ሁለቱንም ድርጅቶች መሳሪያ አድርጎ፤ አንዱን በኦሮምያ ክልል፣ ሌላኛውን በአማራ ክልል ላለው አገዛዝ ሲጠቀምባቸው እንደነበረ እናስታውሳለን:: ከእነዛ ሁለት ድርጅቶች ውስጥ የወጡ ሰዎች ናቸው የኦዴፓና አዴፓ መሪዎች::

ስለሆነም በመጀመሪያ ደረጃ ሕወሓት ይቆጣጠረው የነበረውን መዋቀር ሙሉ ለሙሉ የማፕራት ግዴታም ነበረባቸው:: በዛ ረገድ በከፍተኛው አመራር ደረጃ፣ በስራ አስፈፃሚ ኮሚቴያቸው፣ በማዕከላዊ ኮሚቴያቸው ሁለቱም ድርጅቶች የሕወሓትን ተፅዕኖና መሪነት ለማምከን ተንቀሳቅሰዋል:: እንግዲህ እዚህ ላይ ማየት ያለብን ሁለቱ ድርጅቶች ሕወሓትን ነው የተኩት፤ ሕወሓት ደግሞ እንዲሁ በዝምታና "አሜን" ብሎ አይደለም ስልጣኑን ያስረከበው::

**ግዮን፡- ሙሉ በሙሉ ሕወሓት በሽንፈት ነው ስልጣኑን የሰጠው ማለት ይቻላል?**

አምባሳደር ካሳ፡- በሽንፈት ነው:: ከሽንፈት ባሻገር ደግሞ ሕወሓት የኢህአዴግ መሪ በነበረበት ጊዜ የተፈፀሙ በደሎች፣ የተከናወኑ ዝርፊያና ሌብነቶችን ጨምሮ ሌሎች በርካታ ነገሮች በአንድ ዓመቱ የጠ/ሚ/ሩ የስልጣን ጅማሬ ላይ ተጋልጠዋል:: ይሄ ደግሞ የአመራር አቋም ብቻ ሳይሆን የህዝብም ጥያቄ ስለነበረ፤ ሕወሓት ወደ መከላከልና ወደ መሸሽ ፣ወደ መመሸግ የሄደበትን ሁኔታ ተመልክተናል::

የሕወሓት መሪዎች መቀሌ ሲመሽጉ፤ ሕወሓት ያደራጃቸው ድርጅቶች ኦዴፓና አዴፓ በአንፃሩ ስልጣኑን ሲይዙ፤ እነዚህን ድርጅታዊ ባህሪያቸውንና በድርጅቱ መዋቀር ውስጥ ያሉትን ሰዎች ማንነት ጠንቅቆ የሚያውቀው ሕወሓት፤ በዚህ መረጃው ተጠቅሞ እሱን የተኩት የለውጥ ኃይሎች አሰራር እንዳይሳካ፣ ለማደናቀፍ አልሞከረም ለማለት አይቻልም:: በግልፅም እየታየ ነው፤ እየሞከረም ነው::

አኔ አሁን የማየው ችግር፤ በከፍተኛው አመራር ደረጃ የአዴፓን በቅርበት ተመልክቻለሁ፣ ኦዴፓ ውስጥ የነበረውንም እንዲሁ ከርቀትም ቢሆን ታዝቤያለሁ:: ሁለቱም እነዚህ የሕወሓት መሳሪያ ናቸው የሚሉትን የቀድሞ አመራሮች እያስወገዱ የሄዱበትን መንገድ ተመልክተናል::

**ግዮን፡- የሕወሓት መጠቀሚያ ናቸው የሚባሉትን አመራሮች፤ ሁለቱ ድርጅቶች እስከመጨረሻው አስወግደዋል ብለው ያምናሉ?**

አምባሳደር ካሳ፡- በከፍተኛ አመራር ደረጃ ስል እንግዲህ በስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ፣ ከሞላ ጎደል በማዕከላዊ ኮሚቴ ደረጃ ያስወገዱ ይመስለኛል:: በአብዛኛው አስወግደዋል ማለት ይቻላል:: በአዴፓ በኩል የበለጠ በቅርበት ያለውን ስለማውቅ ነው፤ በኦዴፓ በኩልም የእዚሁ ዓይነት ሂደት ነው ያየነው:: ይሄ ብቻ ሳይሆን በዛ መዋቀር ውስጥ ያሉ ሰዎችን በአዲስ አመራር የመተካቱ ሂደት ቀላል አይደለም:: በዛ ረገድ ከኦዴፓ (ኦህዴድ) ይልቅ አዴፓ (ብአዴን) ተሳክቶለታል ማለት ይቻላል፤ አንፃራዊ በሆነ መልክ:: ግን በሁለቱም በኩል አይበቃም ያሏቸውን ማስወገዳቸውን አይተናል::

እነዛ የሚወገዱት ሰዎች ስልጣኑን ይልቀቁ እንጂ የሚኖሩት እዛው ቀድመው የሚኖሩበት አካባቢ ነው:: እነሱ እንግዲህ በኩርፊያም ሆነ በሌላ ስሜት፤ በለውጡ ሂደት ላይ ተግዳሮት አላሰደሩም ማለት አንችልም:: ይሄ አካሄድ ወይም በላይኞቹ አመራሮች ላይ የተወሰደው ዕርምጃ መቀጠል አለበት:: በማዕከላዊ ኮሚቴ ደረጃ ተደረገ ማለት፣ ወይም ደግሞ ከክልሉ ስራ አስፈፃሚና በክልሉ ስር ባሉ ቢሮዎች ከእነዛ ተነስተን ደግሞ በዞንም፣ በወረዳም እስከ ቀበሌ የእኛ የሚሏቸውንና ከለውጡ ጋር ሊሄዱ የሚችሉ ካድሬዎችን የመመደቡ ስራ ገና አልተጠናቀቀም:: በጅምር ነው ያለው::

**ግዮን፡- ስለዚህ የህዝቡ ማኩረፍ፣ የህዝቡ ለውጥ መፈለግና መጓጓት በቂ ምላሽ ለማስገኘት ገና ብዙ ስራ ይቀራል ነው የሚሉን?**

አምባሳደር ካሳ፡- በአንድ በኩል ይሄ ስራ እየተሰራ ያለና ያልተጠናቀቀ መሆኑን መገንዘብ አለብን:: ይሄ መደረግ አለበት የሚባለውን እኮ አስቀድመንም አስበናል:: እየተደረገ መሆኑንም እያየን ነው ያለነው:: ለምን በዚህ በአንድ ዓመት ውስጥ አልተጠናቀቀም? የሚል አቋም ይዞ መውቀስ "ለተቀማጭ ሰማይ ቅርቡ ነው" የሚባለው ዓይነት ሂስ ሊያስነዝር ይችላል:: ሌላኛው እንግዲህ ምን ዓይነት ህብረተሰብ? ምን ዓይነት ኢኮኖሚ? እንደው በአጠቃላይ ምን ዓይነት የፀጥታና የደህንነት የፖለቲካ ሁኔታዎችን ነው ይሄ የለውጥ ሃይል የተረከበው? የሚለውንም ደግሞ በጥንቃቄ መመልከት ያለብን ይመስለኛል::

በዛ ረገድ መጀመሪያ ለኢኮኖሚው እኔ ቅድሚያ የምሰጠው:: ሀገራችን የወጣቶች ሀገር ነች እንባላለን፤ ምክንያቱም ወደ ሰባ በመቶ የሚሆነው፣ የኢትዮጵያ ህዝብ ዕድሜው ከሰላሳ ዓመት በታች ነው እያልን ነው:: ኢኮኖሚው በሕወሓት የአመራር ዘመን ያው እንደምናውቀው በኢንቨስትመንት መልክም ሆነ በብድርም ሆነ በእርዳታ፣ ኢትዮየጵያ ውስጥ ታይቶ በማይታወቅ መጠን ከፍተኛ የውጭ ሀብት ወደ ኢትዮጵያ ገብቶ ነበር::

እነ ትራንስፓረንሲ ኢንተርናሽናል ሌሎች አግባብ ያላቸው አካላት አሁን እንደገለፁት ያን የሚያህል በብዙ ቢልየን ዶላር የሚቆጠር የውጭ ገንዘብ ወደ አገራችን ቢገባም፣ ለሀገሪቱ ዕድገት የዋለው በጣም መጠነኛ ነው:: ምክንያቱም ብዙው ገንዘብ ተዘርፏልና:: ይሄን በተመለከተ ብዙ ትችት ቀርቧል:: በዚህ ምክንያት በማህበራዊ አገልግሎቶች ረገድ ጤናን በተመለከተ፣ ትምህርትን በተመለከተ ዕድገት የታየ ቢሆንም፤ ይሄ ዕድገት በተለይ በትምህርቱ ዘርፍ የነበረው ዕድገት ምን ፈየደ? የሚለው ጥያቄ ያስነሳል:: ምክንያቱም ዛሬ ኢትዮጵያ ውስጥ በታሪካችን ታይቶ በማይታወቅ መጠን የወጣቶች ስራ አጥነት ጎልቶ መጥቷል::

ወጣቱ ይማራል፤ እንግዲህ ትምህርት ማለት አንፃራዊ ነው:: ግን በየደረጃው ዕድሜው ሲፈቅድለት፣ ከትምህርት ገበታው ትምህርቱን ጨርሶም ሆነ ሳይጨርስ፤ ስራ ፍለጋ የሚሰማራ ወጣት አለ:: ይሄን ወጣት ለሁለት ከፍለን ልናየው እንችላለን:: ቀደም ባለው ጊዜ በየምክንያቱ ትምህርቱን እያቋረጠ፣ ዕድሜው ለስራ ደርሶ ስራ ፈላጊ በሚሆንበት ጊዜ፤ ወላጆቹ ሰፋ ያለ የመሬት ይዞታ ስለነበራቸው፤ የወላጆቹን መሬት እየተጋራ፤ አብሮ እያረሰ እዛው ወላጆቹ አከባቢ ቤት ሰርቶ ትዳሩን መስርቶ የሚኖርበት ሁኔታ ነበረ::

ያ አርሶ አደር የነበረው አካባቢ ዛሬ ያለው መሬት እየተጣበበ ስለመጣ፣ ወላጆቹ ወትሮ ያደርጉት የነበረ የመሬት ቦታቸውን አካፍለው ወጣቱን እዛው በእርሻ ስራ መስማራት አልቻለም:: በዚህ ምክንያት ትምህርት ቀመስ የሆነው ወጣት ዕድሜው ለስራ በሚደርስበት ጊዜ በቤተሰቦቹ እየተደጎመም ሆነ በሌላ ዘዴ ኑሮውን ለመግፋት ወደ ከተሞች ነው የጎረፈው:: ከተሞች ስል እነዚህ የንግድ ቦታ የሚባሉት ትንንሽ ከተሞችን ጭምር ማለቴ ነው:: ይሄ ከፍተኛ የሆነ የሥራ አጥ ወጣት ክምችት በኢኮኖሚ ረገድ ብቻ ሳይሆን በማህበራዊ ባህሪይውም መታየት ያለበት ይመስለኛል::

ስራ ያጣ ወጣት ማለት ተስፋ እየቆረጠ ያለ ወጣት ማለት ነው:: ተስፋ እየቆረጠ ያለ ወጣት ደግሞ ብስጩ ወጣት ማለት ነው:: ብስጩ ወጣት ደግሞ ከዛ ብስጭት የሚያስለቅቀውን ነገር ይፈልጋል፤ ዕፅ መጠቀምን ይመርጣል:: ያ አምሮቱ ካልተሳካለት አቅሙ በፈቀደ ዜዴ ሁሉ ያንን ነገር ለማግኘት ይመኛል:: ይሄንንን በምልበት ጊዜ ጥንቃቄ ማድረግ ያለብን፤ እንደው ወጣቱ ሁሉ፣ ስራ አጥ ወጣቱ ሁሉ በዚህ ከታጎሪ የሚፈረጅ ነው የሚል ግንዛቤ እንዳንወስድ መጠንቀቅ ያስፈልጋል:: እኔ ኢትዮጵያ ውስጥ ጥቂት ወራት ቆይቼ፤ ብዙ አካባቢዎች ተዘዋውሬ ለማየት ሞክሪያለሁ:: በዚህ የሰራተኛ ጉዳይ ቀዳሚ የስራ ልምድም ነበረኝ፤ በፊት በስራም ተሳትፌ ስለማውቅ፤ ችግሩ ምን ያህል የገዘፈ እንደሆነና ዛሬ ኢትዮጵያ አሉ ከሚባሉ "ሶሾ ኢኮኖሚ" ችግሮች ሁሉ

ትልቁ ችግር የወጣቶቻችን ስራ አጥነት ነው:: ይሄንን ነገር በሆነ መንገድ መፍታትና ከችግሩ መውጣት አለብን የሚል ስሜት አድሮብኝ ነው ወደ አሜሪካ የተመለስኩት::

ይሄንን ጉዳይ በተመለከተ ላገኘኋቸው አመራር አካላት ሁሉ አስተያየቴን በቃልም በፅኁፍም ስገልፅ ነበር:: ከአንዳንዶቹ ጋራ ስለመፍትሔው ስመካከር ነበር፡ እንግዲህ ይሄን የሥራ አጥነት ችግር እነ ዶ/ር ዐቢይ የፈጠሩት አይደለም:: የወረሱት ነው::በወረሱት ላይ ደግሞ የአንድ አመት ተመራቂዎችም ሆኑ ድሮፕ አውት (የሚያቋርጡ) ወጣቶች ደግሞ ተጨምረውበታል:: በዚህ አንድ ዓመት ውስጥ የተመረቁትንና ያቋረጡትን፣ ስራ አግኝተው ከተሰማሩት ወጣቶች ጋር ብናስተያይ ስራ ያገኙት ወጣቶች ቁጥር በጣም አነስተኛ ነው::

የእዚህ የስራ አጥነት ችግር ለመቅረፍ ቀላል አይደለም:: ከዚህ ጋር ተዛምዶ አሁን ሀገር ውስጥ ያለውና ሁሌ የምንነጋገርበት አንዱ "ኢትዮጵያ ፈረሰች"፣ "ኢትዮጵያ ተገነጣጠለች" የሚለው ስሜት ያሳደረው የሰላምና የመረጋጋ ዕጦት ነው:: ሰላምና መረጋጋት በምንልበት ጊዜ ማህበረሰባችንም ስራ አጥቶ፣ ተስፋ ቆርጦ የተበሳጨ ወጣት በብዛት የሚገኝበት መሆኑን መዘንጋት ያለብን አይመስለኝም:: በተጓዳኝ መሰራት ያለባቸው ስራዎች አሉ::

**ግዮን፡- ምን ምን ናቸው እነዛ ስራዎች?**

አምባሳደር ካሳ፡- በአንድ በኩል ሰላምና መረጋጋቱን የማስፈን ሂደት ነው:: በሌላ በኩል ኢኮኖሚውን አንቀሳቅሶ ለእነዚህ ወጣቶች ስራ መፍጠር ነው:: ስለዚህ ስራ ፈጣሪ የሆኑ ፕሮጀክቶች ላይ ማተኮር ያለብን ይመስለኛል:: አሁን ኢንዱስትሪያል ዞን የሚባሉትን አንድ ሁለቱን ተመልክቻለሁ፤ በርግጥ የውጭ ኢንቨስተሮች ኢንዲመጡ የሚጋብዙ ናቸው:: ግን የተከማቸውን የስራ አጥ ወጣት ችግር ይቀንሳሉ ወይ? በእነሱ በኩል የሚፈሰው ሌላው የኢኮኖሚ ጠቀሜታ እንዳለ ሆኖ፣ ከዚህ ችግር አንፃር እንዴት ይታያል? በምንልበት ጊዜ ማየት ያለብን፤ ያንን ካፒታል ይዘው የሚመጡ ኢንቬስተሮች በእነዚህ ኢንዱስትሪ ዞኖች ውስጥ ለመስራት የሚፈልጉት ለማትረፍ ነው::

ለማትረፍ ቅድሚያ ስለሚሰጡ ብዙዎቹ ፕሮጀክቶች ካፒታል ኢንሴቲቭ ናቸው:: በመሳሪያ (በማሽን) ኃይል የሚሰሩ ናቸው:: በሰው ኃይል የሚሰሩ አይደሉም:: በማኑፋክቸሪንግ ዘርፍ ካፒታል ኢንሴንቲቭና ሌቨር ኢንሴንቲቭ የሚባሉ ነገሮች አሉ:: በኢንዱስትሪው ሌቨር ኢንሴንቲቭ የሚባለው የሚቻለውን ያህል፣ ከማሽን (መሳሪያ) ይልቅ በሰው ኃይል ለማምረት የሚደረግ እንቅስቃሴ ነው:: ግን ደግሞ የሰው ኃይል በብዛት ማሰማራቱ የራሱ የሆነ የአስተዳደር ችግር አለው፤ ሌላም ተዛማጅ ጉዳይ አለው:: ስለዚህ ትርፍ ላይ ብቻ በሚያተኩሩበት ጊዜ ኢንቨስተሮች በሰው ሀይል ሊሰራ የሚችለውን ነገር ሁሉ በተቻለ መጠን በማሽን ለመስራት ያተኩራሉ:: እሱ ካፒታል ኢንሴንቲቭ ይባላል::

አሁን በኢንዱስትሪ መንደሮች ውስጥ የሚቋቋሙት ካፒታል ኢንቴንሲቭ ናቸው:: ምክንያቱም ከውጭ የሚመጡት ኢንቬስተሮች የሰው ሃይል ክፍያው አናሳ ስለሆነ፤ አንፃራዊ አድቫንቴጅ እናገኛለን ብለው ነው የሚመጡት:: በዛ ምክንያት የሚያስፈልጋቸውን የሰራተኛ ኃይል በተቻለ መጠን ለመቀነስ ይሞክራሉ:: በተቻለ መጠን ለሰራተኛ የሚከፈለውን ደሞዝ ለማሳነስ ይሞክራሉ::እነዚህ ኢንዱስትሪያል ፓርኮች መጠነኛ አስተዋፅኦ ሊያደርጉ ቢችሉም ለዚህ ችግር መቅረፊያ ይሆናሉ ማለት ግን ያስችግራል:: ብዙ የእኛ ዓይነት ፈተና የገጠማቸው ሀገሮች አሉ፤ አሜሪካም ከአንደኛው ዓለም ጦርነት በኋላ የነበራቸውን ዘመን ብንመለከት፣ ያንን ችግር የተወጡት የበለጠ ገጠራማው ክፍል ላይ በማተኮር ነው:: ከተሞች ውስጥ ደግሞ የፐብሊክ ወርክ ፕሮጀክቶችን በመቀረፅ ነው ችግሮቻቸውን የፈቱት::

በዛ ረገድ አሁን እኔ ኢትዮጵያ ውስጥ እንዳየሁት ከሌሎቹ ሴክተሮች የበለጠ የኮንስትራክሽን ዘርፍ የሥራ ዕድል ፈጥሯል:: ያ ግን የሚቀጥል አይመስልም:: የግብዓትም፣ የገበያም ሆነ ሌላ ተዛማጅ ነገሮች አሉና:: ተደጋግሞ እንደሚባለው የኢትዮጵያ ሀብት የሰው ኃይሏ ነው፣ መሬቷና ውሃዎቿ ናቸው:: ኢትዮጵያውያን በዚህ በእርሻ የተሻለ ዕድል ሊኖረን ይችላል ብዬ እገምታለሁ:: የገጠሩ ልማት ደግሞ አስፈላጊ ነው፤ መሬቱም ውሃውም አለ:: ለእዛ የሚሆን ካፒታል በማፈላለግ ላይ እንዳሉ አውቃለሁ:: እነርሱ በፍጥነት ስራ ላይ ሊውሉ አልቻምሉ፣ ዝግጅት ይጠይቃልና::

በተለይ እነዚህን የገጠር ፕሮጀክቶች ለመተግበር ካፒታል ያስፈልጋል:: የውጪ ምንዛሬ ኮምፖናንትም አላቸው፤ የዘመነ የእርሻ ስርዓት ማካሄድ ስለሚታሰብ:: ይሄ ሁሉ በዚህ አንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ ለምን አልተተገበረም? ለማለት ያስቸግራል:: ይሄንን የጠቀምኩት የስራ አጥነቱን ችግር በተመለከተ እርሱ ካለው የሰላምና መረጋጋት ችግር ጋር ዝምድናም እንዳለው ጭምር ለማመልከት ነው:: ብዙ ጊዜ ሰላምና መረጋጋት ስንል በብዛት የምናስተውለው ወጣቶች ላይ ነው::

በሌላ በኩል ከላይ እንደገለፅኩት፤ አሁን የአመራር ስልጣኑን የጨበጡት ኦዴፓና አዴፓ ናቸው በምንልበት ጊዜ የኢትዮጵያ ህዝብ በሙሉ የመረጠው አመራር እንዳሆልነ ገልፀናል:: ስለዚህ ሁለቱም ድርጅቶች ተቀናቃኞች አሏቸው ማለት ነው:: ጠ/ሚ/ር ዐቢይ አህመድን ያየን እንደሆነ ድርጅቶቹን ወደ ጎን ትተን፤ በመስመር ደረጃ ብንመለከት እነሱ ኢትዮጵያዊነት የሚሉት፣ የኢትዮጵያ አንድነት የሚሉት፣ ዴሞክራሲና እኩልነት የሚለውን ህብረ ብሄራዊነት በማለት የሚያቀነቅኑትን፣ የሚነግሩንን ነገር ከልባቸው እንደሚመኙ፤ መተግበርም እንደሚፈልጉ እኔ አምናለሁ፤ አልጠራጠራቸውም:: ግን በርካታ ተግዳሮቶች አሉባቸው::

**ግዮን፡- እነዚህን ፈታኝ የሚሏቸውን ተግዳሮቶች በግልፅ ቢያስቀምጧቸው?**

አምባሳደር ካሳ፡-የእነሱን ኮንሰስታንሲ ወደድንም ጠላንም መላው የኢትዮጵያ ህዝብ ሳይሆን የኦሮሞ ሕብረተሰብ ክፍል ነው:: ይሄ ኮንሰስታሲያቸውን ፖለቲከኞች እንደመሆናቸው መጠን ህዝብ እንዲከተላቸው ይፈልጋሉ:: ግን እዛ ኮንስታንሲ ውስጥ ምን ዓይነት ሁኔታ ነው ያለው? በምንልበት ጊዜ አሁንም ቢሆን በዚህ በኦሮሞው ህብረተሰብ ክፍል ውስጥ መጠኑ እየቀነሱ ቢሄድም በኦነግ 50 እና 60 ዓመት የተቀነቀነ የመገንጠል አባዜ ከህዝቡ አዕምሮ ውስጥ ሙልጭ ብሎ ወጥቷል ማለት አይቻልም:: ከኦሮሞ ህዝብ ውስጥ ማለቴ ነው::

ያንን የሚመኙ ኤለመንቶች አሁንም አሉ፤ ይባስ ብለው ደግሞ ከእነዚህ ኤልመንቶች መካከል ትጥቅ ያልፈቱና በትጥቅ ጭምር አመራሩን የሚገዳደሩ ኃይሎች አሉ:: በዚህ በምዕራብ ወለጋ የነበረውን፣ በቦረና የነበረውን ሁኔታ እናውቃለን:: በርግጥ ዕርምጃ ተወስዶ ለማርገብ ተሞክሯል፤ ግን ሙሉ በሙሉ መፍትሄ አግኝቷል ማለት አይደለም:: በሌላ በኩል ደግሞ ሕወሓት ከአገዛዙ ሲወገድ አርፎ አልተቀመጠምና የለውጡ ኃይል አንዳይሳካለት አንዳንድ ችግር እየፈጠረ ነው ብለናል፤ እነዚህ እንገነጠላለን ብለው አመራሩን ለማድከም በትጥቅ ትግል የሚንቀሳቀሱትን የኦሮሞ ቡድኖች ሕወሓት ባለው አቅም አይረዳቸውም ማለትም አይቻልም::

በሌላ በኩል ደግሞ የኢትዮጵያን አንድነትና ጥንካሬ የማይፈልጉ ታሪካዊ ጠላቶች እንዳሉን መርሳት የለብንም:: እነዚህ ታሪካዊ ጠላቶች ዳግም ውስጣችን ያለውን ሁኔታ እያደመጡ ሊያዳክሙን የሚችሉ ዕርምጃዎችን አይወስዱም ማለት አይቻልም:: አንዱ ተግዳሮት እነዚህ እንገነጠላለን የሚሉትን የኦሮሞ ሃይሎች ለማርገብ እየሞከሩ እንደሆኑ እናያለን::

ሁለተኛው ሕወሓት ከተወገደ፣ የትግሬዎቹ ጠቅላይነት ከተነሳ አሁን ደግሞ ተራው የኦሮሞ ሆኖ "እኛው ጠቅላይ ሆነን መውጣት አለብን" የሚል ኃይል ደግሞ አለ፡፤ ይሄ ሃይል አደገኛ ሃይል ነው:: ይሄንን የሚሉት እነዚህ ልሂቃን የምንላቸውና ፖለቲከኞች ናቸው:: በኦነግ ውስጥ ያሉ::

የእነዚህ ኃይሎች የኦሮሞ ጠቅላይነት እሳቤ ለእዚህ ስራ ላጣው ወጣት ያጓጓዋል ያስጎመጀዋል:: ችግሩን የሚቀርፍለት ይመስለውና በቀላሉ በእዛ ስር ሊሰለፍ ይችላል:: ይህ እንዳይሆን ደግሞ እነ ጠ/ሚ/ር ዐቢይ አህመድ ይሄንን ወጣት ላለመዘረፍ የሚሄዱበት መንገድም እንዳለም እያየን ነው:: ስለዚህ ከእዚህ ሁለት ተወዳዳሪ ሃይሎች እየታገሉ እያሉ፤ እኛ የምንፈልገውን ብቻ እንዲያደርጉ መመኘት የዋህነት ይመስለኛል:: ስለዚህ መታገስና ጊዜ መስለጠት አለብን:: ደግሞም ይገባል::

**ግዮን፡- በቅርቡ የኢህአዴግ ም/ቤት ስብሰባ አጋር ድርጅቶችን ባካተተ መልኩ ወደ አንድ ድርጅትነት ይቀየራል ቢባልም ይሄ ሀሳብ በጉባኤው አልተነሳም፤ ጉባኤውም የተከናወነው በዝግ ነበር:: ከስብሰባ አስቀድሞ ሕወሓት ባወጣው መግለጫ የውህደቱን መንገድ እንደማይደግፍና እሱም እንደማይካተት አሳውቋል:: በሌላ መልኩ በኢህአዴግ ጉባኤ ላይ እስከ ዛሬ ባልታየ መልኩ አጋር ድርጅቶች ተገኝተዋል:: እነዚህን ሁኔታዎች እርስዎ እንዴት አገኟቸው?**

አምባሳደር ካሳ፡- በሕወሓት በኩል አንደኛ አሁን ያለው ብሔር ተኮር ፌደራል አደራረጀት መነካት እንደሌለበት፣ ሕገ መንግስቱ መነካት እንደሌለበት፣ ወደ አንድነት የሚያስኬድ ምቹ ሁኔታ እንደሌለ ተገልጧል:: ስለዚህ ኢህአዴግ ወደ አንድ ወጥ ኢትዮጵያዊ ፓርቲነት ይለወጣል የሚለው ሀሳብ ሕወሓትን በአሁኑ ደረጃ ሊጨምር የሚችል አይመስልም:: በሌላ በኩል እነዚህ አጋር ድርጅቶች በስብሰባው ላይ እንዲገኙ መደረጉ ደግሞ፤ ቀደም ብሎ በጠቅላይ ሚኒስትሩ ተገልፆ የነበረውን የመዋሃድ ሂደት እውን ለማድረግ እንደ ጅማሮ ነው ብዬ እገምታለሁ::

ስለዚህ ሕወሓትን ሳይጨምሩ ሶስቱ (ኦዴፓ፣ አዴፓ፣ ደኢህዴን) የኦሮሞ፣ የአማራና የደቡብ ድርጅቶች እነዚህን አጋር ድርጅቶች ይዘው ወጥ ኢትዮጵያዊ ፓርቲ ወይም ውህድ ሆነው ራሳቸውን ለምርጫ ያቀርባሉ የሚለው ነው የሚታየኝ:: በአጭር ጊዜ ውስጥ የሕወሓትን አቋም ማስለወጥ የሚችሉ አይመስልም:: ሕወሓት ደግሞ እንደምንሰማው በራሱ ለሶስት የተከፈለ ሆኗል:: እነ ደብረፂዮን ሊፈልጉም፣ ሊስማሙም ይችሉ ይሆናል:: ግን ሌሎቹ ኃይሎች አሁንም የመወሰን ስልጣን ስላላቸው ደፍረው ላይሄዱበት ይችላሉ::

ከዚህ በተጨማሪ ትግራይ ውስጥ የተፈጠረ የሕዝብ መከፋፈል አለ፤ ዛሬ ምስራቅ ትግራይና ምዕራብ ትግራይ እንደ በፊቱ እየተናበቡ ያለ አይመስልም:: ትንሽ የአሻፈረኝ ስሜት በምስራቁ በኩል እየተንፀባረቀ ነው:: ይህ ሁኔታ ደግሞ እያደገ ሊሄድ የሚችል ይመስላል:: ታሪካዊ መሰረትም አለው::

**ግዮን፡- ምንድን ነው ታሪካዊ መሰረቱ?**

አምባሳደር ካሳ፡- ታሪካዊ መሰረቱ ይሄ ቀዳማይ ወያኔ የምንለው በ1934 እና 1935 ዓ.ም በትግራይ ተከስቶ የነበረውን እንቅስቃሴ ከተመለከትን ያኔ በማዕከላዊ መንግስት ላይ አምጾ የተነሳው ምስራቅ ትግራይ በተለይ እንደርታ ነው:: አሁን መቀሌ የምንለው አካባቢ:: እንግዲህ ልዩነቱን መቀሌና አደዋ ልትለው ትችላለህ:: የምስራቁ ማዕከል መቀሌ ነው፣ የምዕራቡ ማዕከል አድዋ ነው:: ልዑል ራስ መንገሻ ስዩም ገና ልጅ እያሉ ደጃዝማች ተብለው እሳቸውን በመያዝ ያንን አመፅ ያካሄዱት የምስራቅ ትግራይ ተወላጆች ናቸው:: ይሄንን አመፅና መነሳሳት ያከሸፉት ደግሞ ራስ አበበ አረጋይ የበላይ ሆነው ጦሩን ቢያዘምቱም፣ አካባቢውን ለተወሰነ ጊዜ ቢያስተዳድሩም እነ ደጃዝማጅ በላይ ካሳ ናቸው የድሉ ባለቤት::

ደጃዝማች በላይ ካሳ አርበኛ ናቸው፣ የአድዋ ተወላጅ ናቸው:: ያንን አመፅ የደመሰሱት እነዚህ ሰዎች ናቸውና ከዛን ጊዜ ጀምሮ በአድዋና በመቀሌ ተወላጆች መካከል መቀናናትና አለመግባባት አለ:: መፎካከርም አለ:: ሁለተኛውንና 27 ዓመት ስልጣን ላይ የነበረውን ወያኔ ያየን እንደሆነ መሰረቱን አድዋ ላይ አድርጎ ነው የተነሳው:: ከዛ በኋላ አክሱምና ሽሬን ጨምሯል:: አሁን ይሄ ቡድን ለሶስት ተከፍሏል:: የድረብፂዮን ግሩፕ አንዱ ሲሆን፣ አንዱ የጌታቸው አሰፋ ሌላው ደግሞ የስብሃት ነጋ ግሩፕ ልትለው ትችላለህ::



**ግዮን፡- ይሄ መከፋፈል በሕወሓት ውስጥ ካለ የጠ/ሚ/ር ዐቢይን ሀሳብ የሚደግፈው ቡድን ሙሉ ለሙሉ ወደ ለውጡ መቀላቀል ያልቻለበት ምክንያት ምንድን ነው? ዳር ዳር ማለቱስ የት ድረስ ያስኬዳል?**

አምባሳደር ካሳ፡- ትልቁ ዳርዳርታ ሕወሓት ቅድም እንዳልነው ምዕራብ ትግራይ ውስጥ ቢመሰረትም፣ ቢደራጅም ምስራቁን ደግሞ ማቀፍ ስለነበረበት "ወያኔ" የሚለውን ቃል ድርጅቱ ውስጥ የጨመረው ምስራቅ ትግራይን ለማቀፍ ወይም ለማካል እንዲረዳው ነው:: ከዛ በኋላ ከምዕራብ ወደ ምስራቅ ተንቀሳቀስሶ ምስራቅ ውስጥም ድርጅታዊ መዋቅሩን መዘርጋት ችሎ ነበር::፡

ወደ መነሻው ከሄድንና ሂደቱንም እስከ ደርግ ውድቀት ከተከታተልን ኢትዮጵያን የመግዛት፣ ኢትዮጵያን የማስተዳደር ነገር የተመኘው ኢ..ህ.ዴ.ን ከተቀላቀለውና ወደ አማራው ህዝብ፤ ወደ ወሎና ጎንደር መሻገር ከቻለ በኋላ ነው:: እስከ እዛ ድረስ የታገለው ግን ትግራይን ከኢትዮጵያ ለመገንጠል ነው:: ስሙም፣ ማኒፌስቶውም በዛው መሰረት የተዘጋጀ ነው::

ከሻዕቢያ ጋር የነበረውን ግንኙነት ብንመለከት ሕወሓት ከሻዕቢያ ጋር የነበረው ችግር "እገነጠላለሁ፣ አትገነጠልም" የሚል ነው:: ሻዕቢያ "እኛ የቅኝ ተገዢነት ታሪክ ስላለን፣ ከቅኝ ግዛት ነፃ የመውጣት ጥያቄ ይዘን ነው የተነሳነው:: እናንተ የኢትዮጵያ አካል ሆናችሁ የኖራችሁ ናችሁ፣ እዛው ኢትዮጵያ ውስጥ የመንግስት ስልጣን ለመንጠቅ ታገሉ እንጂ መገንጠል አያስፈልጋችሁም" የሚል አቋም ነበረው:: እነሱ ደግሞ "እናንተ የትግል አጋራችን ናችሁ እንጂ ሞግዚታችን አይደላችሁም፤ ምን ማድረግ እንዳለብን ልትጠቁሙን አይገባም" በሚል በየጊዜው ይናቆሩ ነበር፤ ፅሁፍ ይለዋወጡ ነበር፤ ይነቃቀፉ ነበር::

አሁንም የሕወሓት ትግራይን የመገንጠል ዓላማ አልከሰመም :: ውህደቱን የማይፈልገው ሃይል ዋነኛው ምክንያቱ ይሄ ነው:: እንደውም ከዚህ ዘለል ብለው በእነሱ ምኞት ከትግራይ በተጨማሪ፤ የትግራይን ክልል የማስፋቱን ሂደት እያየን ነው:: ወደ ወልቃይትና ወደ ጠገዴ ተስፋፍተው መሬት በመያዝ ትግራይን ከሱዳን ጋር ማገናኘትና ትግራይን የጎረቤት ሀገር ድንበር ባለቤት የማድረግ፤ በዛው ደግሞ ወደፊት ለሚያቋቁሙት ትግራይ ግብርና ስራ እጅግ በጣም ጠቃሚ የሆነ መሬት ማግኘት:: እንደዚሁ በራያ በኩል አካባቢው በጣም ለም ስለሆነ፣ ወደ ፊት ለምትቋቋመው ትግራይ እንዲሁ ለም መሬት ለማግኘት፤ ከዛም ከፍ ካለና ከተሳካላቸው ደግሞ እንደውም ወደ አፋር ተሻግረው የቀይ ባህር ዳርቻ ሀገር የመሆን ህልምም አላቸው::

ይሄ ብቻ አይደለም የአጋዚ ሙቭመንት ብለው የጀመሩት ፕሮጀክት አላቸው፤ አዲስ ፕሮጀክት:: የእዚህ ፕሮጀክት ዓላማ በኤርትራ በኩል ደገኛውን የአካለጉዛይ፣ የሀማሴንን፣ የሰርዓይን ህዝብ አንድ ነን ብለው በመቀስቀስ በኢኮኖሚ ችግሩ በኩል በመግባት ወደ ትግራይ ለመሳብና ከትግራይ ጋር ደጋውን ኤርትራ አዋህዶ "ትግራይ ትግርኝ" በሚለው ኮንሰፕት አዲስ ጠንካራ ሀገር ሆና መውጣት ይቻላል የሚል ህልም ውስጥ ያሉ ተጋሩዎችም አሉ:: እና ይሄ ህልም እያለ ይሄንን ስማቸውን የመለወጡ፣ በተለይ ደግሞ ነፃነታቸውን ሰውተው ከሌሎቹ ፓርቲዎች ጋር ተዋህደው፤ ወጥ ፓርቲ ሆነው የመውጣቱ ፈተና የገጠማቸው ነው የሚመስለው:: የሚያደርጉትም አይመስለኝም::

**በአቶ ለማ መገርሳና በአቶ ገዱ አንዳርጋቸው ሹመት፤ በአዲስ አበባና በተለያዩ ርዕሰ ጉዳዮች ዙሪያ ያደረግነውን ቃለምልልስ በቀጣይ ዕትማችን ይዘን እንደምንቀርብ ከወዲሁ እንገልፃለን::**

# ሠጋት!... እልህ!... ወይስ መብት



መለስ ሸኔ

አዲሱ ቃላችን “ለውጥ” የሚለው ከሆነ ዓመት ተቆጠረ:: በዚህ አንድ አመት ጊዜ ውስጥ ቃሉን የሚመጥን ተግባር አይተናል ወይ ብለን ስንጠይቅ የምናገኘውን መልስ ግን መተንበይ ካልሆነ በቀር እርግጠኛ ሆነን ለመናገር አዳጋች ይሆንብናል:: በዚህ የለውጥ እንቅስቃሴ ውስጥ ችግሮች ከመቼውም የበለጠ እንደ አሸን እየፈሉ በከፊል ሠላማዊ የነበረውን የኑሮ ዘይቤያችንን እያናጉት ቢመጡም ቅሉ የፖለቲካ ጥማታችንን ግን በመናገርም ደረጃ ቢሆን እያረኩት ነው:: እንግዲህ ለውጡ ከዚህ ጥግ የሚነሳ ከሆነ ዘንዳ እኔ ደግሞ ዳር ዳሩን እንዲህ ልዳስሰው ከጀልኩ::

የለውጡ መሪ የሆነው የዶ/ር አብይ መንግስት በበርካታ መድረኮችና በተገኘው አጋጣሚ ሁሉ ስለሠላም ስለአንድነትና ስለኢትዮጵያዊነት በመስበክ ረገድ የተሳካ ጊዜ አሳልፏል ለማለት ያስደፍራል:: የዚያኑ ያህል ልክ ወርቃማውን የኢትዮጵያዊነት ቅኔ በስማገባቸው ማግስታት ሁሉ ግን የልዩነታችንን ክፋት ወለል አድርገው የሚያሳዩ የመግደል፣ የማፈናቀልና የመበታተን ስራና ሴራዎችን እያየን ነው:: ይህ ተግባር መነሻው ከየት ነው ብሎ ለመናገር የሚያስችል ሀቅ ማግኘት ባይቻልም የተጀመረውን የለውጥ እንቅስቃሴ ከውስጥም ከውጭም (አንድም ከአገር ውስጥ አሊያም ከውጭ፣ አንድም ከገዢ ፓርቲው ውስጥ አሊያም ውጭ) እርምጃውን ሆነ ብሎ የማዳከምና የማክሰም እንዲሁም በሩጫና ግርግሩ ውስጥ አትራፊ ሆኖ ለመገኘት የሚደረግ ወይም የቆየ ድብቅ አላማን ወደ ተግባር ለመለወጥ የሚደረግ እንቅስቃሴ መኖሩን ያመለክታል::

ከዚህ ስንነሳ ደግሞ ነገሩ ከስጋት፣ ከእልህና ከመብት ጉዳዮች ጋር በቀጥታም በተዘዋዋሪም የሚያስናስል ሆኖ ይስተዋላል:: በአገር አንድነትና ሠላም ጉዳይ ላይ እልህ የሚያጋቡ ጥያቄዎች መነሳታቸው የግድ ቢሆንም፣ የእልሁ ዓይነትና ደረጃ ግን ገደብ የሌለውና አንዳንዴም ከአገራዊ አጀንዳ ይልቅ በግለሰቦች ፍቃድና ፍላጎት ላይ የተመሰረተ ሆኖ ማየታችን ደግሞ ነገሩን የበለጠ ያወሳስበዋል::

ሠዎችን ለዓመታት ጎጆ ቀልሰው፣ ትዳር መስርተውና ሀብት አፍርተው ከኖሩበት ኢትዮጵያዊ ቀዬ ማፈናቀልና ማባረር እንደ መብት የተቆጠረበትንና በዚህም ወቅታዊ የለውጥ ምላሽ ያልተሰጠበት፣ ይልቁንም ወደባሰ ደረጃ እየተሸጋጋረ ያለበት ሁኔታ ላይ የመድረሳችን ዋነኛ ምክንያት ግለሰባዊና መንግስታዊ ዕልህ ምን ያህል ስር እንደሰደደ የሚያሳየን ሀቅ ነው:: የመንግስትን ተግባራት ግለሰቦች እንደልባቸው የሚያደናቀፉበትና መንግስትም የመብት ጥያቄ ነው ብሎ የሚያልፍበትና መፍትሄ የማያበጅበት አካሄድ የ “ለውጥ” ነው ብሎ ማመን አስቸጋሪ ይሆናል::

በትክክለኛው መርህ ላይ መንዝና ማስተዋል ከተቻለ የአስተዳደሩን ስራ የሚሰራው የመንግስት አካል የዜጎችን ጥቅምና ክብር የሚያስከብሩ መሠረታዊ ስራዎችን ለመስራት ዳተኛ የሆነበትን አካሄድ ስንመለከት የእልህና የመብት ጉዳዮች ውላቸው እንደጠፋ የሚያሳየን ሲሆን፣ በዜጎች ላይ ደግሞ የስጋት ደመና እንዲያጠላባቸው መንገድ ከፍቷል::

በመሰረቱ የግልን ስጋት ወደ ሌሎች የማስተላለፍ ተፈጥሯዊ ባህሪይ የሚገነባና የሚያድገው ሠሚ ጆሮና ተቀባይ ህሊና ባለበት ሁኔታ ውስጥ ነው:: ሠሚ ጆሮና ተቀባይ ህሊና ከሌለ ሥጋት ከቁብ አይቆጠርም:: ይህ ማለት ግን ሰብዓዊ ፍጡር ከስጋት የፀዳ ህይወት ይኖራል ማለትም አይደለም:: ነገር ግን ከትልቅ ወደ ትንሽ ወይም ከላይ ወደታች የሚፈስ የሥጋት ጅረት ግን መገደቢያም ሆነ መመለሻው አቅምን ይፈትናል::

በለውጡ መከሠት ተስፋ ያደረገው ዜጋ ባልጠበቀው መልኩ ወደ ባሰ የጎሠኝነት ማጥ ውስጥ መግባቱን ያስተዋለው በዕውቀት ውስጥ ሆኖ ነው ማለት ይከደብዳል:: ምክንያቱም ህዝቡ በማናቸውም ግዜ አብሮ በመኖር ውስጥ ያለውን አንድነትና መተሳሰብ እንዲዘነጋ የተደረገው የራሱ ፍላጎት ሆኖ ሳይሆን፣ ከላይ ወደታች እንዲፈስ በተደረገ የሥጋት ጎርፍ መሆኑን የሚያሳዩና አሁንም ድረስ ያልነጠፉ የአብሮ መኖር ልማዶቹ ዕውነታዎች ማረጋገጫዎች ናቸው:: ሌላው ቀርቶ የመፈናቀሉና የመሰደዱ ሠለባዎች የሆኑት ዜጎች እንኳን አፋቸውን ሞልተው የሚናገሩት አብረው ከኖሩት ማህበረሰብ ጋር አንዳችም ግጭትና ፀብ እንደሌላቸው መሆኑ ከጀርባ ያለው አንድነትን የማዳከምና የመከፋፈል ሴራ ከወያኔ ሲወርድ ሲዋረድ መጥቶ በለውጡ እንቅስቃሴ ውስጥም ሠንኮፉ እንዳልተነቀለ የሚያሳየን ይሆናል::

ሥጋት የሚነጨው በራስ የመተማመን ስሜት ሲጠፋና ፍርሃት ውስጣችን ሲነግስ በመሆኑ ዜጎች ራሳቸውን በዚህ አረንቋ ውስጥ አስገብተው ራሳቸውን ለመከላከል በሚል ወደ ሌላ አቅጣጫ እንዲጓዙ በማድረግ የታቀደው ዲሞክራሲያው ለውጥ እንዳይከሠት ግዜ ሰጥተው የሚሰሩ ኃይሎች መኖራቸው ግልፅ ነው:: ይሄ ደግሞ ጥቅሞቻቸው የተነኩባቸው ወገኖች በገንዘብም፣ በቃልም፣ በተግባርም የሚደግፏትና የሚያቀጣጥሉት እሳት ለመሆኑ መስካሪ አያሻውም::

በተለያዩ አከባቢዎች የሚፈጠሩት ግጭቶችም ከመብት ጥያቄ ጋር እንዲቆራኙ የመዳፈጋቸው ነገር እጅግ አሳፋሪና ለውጡን የመሸንቆጫ መሣሪያ ተደርጎ መወሰዱ ምን ያህል የህግና የፍትህ መርሃችን እንደተናጋ የሚያሳየን መስታወት ሆኗል:: የዜጎች መብት በህገ መንግስቱ በጉልህ ተቀምጦ ሳለ ዛሬ ላይ ለውጡን ተንተርሶ በሌላ አቅጣጫ እንዲተረጎምና በዜጎች ላይ ጫና እንዲያሳድር ማነሳሳቱ አገርን ለመለወጥ ህልም ያላቸውን ሁሉ ሊያሳስባቸው፣ በጥንቃቄ እንዲመለከቱት የሚያስገድዳቸው የለየለት የፀረ ሠላምና አንድነት ሀይሎች አጀንዳ መሆኑን ማመን ያስፈልጋል::

ድብቅ አላማዎች ያሏቸውና መገለላቸውን አምነው መቀበል የተሳናቸው የወያኔ ተላላኪዎችና አስፈፃሚዎች የለውጡን እንቅስቃሴ ለማጨናገፍ ዛሬም ቢሆን በያሉበት ሆነው (በድርጅታቸው መዋቅር የመንግስት ሥልጣን ላይ) ወዲህ ደጋፊ በመምሰል ወዲያ ደግሞ አገሪቱንና ዜጎቿን ወደ መበታተንና ወደቀደመው አምባገነናዊ ሥርዓት ለመመለስ የቻሉትን ያህል እየታገሉ መሆናቸው ግልፅ ነው:: ምክንያቱም እነሱ የሥጋት ሰለባ ሆነዋልና::

በውስጣቸው የነገሰውን የፍርሃትና የመገለል ስሜት ወደ እልህና የመብት ጥያቄ እንዲለውጠው ህዝቡን ሲያስጨንቁት መገኘታቸው ብዙም አያስደንቅም:: በእነርሱ ብቻ ሳይሆን በሠዎች አጠቃላይ ባህርይ ላይ የሚከሰት ተፈጥሯዊ ክስተት ነውና:: ምክንያቱም ያሠብነውና ያቀድነውን ወይም ደግሞ የምንሰራውን ስራ በተግባር ማረጋገጥ ሲያቅተንና አካላዊም፣ መንፈሳዊም ስንፈትና ድካም ሲጫነን ድክመታችንን የብቻችንን አድርገን ለመቀበል አቅሙን እናጣለን:: ስለዚህ ያለን አማራጭ ሌሎችን ተከታይ በማድረግ የሥጋት ጠበል መርጨትና አጋዥና ደጋፊ (አማኝ) ማበርከት ዋነኛ ስራችን ይሆናል::

አሁን በገሃድ እያየነው ያለነው ይሄንኑ ነው:: ነገር ግን እነዚህ የመቆስቆሻ መሳሪያዎች ከተዳፈነው እሳት ጋር አመድ ለብሰው የቆዩ እንጂ አዲስ የተፈጠሩ አለመሆናቸውም መታወቅ ይኖርበታል:: የለውጡም ዓላማና እደርስበታለሁ የሚለው ግብ የተዳፈነውን እሳት አውጥቶ ማቀጣጠል ሳይሆን ሳንዴና ለመጨረሻ ጊዜ አውጥቶ በማጥፋት እሳቱን ከማቃጠያነት ወደ ብርሃንነት የመቀየር ቁርጥ ውሣኔ ማሳያ እንደሆነ ሊያሳምነን ይገባል::

እርግጥ ነው በብዙ ድክመታችን ወቅት ረዳት መፈለግና መሻት የሚነቀፍ ተግባር አይደለም:: ነገር ግን ደጋፊዎቻችንን የምናመጣውና አብሮን እንዲጓዝ የምናደርገው ለምን ዓላማ ነው? ለሽንፈታችን መሸፈኛ ወይስ ለሠውየው ካለን አዘኔታ ተነስተን? ይህ አካሄድ በተራ የዕለት ከዕለት ኑሯችን ውስጥ ቢከሰት ከቁጥር ላናስገባው እንችል ይሆናል:: ሆኖም አገርን ያህል እየመራን ነው ለሚሉና ለዜጎች መብት መከበር እሰራለሁ ብለው ድምፁን ጭምር ነጥቀው ከስልጣን ማማው ላይ ከተፈናጠጡት ሠዎች ተርታ ሲተገበር ማየት በጣም ያምማል::

የለውጡ መንግስት አሁንም የፊት የፊቱን ሲሮጥበት የጉያውን ግን እየዘነጋው እንደሆነ ያየንባቸው “የለውጡ እንቅፋቶች”ን ጊዜ ሳይሰጥ ሊመነጥራቸውና ቃል ለገባለት ህዝብ ኪዳኑን መፈፀም እንዳለበት እንደዜጋ ማሳሰቡ ኩነኔ አይሆንም:: ዜጎች ሁለንተናዊ መብቶቻቸው ከቃል ባለፈ በተግባር ተተርጉመውና በህገ - መንግስቱ የተሰጣቸውን ሙሉ መብት ተላብሰው መኖር ሲችሉ ነው የኢትዮጵያዊነት ዝማሬውም ሆነ ትንሳኤው ዕውን የሚሆነው::



ከናፍቆት ገለው
**አሜሪካ**

# የአዲስ አበባን ነገር . . .

## የሰው ልጅ ያካለፈበት ከዲስ ፈተና ከልገጠመኝም



በአንድም በሌላ መልኩ ከወሰን አከላለል እና ከማንነት ጋር በተያያዘ በየአቅጣጫው የሚነሱ አለመረጋጋቶች፣ የተጀመረውን የለውጥ ሂደት በተደጋጋሚ ሲያንገዳግዱት አይተናል። በዚህ ሰሞን ከአዲስ አበባ ጉዳይ ጋር በተያያዘ የተፈጠረውን ትንቅንቅ ያህል ግን ለውጡን በኃይል የናጠ ፍጥጫ ያጋጠመን አልመሰለኝም። አዲስ አበባን በተመለከተ የሚነሳው አለመግባባት፣ መሰረታዊ የሀሳብ ልዩነት ያዘለ መሆኑ የሚካድ አይደለም። ሆኖም፣ ሁኔታው ወደ መጋጋል የማደጉ ምክንያት ከሀሳብ ልዩነቱ ግዝፈት የሚነሳ ነው የሚል እምነት የለኝም። በእኔ እይታ፣ ልዩነቱን ወደ አልተፈለገ መካረር እንዲያመራ ትልቁን ሚና የተጫወተው፣ በሁሉም ወገን ያሉ የፖለቲካው ተዋናዮች የተያያዙት ከራእይ ይልቅ ቁጣ እና እልኽ የሚዘውረው ፖለቲካ ነው። ነገሩን አርግቦ፣ ለውጡን ለመታደግም፣ ፈር የለቀቀውን ግብ ግብ ወደ ተረጋጋ ወይይት መግራት ወሳኝ ይሆናል።

በአዲስ አበባ ዙርያ የተቀሰቀሰው ውጥረት፣ በአንድ ቀን የፈነዳ አይደለም። ከለውጡ ማግስት ጀምሮ፣ የተለያዩ ክስተቶችን ታክኮ ሲንተከተክ የከረመ ነው። ወደ ኋላ ተመልሰን ካየን፣ በቡራዮ የደረሰውን ጥቃት ያስተናገድንበት አግባብ፣ ነገሮች ባልተፈለገ አቅጣጫ እንዲፈሱ አሉታዊ እርሾ የጣለ አንዱ አጋጣሚ ይመስለኛል። አደጋ እንደ አያያዙ ነው። ወይ ያሰባስባል ወይ ይበታትናል። የቡራዮ ጥቃት፣ አላሰባሰበንም። በአደጋው ማግስት፣ ጥቃቱን በአንድ ድምጽ ከማውገዝ እና ለተጎጂዎቹ በሕብረት ከመድረስ ይልቅ፣ የጥቃቱ መንስኤ እከሌ የሚባል ግለሰብ ቀስቃሽ ንግግር ነው፣ ጥቃቱን ያደረሰው በመደመር ስም ሀገር ውስጥ የገባ እንደዚህ የሚባል ቡድን ነው። በሌላም በኩል፣ የእኛን ስም ለማጠልሸት እንዲህ የተባለ ቡድን ያቀናበረው አደጋ ነው እና በመሰል መወነጃጀሎች ተጠመደን ነው ያሳለፍነው። ግለሰቦች ወይም ቡድኖች የሚያደርጉት ቅስቀሳ ለጥቃቱ መንስኤ ሆኗል የሚል እምነት ካለ፣ መፍትሄው፣ ሕብረተሰቡ ውስጥ ለጠብ እና ግጭት እድል የሚሰጥ ድባብ እንዳይሰፍን አብሮነትን የሚያንጽ ስራ መስራት ነው። በተረፈ፣ ቀጥተኛ እና የሚያስተማምን መረጃ በሌለበት፣ ተጠያቂው ይሄኛው ወይም ያኛው ቡድን ነው የሚል መረጃ በሚዲያ ማቀበል ህዝብን ስሜታዊ ለሆነ አጸፋዊ መልስ በማነሳሳት ለማያባራ የግጭት አዙሪት በር መክፈት ይሆናል። እዛም ካላዳረሰን፣ መወነጃጀሉ የሚጋብዘው አላስፈላጊ እሰጣገባ በቀጣይ የሚገጥሙ ልዩነቶች የሚስተናገዱበትን መንፈስ ያሻክራል።

የቡራዮን አደጋ ተከትሎ፣ በአንዳንድ የኦሮሚያ ህንጻዎች ላይ የተሞከሩ ጥቃቶች፣ በአዲስ አበባ ጎዳና ላይ የግለሰቦችን ስም እየጠሩ ይውጣልን ሲሉ የተሰሙ ድምጾች፣ አግባብ ያልነበሩ እና ውግዘት የሚገባቸው ድርጊቶች ነበሩ። አንዳንድ አክቲቪስቶች እና ጋዜጠኞች፣ በአደጋው ዙርያ ሲያቀርቡት የነበረው ጥንቃቄ የጎደለው ትንተና፣ ለክስተቱ አስተዋፆኦ አድርጎም ይሆናል። ይህ እንዳለ ሆኖ፣ በወቅቱ ድርጊቱን ለማውገዝ፣ አምስት የኦሮሞ የፖለቲካ ፖርቲዎች በህብረት ያወጡት መግለጫ፣ በስሜታዊነት እና በግርግር መኃል፣ ቁጥራቸው እዚህ ግባ በማይባል ግለሰቦች ተሳትፎ የተፈጠረን ክስተት ወደ "ኦሮሞነትን ከአዲስ አበባ የመግፋት፣ ኦሮሞ ጠል እንቅስቃሴ" አድጎ የቀረበበት ሁኔታ ሚዛን የሳተ ነበር ባይ ነኝ። የኦሮሞ የአዲስ አበባ ባለቤትነት፣ መግለጫው አስረግጦ ካለፈው መልክቶች ዋናው ነበር። መግለጫው አያይዞም ሌሎች ብሔሮች አብረው መኖር እንደሚችሉ ያስቀምጣል። በወቅቱ፣ አቶ በቀለ ገርባ ከኤልቲቪ ጋር ባደረጉት ቃለመጠይቅ፣ ይህን አቋም በመግለጫው ውስጥ ማካተት ለምን እንዳስፈለገ በሰጡት ማብራሪያ፣ በአዲስ አበባ ውስጥ የኦሮሞ መሰረት ባላቸው ድርጅቶች ላይ በተቃጣው ጥቃት ምክንያት፣ መሬቱ የማን እንደሆነ ማስታውሱ አስፈላጊ ሆኖ ስላገኙት መሆኑን ገልጸዋል።

የአዲስ አበባ ባለቤትነት ጉዳይ ሌላ ርእስ ሆኖ፣ አዲስ አበባ ኦሮሞነትን ትገፋለች የሚል ስጋት ግን ትክክለኛ እይታ ነው ብየ አላስብም። ለውጥ ላይ እንደመሆናችን ፖለቲካችን የተረጋጋ አይደለም። ባልተረጋጋ ፖለቲካ ግጭቶች ይኖራሉ። ፖለቲካችን ብሔር ተኮር እንደመሆኑ ግጭቶቹ የብሔር መልክ መያዛቸው አያስገርምም። ሆኖም እነዚህ ግጭቶች ምንጫቸው ግዚያዊ ፍራቻ እና ቁጣ እንጅ ስር የሰደደ ጥላቻ አይደለም። በአንድነት፣ በስምምነት መንፈስ ውስጥ ስንሆን፣ ለኦሮሞነት እንግዳ ያልሆነው አዲሳቤ አይደለም፣ የባህርዳር ህዝብ፣ ለማ መገርሳ አማራ ክልል በሄዱበት ወቅት፣ የእኛስ ልጆች ለምን ኦሮምኛ አይማሩም፣ የኦሮሞ ባህል ማእከል ከተማችን ውስጥ ይገንባልን የሚል ጥያቄ ሲያስተጋባ አይተናል። የኢትዮጵያ ህዝብ ባህል፣ ቋንቋ እየተወራረሰ ነው የኖረው። አንድነቱ እስከተጠበቀለት ድረስ ይህን አጠናክሮ መቀጠል አይገደውም። ኦሮሞነት አዲስ አበቤነት ውስጥ ትልቅ አሻራ ያሳረፈ ማንነት ነው። ወደፊትም አዲስ አበባ ኦሮሞነትን ይበልጥ ተላብሳ እንዳትቀጥል የሚቸግራት ነገር አይኖርም። ነገር ግን፣ አያት ቅድመ አያቶቻችን በጋራ አቅንተው፣ በጋራ ጠብቀው ባወረሱን ሀገር፣ የሁሉም ኢትዮጵያዊ መዲና በሆነችው አዲስ አበባ ላይ፣ አንዱን ባለቤት አድርጎ፣ የተቀረውን በገዛ ሀገሩ የመኖሪያ ፈቃድ የሚሰጥ አስተሳሰብ አብሮነትን የሚረዳ አይደለም።

በከንቲባው ሹመት ዙርያ የሚነሳው ውዝግብ፣ ሌላው የአዲስ አበባን አጀንዳ አለቅጥ የወጠረው ጉዳይ ይመስለኛል። በመጀመርያ ደረጃ አዲስ አበቤነትን የሰራው ኢትዮጵያዊነት ነው። የአዲስ አበባ ከንቲባ ለመሆን ኢትዮጵያዊ መሆን በቂ መስፈርት ነው። ለኔ ከዚህ በተቃራኒ የሚሰነዘሩ አስተያየቶች፣ አዲስ አበቤነትን አጥብቦ ከመረዳት የሚመነጩ ►

ሆነው ነው የሚታዩኝ። የከንቲባው ሹመት ህጋዊነት ላይ የሚነሱ ቅሬታዎች፤ በተናጠል ከመዘንናቸው፤ አሳማኝ ሆነው ሊታዩ ይችላሉ። አጠቃላይ የኢትዮጵያ ፖለቲካ አውድ ውስጥ ከትተን ካየናቸው ግን ያን ያህል ትርጉም የሚሰጡ አይደሉም። አሁን ባለው ኢሕአዲጋዊ የመንግስት ስርአት፤ ከንቲባዎች ይሾማሉ እንጅ አይመረጡም። ይሄ ለአዲስ አበባ የተለየ አይደለም። የሁሉም የኢትዮጵያ ከተሞች ነባራዊ ሁኔታ ነው። ወደፊት ህዝብ መሪዎቹን በቀጥታ የሚመርጥበት ስርአት እንዲኖር መታገል ተገቢ ነው። ነገር ግን፤ አንድ ሀገር ውስጥ ዲሞክራሲ ወጣ ገባ ሆኖ ሊተገበር የሚችልበት ሁኔታ የለም። አዲስ አበባ ከንቲባዋን የምትመርጥበት ቀን፤ የጅማ ወይም የጎንደር ነዋሪዎች ከንቲባቸውን በቀጥታ ከሚመርጡበት ቀን ቀድሞ ሊመጣ አይችልም። ይሄ እውን የሚሆነው ደግሞ፤ በሀገር ደረጃ ስምምነት ፈጥሮ አስተማማኝ ዲሞክራሲ መዘርጋት ሲቻል ብቻ ነው። መሰረቱ ሲስተካከል ሁሉም ነገር ቦታ ቦታውን ይይዛል። በአንጻሩ እንዲህ አይነት ቁንፅል ነገሮች ላይ መቸንከር፤ ወሳኙን ዲሞክራሲያዊ ተቋማት የመገንባት አጀንዳ ወደ ኋላ እየገፋ በምርጫ በተመረጠ መንግስት የምንተደደርበትን ግዜ የባሰውኑ ያርቀዋል።

መንግስት ህግ የማክበር እና የማስከበር ኃላፊነቱን እንዳይዘነጋ የማያቋርጥ ጫና መፍጥር አስፈላጊ ነው። አግባብነት የሌላቸው ድርጊቶች ሲፈጠሩም እርምት መጠየቅ ይገባል። ከዛ ባለፈ ግን፤ የመንግስትን አስተዳደራዊ ኃላፊነት የሚጋፋ ማንኛውም አይነት እንቅስቃሴ ውስጥ መግባት ትክክል አይሆንም። የኢሕአዲግ ስልጣን ከምርጫ ኮሮጆ እንዳልመጣ፤ ሁሉም የሚያውቀው እውነት ነው። የኢሕአዲግን አስተዳደር እውቅና የመስጠቱ አስፈላጊነት፤ ውክልና አለው የለውም ከሚል ክርክር የሚነሳ አይደለም። ተወደደም ተጠላም፤ ባለፉት ሦስት አስርት አመታት ኢሕአዲግ ሀገር ሆኖል። አስተሳስሮ ያኖረን ሀገራዊ አንድነት ከምንግዜውም በላይ በላላበት፤ ምንም አይነት ነጻ መንግስታዊ ተቋማት በሌሉበት፤ ሀገረ መንግስቱ ተደግፎት የቆመው ብቸኛ ባላ የኢሕአዲግ መዋቅር ነው። የተናደው አንድነታችን በቅጡ ሳይጠገን፤ የዲሞክራሲ መሰረተ ልማት ሳይዘረጋ፤ ኢሕአዲግ በዚህም በዚያም ተገዝግዞ ህልውናውን ቢያጣ፤ ሀገር በላያችን ላይ ላለመደርመሱ እርግጠኞች አይደለንም። እየዘነጋን ካልሆነ፤ ኢሕአዲግ ከስሩ ተነቅሎ ከመውደቁ በፊት፤ ከውስጡ ተራማጅ ቡድን ወጥቶ፤ ያለብዙ እንገጭ እንጓ የለውጥ ምዕራፍ ሲከፈት፤ እንደዛ በደስታ ያሰከረን ቁምነገር ከዚህ የሀገር መፍረስ አደጋ እፎይታ ማግኘታችን ነበር።

በመንግስት አካላት በኩል የታዩ ክፍተቶች፤ የአሰራር ግልጽነት መጉደል፤ እንዲሁም የደህንነት ስጋት የሆኑ የጎዳና ላይ እንቅስቃሴዎችን ከመከላከልም ሆነ ከመኮነን አንጻር የነበረው ቸለተኝነት፤ በአዲስ አበባ ዙርያ ለተነሱ አለመግባባቶች መጋጋል የራሱ አስተዋፅኦ ነበረው። ሆኖም፤ መንግስት በነጻ ሀሳብን የማሰማት እና በሀገራችን ጉዳይ ላይ የመሳተፍ መብታችንን እስካላገደ ድረስ፤ አሁንም የሚሻለው ተቀራርቦ፥ መንግስት አሰራሩን ለህዝብ ቅርብ እንዲያደርግ፤ የተወሰኑ ግለሰቦችም ሆኑ ቡድኖች ከህግ ውጭ እንዳሻቸው ትእዛዝ ሊያስተላልፉ የሚችሉበትን እድል እንዲዘጋ፤ ሕብረተሰቡ በአግባቡ ቅሬታውን አሰምቶ እርምት የሚያገኝበትን አሰራር እንዲያመቻች፤ ጸጥታ የማስከበር ኃላፊነቱን እንዲወጣ፤ አጠቃላይ በህዝብ እና በመንግስት መኃል አለመተማመን የሚፈጥሩ ክፍተቶችን እንዲያጠብ በትብብር መስራት ነው። የኢሕአዲግ የለውጥ ኃይል፤ ከተለመደው የመገፋፋት ፖለቲካ ወጥቶ፤ ለጋራ አላማ ተደጋግፎ ለመቆም፤ ተቀናቃኝ ሀሳቦችን አስታርቆ ሀገራዊ አንድነትን ለማነጽ


የአዲስ አበባን ጉዳይ መጠላለፍ ውስጥ ያስገባው አንዱ ምክንያት፤ ነገሩ ከአጠቃላዩ ፖለቲካ በጣም ተነጥሎ የተራገበበት ሁኔታ በመፈጠሩ ይመስለኛል። እይታችን አንድ ነገር ላይ ያለቅጥ በተተከለ ቁጥር ሚዛን እንስታለን። ይህ እንዳይሆን አካባቢያዊ ስጋቶችን ለመቅረፍም ሆነ ፍላጎታችንን ለማስፈጸም የምንሄድበት መንገድ ከሀገራዊው ዲሞክራሲያዊ ስርአት የመገንባት ራእይ ጋር ማናበብ ጠቃሚ ይሆናል። ዙሪያ ገባውን ያማከለ እይታ፤ ለችግሮቻችን ትክክለኛ እና ዘላቂ የመፍትሄ አማራጮችን የማየት እድላችንን ያሰፋዋል።

ያሳየው ቁርጠኝነት ብዙ እርቀት አራምዶናል። ወደፊትም በኢትዮጵያ ፖለቲካ ውስጥ የያዙትን ማዕከላዊ ሚና አስጠብቀው ለመቀጥል፤ ሚዛን የሚያሳጣቸውን የውስጥም የውጭም ችግር አጥርተው፤ የመጡበትን መንገድ አጠናክሮ መቀጠል ከነሱ የሚጠበቅ ይሆናል።

አዲስ አበባን ተንተርሶ የሚነሳ ማንኛውም አለመግባባት፤ እራሱን ችሎ የቆመ አይደለም። ከአጠቃላይ የሀገሪቱ ውስብስብ የፖለቲካ ሁነት የሚመዘዝ ነው። የሀገሪቱ ፖለቲካ ከመሰረቱ እየተደላደለ ሲሄድ፤ አዲስ አበባ ተኮር የሆኑ ልዩነቶችን መፍታት ቀላል ይሆናል። በተቃራኒው አዲስ አበባ የሀገሪቱ ፖለቲካ እምብርት እንደመሆኗ፤ አዲስ አበባ ላይ ነገር ከተበላሸ አጠቃላዩን የሀገር ፖለቲካ ቅርቃር ውስጥ የመክተት አቅም አለው። ጥንቃቄ የሚያስፈልገው ለዚህ ነው። የአዲስ አበባን ጉዳይ መጠላለፍ ውስጥ ያስገባው አንዱ ምክንያት፤ ነገሩ ከአጠቃላዩ ፖለቲካ በጣም ተነጥሎ የተራገበበት ሁኔታ በመፈጠሩ ይመስለኛል። እይታችን አንድ ነገር ላይ ያለቅጥ በተተከለ ቁጥር ሚዛን እንስታለን። ይህ እንዳይሆን አካባቢያዊ ስጋቶችን ለመቅረፍም ሆነ ፍላጎታችንን ለማስፈጸም የምንሄድበት መንገድ ከሀገራዊው ዲሞክራሲያዊ ስርአት የመገንባት ራእይ ጋር ማናበብ ጠቃሚ ይሆናል። ዙሪያ ገባውን ያማከለ እይታ፤ ለችግሮቻችን ትክክለኛ እና ዘላቂ የመፍትሄ አማራጮችን የማየት እድላችንን ያሰፋዋል።

ዲሞክራሲያዊ ስርአት ለማቆም ስንሞክር እኛ የመጀመርያዎቹ አይደለንም። የሰው ልጅ ያላለፈበት አዲስ ፈተና አልገጠመንም። መሸናነፍ እንደማንችል በግዜ ተረድተን ለመገናዘብ መነጋገር ብንችል፤ ከመካሰስ ይልቅ ያላግባባንን ነገር ከምንጩ ተረድተን መፍትሄ ለማፈላለግ ብንተጋ፤ መላ የማይገኝለት ነገር አይኖርም። እንደ እኔ ይህን እንዳናደርግ እንቅፋት እየሆነብን ያለው እልኸ እና ቁጣ የሚያጠቃው ፖለቲካችን ነው። በድርድር ፍላጎቶቻችንን ለማጣጣም፤ ስጋታችንን ለመቅረፍ የሚያስችል ጤናማ የመስተጋብር ዘይቤ ስላላዳበርን፤ ለሁሉም ችግር መልሳችን ቁጣ ሆኗል። በዚህም በዛም የሚወረወሩ ኃይለ ቃሎች፤ መግለጫዎች፤ ከይዘታቸው ይበልጥ ድምጸታቸው ይጎረብጣል። "ለተቃራኒ ቡድን" የመልስ ምት ከመሆን ተሻግረው፤ አለመግባባቱን ከማስታረቅ አንጻር ሊኖራቸው የሚገባው ዋጋ የታሰበበት አይመስልም። በዚህ ምክንያት አንዱ የሌላውን እልኸ እና ቁጣ ያለማቋረጥ የሚቀሰቅስበት አዙሪት ውስጥ እየገባን ነው። ከዚህ አዙሪት ሰብሮ ለመውጣት ስሜታዊነትን አሸንፈን፤ አካሄዳችንን ለራእይ የማስገዛት አቅም መፍጠር ይኖርብናል። መለያየትን በመቀራረብ፤ ፉክክርን በመተጋገዝ መንፈስ ለማሸነፍ ቁርጠኛነቱ ያስፈልገናል። ቀላል አይደለም። ነገር ግን ሁለት ወዶ አይሆንም። ቁጣ ሀገር አይገነባም። ሀገር ይኑረን ካልን፤ ወደ መግባባት የሚያደርሰንን መንገድ ለይተን መያዝ ግድ ይላል።

# የአበሻው የሙዚቃ ንጉሥ ትውስታ




በኢትዮጵያ የሙዚቃ ታሪክ ውስጥ ዘመን የማይሽረው ንግስናን የተጎናፀፈው የሀበሻው የሙዚቃ ንጉስ ዶ/ር አርቲስት ጥላሁን ገሠሠ ልክ የዛሬ 10 ዓመት በሚያዝያ ወር ነበር ህይወቱ ያለፈው፡፡ ምንም እንኳን ሀዘኑ የብዙዎቹን አድናቂዎቹን ቅስም የሰበረ ቢሆንም፤ ንጉሱ ሙሉ ክብርን የተጎናፀፈና አይረሴ የሆነ የሽኝት ዝግጅት ነበር የተደረገለት፡፡ ሥራዎቹ እስከ የማይባል ጊዜ ድረስ ሲደመጡ ይኖራሉ፡፡

የዶ/ር አርቲስት ጥላሁን ገሠሠን ህልፈት አስመልክቶ የግዮን እህት መጽሔት በሆነችው "ዕንቁ" መፅሄት በወቅቱ ተዘጋጅቶ ከነበረው ልዩ ዕትም ላይ ለትውስታ እንዲሆን የሚከተለውን አቅርበናል፡፡

መስከረም 17/1933 ዓ.ም በዕለተ መስቀል በአዲስ አበባ ልዩ ስሙ ጠመንጃ ያዥ እየተባለ በሚታወቀው ሰፈር እትብቱ ከሙዚቃ ጋር የተቆራኘው ውዱ ጥላሁን ገሰሰ ተወልዶ እልል ተባለ፡፡ ጠመንጃ ያገቱ ደስታውን በእሩምታ ተኩስ አበሰረ፡፡


እናቱ ወ/ሮ ጌጤ ጉርሙና አባቱ አቶ ገሠሠ ወ/ኪዳን ቀዳሚም ተከታይም የሌለውን ልጃቸውን ወዲያው በስምምነት "ጥላ መሸሸጊያ ተወለደልን" ሲሉ ጥላሁን በማለት ስም አወጡለት፡፡

ሕፃኑ ጥላሁን ገሠሠ በእናቱ እቅፍ አዲስ አበባ የቆየው ለስድስት ወራት ያህል ብቻ ነበር፡፡ የአባቱ እናት የሆኑት እመት ሐበሻ አሊ ይህን የስስት ልጅ እኔ ካላሳደግኩት ብለው ወደመኖሪያ አካባቢያቸው ወሊሶ ወሰዱት፡፡

ዕድሜው ለትምህርት ሲደርስም እዚያው ወሊሶ ግዮን ት/ቤት (ከዓመታት በኋላ ስሙ ተለውጦ ራስ ጎበና ዳጨው አባ ጥጉ) ት/ቤት አስገቡት፡፡

የእናት አባቱ ፍቅር እረፍት ይነሳው የነበረው ሕፃኑ ጥላሁን እስከ አስራ ሁለት ዓመቱ ወሊሶና አዲስ አበባ መመላለስ ስላዘወተረና የሕፃንነት ልቡን ሙሉ በሙሉ ለሙዚቃ በማስገባቱ ለቀለም ትምህርቱ ትኩረት አልሰጠውም ነበር፡፡ በመጨረሻም በ1945 ዓ.ም ወላጆቹን ጥየቃ አዲስ አበባ በመጣበት ወቅት የእናቱና አባቱ ትዳር በመናጋቱ ተበሳጭቶ ወደ ድሬድዋ ኮበለለ፡፡ አያቱም አልሰነፉም አግር በእግር ተከታትለው ድሬድዋ ድረስ በመዝለቅ በኮበለለ በሦስት ወሩ ወሊሶ መለሱት፡፡

ልቡ ያልረጋው ጥላሁን ግን ወሊሶ አርፎ መቀመጥ ስላልቻለ በትሬንታ ኳትሮ የጭነት መኪና ሸራ ውስጥ ተደብቆ አዲስ አበባ ወላጅ እናቱ ዘንድ ከተፍ አለ፡፡ እዚሁ አዲስ አበባ በአጋጣሚው ተመቻችቶለት በውስጡ ሲቀጣጠል የኖረውን የሙዚቃ ፍቅር በሰርጉ ላይ በመዝፈን ተፈጥሮ የለገሰችውን ስጦታ ለእድምተኛው ጆሮ አደረሰ፡፡ የዚህን ታዳጊ ወጣጥ ተስረቅራቂ ድምፅ የሰሙት አንድ የሰፈሩ አዛውንት ከደስታቸው ብዛት የተነሳ



እጁን አንጠልጥለው ሀገር ፍቅር ቴአትር ቤት ወስደው ለክቡር አቶ መኮንን ሀብተወልድ አስረከቡት፡፡

ጥላሁን በሀገር ፍቅር ቴአትር ቤት ግቢ ውስጥ ቆሞ ሁኔታዎችን በአድናቆት እየተከታተለ እያለ በድንገት ከአቶ ኢዮኤል ዮሐንስ ጋር አይን ለአይን ይጋጫል፡፡ አቶ ኢዮኤል ዮሐንስ ከአሁን ቀደም ትርኢት ለማሳየት ወሊሶ ሄደው በነበረ ጊዜ ታዳጊው ጥላሁን የሱዳንኛ ዜማና ባህላዊ ዘፈኖችን ሲጫወት አይተውት እንደነበር ትዝ ይላቸዋል፡፡ ትዝታ ብቻ ሳይሆን አዲስ አበባ መጥተው ሀገር ፍቅር ቴአትር ቤት እንዲቀጠር የመከሩት ምክር ትዝ ብሏቸው "መጣሽ አንቺ ልጅ" ብለው በደስታ

አቅፈው በመሳም ጭናቸው ላይ አስቀምጠው እየደባበሱት በፉጨት "ጥላ ከለላዬ" የሚለውን አዲስ ዘፈን ያንጎራጎሩ ጀመር፡ ከሰዓት በኋላ ይህንኑ ዘፈን ጥላሁን እንዲዘፍነው ተደርጎ በ30 ብር የወር ደመወዝ የሀገር ፍቅር ቴአትር ቤትን መድረክና የሕዝቡን ልብ በዚሁ ዜማ በማሟሸት አንፀባራቂው ኮከብ በሕዝብ ፊት ማብራት ጀመረ፡፡ በማግስቱ ከሰዓት በኋላ "ጽጌሬዳ ነሽ" ተደርሶ ተሰጠው፡፡ ከዚያ በኋላማ ማን ያቁመው፤ ዕንቁው ጥላሁን ከዕለት ወደ ዕለት የደምፁ ውበት እየፈካ፣ በሰውነቱ እንቅስቃሴ ተመልካቹን እየማረከ፣ በተዋቡ አይኖቹ እያማለለ በመዝፈንና ቴአትሮች ላይ በመተወን ከ1946 — 1948 ዓ.ም የሀገር ፍቅርን መድረክ ነገሰበት፡፡

ከ1948 — 1978 ዓ.ም ወደ ክብር ዘበኛ የሙዚቃ ክፍል በመዘዋወርም ያንኑ የኮከብነት ቀለሙን በማድመቅ ከሦስት መቶ የሚበልጡ ዜማዎችን ተጫውቷል፡፡ጥላሁን ክብር ዘበኛ የሙዚቃ ክፍል የተቀጠረው በሲቪል ሠራተኝነት ቢሆንም፣ ከወታደሮች ጋር ለብዙ ዓመታት ስለሰራ በጥሩ ወታደራዊ ዲሲፕሊን የታነፀ ነበር፡፡

በ1960ዎቹ ዓመታት ግርማዊ ቀደማዊ ኃ/ሥላሴ የክቡር ዘበኛ ክፍለ ጦርን ሲጎበኙ የሙዚቃ ክፍሉ ልምምድ ላይ ነበርና የጥላሁንን ድምጽ ሰምተው ወደ ማጥኛ ክፍሉ ጎራ በማለት እንዲህ ሲሉ መከሩት፡-

"ጥሩ የተሰጥኦ ድምፀ አለህ፤ ይህንን እግዚአብሔር የሰጠህን ጥሩ ድምጽ በአልባሌ ሱሶች እንዳታበላሸው፤ ጠብቀው" በማለት ንጉሳዊ ምክር ሰጥተውት ነበር፡፡ከጥር 1/1978 ጥር 30/1982 ዓ.ም ወደ ብሔራዊ ቴአትር ቤት በመዛወርም ለአራት ዓመታት ያህል አገልግሏል፡፡

ድምፃዊ ጥላሁን ገሠሠ ከግማሽ ክፍለ ዘመን በላይ በቆየበት ሙያ ውስጥ ከ400 በላይ ዘፈኖችን ተጫውቷል፡፡ እነዚህኑ አይጠገቤ ዜማዎቹን ሦስት ያህል ትውልድ እየተቀባበለ ሲዝናናባቸው፣ ሲማርባቸው ሲፅናናባቸውና ሕይወትን ሲተረጉምባቸው ኖሯል፡፡ ወደፊትም እንዲሁ ይቀጥላል፡፡

ክቡር ዶ/ር አርቲስት ጥላሁን ገሠሠ ይህንን መሠል የደመቀ የሙዚቃ ሕይወት የኖረው ሁኔዎች ሁሉ ተመቻችተውለት አልነበረም፡፡ የእናቱ በሰው እጅ መገደልና የገዳዩ ማንነት ያለመታወቅ እጅግ ከፍተኛ የስሜት ጉዳት አስከትሎበታል፡፡ ሚያዚያ 17/1985 ዓ.ም በዕለተ ፋሲካ በሕይወቱ ላይ የተቃጣው አደጋና የጉሮሮው መቆረጥ "በሆድ ይፍጀው" አባባል ተዳፍኖ የቀረ ነው፡፡

ጥር 26/11997 ዓ.ም በደቡብ አፍሪካ አልቪዳል ሆስፒታል በጋንግሪን ሕመም ምክንያት ቀኝ እግሩን ማስቆረጡ፤ ለስሜቱም፣ ለአካሉም ታላቅ ጉዳት ነበር፡፡ ይሄ ሁሉ የሕይወት ፈተናና ውጣ ውረድ ቢያጋጥመውም ለመከራ ሳይበገር፣ ሁሉንም ተቋቁሞ በማሸነፍ፣ አንድም ጋት ቢሆን ከሚወደው ሕዝብ አልራቀም ነበር፡፡ ሁሌም ሕያውነትን በመዘመር ዘመኑን በሙሉ የሕዝብ ፍቅር ►

▶ አትርፎ የኖረው ጥላሁን ገና ብዙ ሲጠበቅና በጉጉት ሲናፈቅ እነሆ ሙያውን አክብሮ ለሕዝብ የኖረው ታላቅ ኮከብ በተወለደ በ68 ዓመቱ ዛሬ ልንሰናበተው ቁርጥ ሆነ፡፡ በአንድ ወቅት ስለ እድሜው ሲናገር እንዲህ ብሎ ነበር፤ "ስለ እድሜ አንድ ነገር መናገር እፈልጋለሁ፤ 100 ዓመት የቤተሰቦቼ ነው፡፡ እኔም መቶውን እንደምደፍን አትጠራጠሩ፡፡ የአባቴ እናት እመት ሐበሻ ዓሊ በ115 ዓመታቸው አረፉ፡፡ የአባቴ አባት ወልደ ኪዳን የኋላዬ ዘ ብሄረ ቡልጋ በ125 ዓመታቸው አረፉ፡፡ መቶ ዓመት የዘሬ ነው ብያለሁና እኔም መቶውን መድፈኔ አይቀርም፡፡ እኛ የኪነት ዘሮች የወይራ ዘር መሆን አለብን እንጂ የብሳና ዘር ልንሆን አይገባም፡፡"

"ሥራዎቹ ይመሰክራሉ፡፡ እሱ ከማንም በላይ ነው፡፡ እሱን ስንሰማ፣ እሱን ስናወድስና ስናደንቅ ኖረናል፡፡ ዘመን የማይሽራቸው ድንቅ ሙዚቃዎችን አበርክቶልናል፡፡ ሁላችንም መሆን ብንችል እሱን መሆን እንመኝ ነበር፡፡ ግን ይህ ከባድ ነው፡፡ ጥላሁን ትልቅ የሙዚቃ ባለውለታ ነው፡፡ እሱን እያዩና እያደነቁ የሙዚቃውን ኢንዱስትሪ የተቀላቀሉና ዛሬ ትልቅ ደረጃ ላይ የደረሱ ሙያተኞችን መመልከቱ በራሱ ምን ያህል የገዘፈ የሙዚቃ ሠው እንደሆነ ያሳያል፡፡"

### ድምፃዊ አያሌው መስፍን

"ማንንም ብትጠይቅ ይሄንን እውነት አይሸሽግም፡፡ አዲስ ሙያተኛ ሲመጣ የሚያበረታታ፣ ምቀኛ ያልነበረ፣ በኪነ ጥበብ ዘርፍ የሚመጣውን ሁሉ ጥልቅ ደረጃ ላይ እንዲደርስ ከመምከር ውጪ የሚያሸማቅቅ ነገር ተነግሮ አያውቅም፡፡ ሰውን በቀና ለመመልከቱ ማረጋገጫው ጥላሁን የማንንም ዘፈን ዘፍኖ አለማወቁ ነው፡፡ የትም ቦታ ሄዶ የራሱን ዘፈን ይጫወታል እንጂ የሰው ዘፈን ሲዘፍን ያየሁበት ቀን ትዝ አይለኝም፡፡ እንደውም እኛ የእሱን ዘፈኖች ወረድ አድርገን እንዘፍናለን፡፡ የእሱን ድምፅ ማውጣት ከባድ ነዋ"

### ድምፃዊ ግርማ ነጋሽ

በፍጥነት ለመድረስና ነገሮችን ለመቆጣጠር ስል ራሴ ነበርኩ መኪናውን የያዝኩት፡፡ ቅርባችን በመሆኑ መጀመሪያ ኦሎምፒ አካባ የሚገኘው ቤተዛታ ነበር የወሰድኩት፡፡ ስሄድ በሩ ተዘጋግቷል፣ ዘበኛው ከፍተውልን ከገባን በኋላ አንዳንድ ሰዎች ብቅ አሉ፡፡ "ዶክተር ጥሩልን፤ ሰው ታሞብናል" ስንል "እስኪ ቆዩ፤ መጀመሪያ ነርሷ ትየው" አሉን፡፡

" እባካችሁ ጥላሁን ገሠሠ ነው፤ በጣም አስቸኳይ እርዳታ ይፈልጋል" ብል የሰማኝ አልነበረም፡፡ ጥግ ላይ የሆነ ዊልቸር አይቼ ራሴ ጎትቼ አምጥቼ፣ ዘበኛው ረድቶን ነው ከመኪና አውርደን ያስቀመጥነው፡፡ ከዚያ በኋላ አንድ ሀኪም መጥቶ ምንም እርዳታ ሳይሰጠው ዝም ብሎ ዊልቸሩን ከወዲያ ወዲህ ይገፋዋል፡፡ ማንኛውም የሕክምና ባለሙያ አንድ ሰው ደክሞ ሲያይ መጀመሪያ እርዳታ መስጠቱ ላይ ነው የሚያተኩረው፤ እዛ በነበሩ የህክምና ባለሙያ ግን ይሄን አልተመለከትኩም፡፡ 24 ሰዓት አስቸኳይ ህክምና እንሰጣለን የሚለው ክሊኒክ ሥራ ላይ ሆኖ ግራ ገብቶኝ "ኧረ አድኑልኝ" እያልኩ ስለምን ጥላሁን ራሱ "ዶክተርዬ መተንፈስ አቃተኝ፣ ትንሽ የምተነፍስበት ኦክስጅን አድርግልኝ፡፡ እያለ ሲለምነው ሌላ ሁለተኛ ዶክተር መጣ፡፡ እሱም እንዲሁ ቆም ብሎ ካየው በኋላ "አስም አለበት?" ብሎ ጠየቀኝ፡፡ እኔም "የለበትም፤ የልብ ችግር ስላለበት እባክህን መጀመሪያ ኦክስጅን ፈልግና ስጠው" ስለው እኔን ጥለውኝ ወደ ትልቁ ቤተዛታ ወደሚያስገባው በር እየሄዱ፣ "ይሄ የልብ ችግር ስለሆነ ጎተራ ጋር የልብ ሕክምና የሚሰጥ ኢንተርናሽናል ክሊኒክ ስላለ ይዘሽው ሂጂ" ብለውኝ ገቡ፡፡

### ባለቤቱ ወ/ሮ ሮማን በዙ

"ጥላሁን እኔ እንዲህ ነኝ ብሎ ራሱን የሚያኩራራ ባይሆንም የሠው ዘፈን ፈፅሞ መጫወት አይፈልግም፡፡ እኔ እስከማውቀው ድረስ ሌሎች የተጫወቱትን ዘፈን ወደ እኔ አታምጡብኝ ነው የሚለው፡፡ ከልጅነቱ አንስቶ ራሴን ሆኜ እገኛለሁ የሚል ታዳጊ ዘፋኝ ነበር፡፡ ከዛ ውጭ እከሌ እንዲህ ስለዘፈነ እኔም ልዝፈን የሚል ነገር አይቼበት አላውቅም፡፡ ይሄን እውነት ደግሞ ማንም ይነግርሃል"

### የግጥምና ዜማ ደራሲ አየለ ማሞ

"የሰማሁት መንገድ ላይ ሆኜ ነው፡፡ ልክ ስሰማ የሆነ አካሌን ያጣሁ ነው የመሰለኝ፡፡ ቅዳሜ ዕለት ከአያሌው መስፍን ጋር በጥላሁን ጉዳይ አውርተናል፡፡ ዕሁድ ዕለት ደግሞ ከአለምነህ ዋሴ ጋር ስለ ጥላሁን ተጫውተናል፡፡ አርብ ማታ ደግሞ ከወይንሸት አስፋው ጋር አንገቱ ስለታረደበት ዕለት አንስተናል፡፡ የፋሲካ ዕለት ማታ ሶስት ሰዓት አካባቢ ቤተሰቡን እንኳን አደረሳችሁ ለማለት ደውዬ ነበር፤ መስመሩ ቢዚ ሆነ እንጂ፡፡ እና ሐረር ትራፊክ መብራት ላይ ቆሜ ስልኬ ጮኸ፤ ሣየው



የእርሱ ቤተሰቦች ናቸው፡፡ ልክ እንዳነሳሁት "አንቺ ትናንት ሞክሬ ሞክሬ" ስል "ኧረ ንጉስዬ ችግር ተፈጥሯል" አለችኝ፡፡ የሮማን እህት ናት፤ "ምንድንነው? ስላት"፤ "ጥላሁን አርፏል" የሚለውን ስሰማ መንገድ ላይ አስፋልቱ መሀል ቁጭ አልኩ፡፡ ትራፊኩ መጥቶ እጄን ይዞ አወጣኝ፡ ፡ በቃ ተነስቼ መጣሁ፡፡ አንተ እንድታየኝ እስከ መቶ አመት እኖራለሁ ነበር ያለኝ አልሆነም፡፡"

### ንጉሴ ታደሰ(የጥላሁን አድናቂ)


## የተረሳው ማዕከል

የታላቁን አርቲስት ጥላሁን ገሠሠ 60ኛ ዓመት የልደት በዓል ለማክበር በ1993 ዓ.ም ተሰባስበው የነበሩ የድምፃዊው የቅርብ ጓደኞች "የጥላሁን ገሠሠ ማስታወሻ አደራጅ ኮሚቴ" የተሰኘ አንድ ቡድን መመስረታቸውን ገልፀው ነበር፡፡ ዛሬ ድረስ ድምፁ አልሰማ አለ እንጂ፡፡ ጥላሁን ገሠሠ በሙያው የቆየበትን 47ኛ ዓመትና 60ኛ የልደት በዓሉን ለማክበር ከተሰባሰቡት መሀል ደበበ እሸቱ፣ ጋዜጠኛ ጌታቸው ደስታ፣ ግርማ ብስራት፣ መርዓዊ ስጦት፣ አብራር አብዶና ሌሎችም ታዋቂ ሰዎች የተካተቱበት "የጥላሁን ገሠሠ ማስታወሻ አደራጅ ኮሚቴ" መስከረም 17/1993 ዓ.ም በተለያዩ ዝግጅቶች የድምፃዊውን በዓል ከማክበር ባሻገር የጥላሁን ገሠሠን የጥበብ ማዕከል ለማቋቋም አቅዶ እንደነበር በይፋ አሳውቆ የነበረ ቢሆንም፣ እስከዛሬም ተግባራዊ ሣይሆን ድምፃዊው በህይወቱ ሊያየው የቋመጠለት ማዕከል ሣይገነባ ተሠናብቷል፤ እስካሁን ማዕከሉ አልተገነባም ማለት ግን ወደፊት ለታላቁ አርቲስት "መታሰቢያ/ማስታወሻ" ማዕከል አይገነባም ማለት አይደለም፡፡

"ጥላሁን በደቡብ አፍሪካው ሆስፒታል እግሩ ከተቆረጠ በኋላ የካቲት 11/1997 ዓ.ም ምሽት ነበር ወደ ሀገር ቤት የተመለሰው፡፡ "እስቲ ደግሞ በአንድ እግሬ ሄጄ ምን እንዳገለግል እንደፈለገ ከፈጣሪዬ ያንን ተዓምር እጠብቃለሁ" ያለው ጥላሁን አውሮፕላን ማረፊያ እንደደረሰ ለቪኦኤው ጋዜጠኛ ሠለሞን ክፍሌ በስልክ ቃለ ምልልስ ከሰጠ በኋላ ለሀገር ውስጥ ጋዜጠኞች የሚከተለውን ብሏቸው ነበር፡፡

‹‹..... ለህዝቡ መጀመሪያውኑ ቃል ገብቻለሁ፡፡ መሞቻዬ እስኪደርስ ከመድረክ አልለይም፡፡ እግሬን ደቡብ አፍሪካ ጥዬ ብመጣም መድረክ ላይ መውጣት ማን ይከለክለኛል? አለበለዚያ ምኑን ልጅ አፈራሁ፡፡ ያሉትን ልጆች ምን ዓይነት ሞራል እሰጣቸዋለሁ? በምን ዓይነት መንገድ ላበረታታቸው እችላለሁ?... ከእኔ በፊት የነበሩት አርቲስቶችን አርማ ይዤ እንደማውለበልብ ሁሉ እነርሱም የእኔን አርማ ይዘው እንዲያውለበልቡ ማሳሰብ አለብኝ፡፡ ውጪ የባከኑት የህዝብ ስጦታዎችና ከውጪ የመጡ መኪናዎችም የቀሩ አሉ፡፡ ይሄ የእኔ ሀብት አይደለም፡፡ የኢትዮጵያ ህዝብ ሀብት ነው፡፡ እኔ ከመከራከሬ በፊት የኢትዮጵያ መንግስት ተከራክሮልኝ ሁሉን ነገር ለባህል ሚኒስትር አስረክቤ እፎይ ብዬ በአንድ ጎኔ ተደላድዬ መቀመጥ ነው የምፈልገው፡፡ ለኢትዮጵያ ያበረከትኩት ታሪክ ምንድን ነው? ቢባል ዋንጫዎች ሌሎችም ነገሮች አሉ፡፡ እነዚያ ሁሉ በክብር ሙዚየም መቀመጥ አለባቸው፡፡ እኛ አገር አልተለመደም እንጂ አርቲስት ከ8 እና ከ9 ዓመት ጀምሮ የሰራበትን ልብሶቹና ቅርሶች የአገራቸው መንግስት ሙዚየም ውስጥ ያስቀምጠዋል፡፡ እኔም ለአገሬ ይህን ባደርግ አንድ መልክ ይይዛል ብዬ አስባለሁ፡፡ ከተሳሳኩ ልታረም እችላለሁ፡፡ አደራችሁን ከጎኔ ተሰለፉ፡፡"

(ድምጻዊ ጥላሁን ገሰሰ)



ከሸዋፈራሁ ኩራቱ ዶ/ር
አሜሪካ

# የተበላሹና ያልገኙናቸው እውነቶች

በጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አህመድ የአንድ አመት ጉዞ የተሳኩት የሚናቁ እንዳልሆኑ ባለፈው ሳምንት ባቀረብኩት ጽሁፍ ለማስቃኘት ሞክሪያለሁ፡፡ ግን በመንግሥትነት ደረጃ የተሠራውና የተበላሸውን ስንመለከት የተበላሸው ሚዛን ይደፋል፡፡ እነዚህን የተበላሹ ነጥቦችና ሌሎች ጉዳዮችን ደግሞ ዛሬ እንመለከታቸዋለን፡፡ በመንግስት ደረጃ ለተበላሹት ነገሮች ምክንያቶቹ፤-

1ኛ የሰበሰቧቸው በአብዛኛው ያልጸዳ እጅ ባለቤቶችን፣ አማካሪና ደጋፊ አድርጎ መያዝ፡፡

2ኛ የህግ አውጪውም ሆነ አስፈጻሚው አንዱን አባርሮ ሌላውን በተመሳሳይ ሁኔታ መተካት፡፡

3ኛ አምናቸዋለሁ የሚሏቸው ሰዎች የሚሰጧቸውን እያነሱ መሾምና ቲፎዞን ማዳመጥ፡፡

ስለአንደኛ አመት የጠቅላይ ሚኒስትርነት ዘመን፤ እርሳቸው ከቀድሞ ጠቅላይ ሚኒስትር ከአቶ ኃይለማሪያም ደሳለኝ ደካማውን ሥልጣን ከተረከቡ ወዲህ ያልተሳኩ ጉዳዮች የገደል ያህል ናቸው፡፡ በመጀመሪያ ጠ/ሚኒስትር እንዲሆኑ ያደረገው የኦሮሞ ወጣቶች ቄሮ እንቅስቃሴ ብቻ አይደለም፤ የመላው የኢትዮጵያ ህዝብ እንቅስቃሴ ነው፡፡ ቄሮ ብቻ አይደለም በደቡብ የሲዳማ ኤጀቶ፣ በጉራጌ ዘርማ፣ የአፋር ወጣቶች ዱኪሂና፣ በአማራው ፋኖ፣ እና ሌሎችም በየክልሉ ቡድን በቡድን እየሆኑ ከመንግስት ሥልጣን በላይ መንግሥትን እየመሩ መገኘታቸው ዜጎችን ስጋት ላይ ጥሏል፡፡ ይህ የነውጠኞች ቡድን በአሁኑ ጊዜ እየተመራ ያለው በማን ነው? ለሚለው መልሱን መንግሥት ብቻ ነው የሚያውቀው ቢባል ስህተት ነው፡፡ የትውልድ ሥነ-ምግባር ብልሹነት ይሉታል ይህ ነው፡፡

ክቡርነታቸው ወደ ውጭ አገር በመጡ ጊዜ "ፖለቲካችሁን ይዛችሁ እንድትመጡ" ያሏቸው አንዳንድ የፖለቲካ ሥራ ትርፍ አፈንፋኝ ግለሰቦች ራሳቸውን እንደ ድርጅት በመቁጠር የሌለውን እንዳለ አስመስለው፤ ፖለቲካ ድርጀት አለኝ ያሉት የእርሳቸውን የውጭ ጉብኝት ተከትሎ ነው፡፡ 2012 ዓ/ም በምርጫ ሰበብ ከመንግሥት ካዝና ይሰጣል የተባለውን የሚሊዮን ብር ድጎማ ለማግኘት እንደ ግሪሳ ወፍ ኢትዮጵያን በፖለቲካ ቁጥር ሲያንበሻብሹ መንግሥት ህጋዊ የፖለቲካ ሰውነታቸውን ሳያጣሩ የሰሩት ሥራ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይን ከጥያቄ ውስጥ ጥሏቸዋል፡፡ ከኢትዮጵያ ህዝብ በታክስ የተገኘ ገንዘብ እና በስሙ ከውጭ በዕርዳታ የሚገኘውን ገንዘብ ለእነዚህ ግለሰቦች ለመስጠት ከሆነ፤ መንግሥት ከማይወጣው

በዚህም መሠረት በአለም ላይ ታይቶ የማይታወቅ የተፈናቀለ (Displaced) ህዝብ ያለበት አገር ቢኖር ኢትዮጵያ ብቸኛ ናት፡፡ በአለም ላይ የጎሳ ብጥብጥና የሰላም ዕጦት ያለበት አገር ቢኖር በኢትዮጵያ ብቻ ነው፡፡ ለዚህ አይነት አስቸጋሪና ውጥንቅጥ ላጣና ለጠፋው አገር የተዘየደ ነገር የለም፡፡ ምክንያቱም የህግና፣ የፍትህ ጉዳይ ስለጠፋ፤ የሰው ልጆች ወደ ማኅበረ-እንስሳነት ጉዞ የጀመሩበት ጊዜ ቢኖር ይህ አሁን ያለንበት ዘመንና ያሳለፍነው አመት ነው፡፡

ችግር ውስጥ ይገባል፡፡ ከውጭ ወደ አገር የገቡት የፖለቲካ ድርጅቶች ነን ከሚሉት አንዳንዶቹ በነፍስ ግድያ የሚፈለጉ ናቸው፡፡ እንዳንዶቹ ደግሞ እስከ አሁን ድረስ በህዝብ ላይ ሽብር እንዲነሳ ከላይ የተጠቀሱትን የቄሮ፣ የፋኖ፣ የአጄቶ፣ የዛሪማ፣ የመሳሰሉትን ከኋላ ሆነው የሚነዱ ነውጥ አራማጆች ናቸው፡፡ በተለያየ ጊዜ የመንግሥትን ገንዘብ በመንግሥት ሥራ ላይ በነበሩበት ወቅት አጋጣሚውን ተጠቅመው ሰርቀውና ዘርፈው የጠፉ ወንጀለኞች ናቸው፡፡ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አህመድ እንደዚህ አይነቱን ሥነ-ምግባርና ሥርዓት አልባ ግለሶቦችን አገር አስገብተው እንደ ስኬት መቁጠራቸው ገርሞኛል፡፡

2ኛ በአለም ታይቶ የማይታወቅ መፈናቀል የደረሰው በክቡርነታቸው የሥልጣን ዘመን ነው፡፡ የክልል መንግሥታት ለጠቅላይ ሚኒስትር አንታዘዝም ያሉበት ጊዜ ቢኖር በዚህ በአንድ አመት ዕድሜ ጊዜ ውስጥ ነው፡፡ የጎሳ ልዩነት፣ቂምና ጥላቻ፣ የፖለቲካ ግሪሳ ብዛት፣ ህዝብ ግራ የተጋባበት፣ ሥጋት የበዛበት ዘመን ያሳለፍነው የእርሳቸው አንድ አመት የሥራ ዘመን ሲሆን፤ አሁንም እንደቀጠለ ነው፡፡ ሁኔታው በዚህ ከቀጠለ በአገሪቱ ላይ ሊደርስ ያለው አበሳ ቅድመ ትንቢያ እንዳይሆን እንጂ ከሩዋንዳ የሚለይ አይመስልም፡፡ ፡

## ያልተሳኩ ኩነቶችና (ምክንያቶቻቸው)

የጠ/ሚ/ር ዐቢይ የሥልጣን ዘመን እንዳይሳካ ካደረጉት ነገሮች አንዱና ዋንኛ ሆኖ የሚጠቀሱት፣ እርሳቸውን በቶሎ የከበቡ ሶስት ጎራ የያዙ ማር አስመስለው መርዝ አጉራሾች ናቸው፡፡ 1ኛ ከውጭ አገር የገቡ እርሳቸውን በጣም የሚጠጉ የተቃዋሚ ፖለቲካ ድርጅት መሪዎች፡፡ 2ኛ የእርሳቸው የፖለቲካ ድርጅት የኦህዴድ(ኦዲፓ) የረጅም ጊዜ ጓዶችና በኋላ ላይ ከሀገርም ከውጭም መጥተው እርሳቸውን የተቀላቀሉት የኦሮሞ ኤሊቶች፣( elites) እና አክቲቨስቶች ነን የሚሉ የነውጥ ቡድን መሪዎች በዋናነት ይጠቀሳሉ፡፡ እነዚህ የሥነ-ምግባር ብልሹ ግለሰቦች ከእርሳቸው በሚያገኙት ድጋፍና ድጎማ በህዝብ መካከል እየገቡ በግልና በመንግስት ሚዲያ የሚነዙት የጥላቻና የቂም፣ የውሸት ፕሮፓጋንዳ አገርና ህዝብን እርስ በርስ እንዲባላ አድርጓል፡፡ በዚህም መሠረት በአለም ላይ ታይቶ የማይታወቅ የተፈናቀለ (Displaced) ህዝብ ያለበት አገር ቢኖር ኢትዮጵያ ብቸኛ ናት፡፡ 3ኛ በአለም ላይ የጎሳ ብጥብጥና የሰላም ዕጦት ያለበት አገር ቢኖር በኢትዮጵያ ብቻ ነው፡፡ ለዚህ አይነት አስቸጋሪና ውጥንቅጥ ላጣና ለጠፋው አገር የተዘየደ ነገር የለም፡፡ ምክንያቱም የህግና፣ የፍትህ ጉዳይ ስለጠፋ፤ የሰው ልጆች ወደ ማኀበረ-እንስሳነት ጉዞ የጀመሩበት ጊዜ ቢኖር▶

ይህ አሁን ያለንበት ዘመንና ያሳለፍነው አመት ነው፡፡ እነዚህ ችግሮች የመጡት እነ ጠ/ሚ/ር ዐቢይ አህመድ በአገር ውስጥ እያሉ የተፈጠሩ ችግሮች ናቸው ፡፡ የችግሮቹን ምንጭ ጠ/ሚ/ር ዐቢይ አያውቁም ቢባል ራስን ማታለል ይሆናል፡፡ የችግሩን ምንጭ ለመቁረጥ የሚቻልበትን መንገድ ያለመቀበል በራሱ ሌላ ችግር ነው፡፡

የኢትዮጵያ ህዝብ በአብዛኛው ምቀኛ ነው፡፡ ለዚህ አንድ ምሳሌ ላንሳ፤ በአንዳንድ ቦታዎች በሕይወት ያለውን ሰው የለም ብሎ በሐሰት የሚከስስና የሚመሰክር ህዝብ ነው፡፡ የወለደውን ወይም አባት ሆኖ ያሳደገውን የሚገድል ህዝብ አለ፡፡ ለዚህም በሥራዬ አጋጣሚ ይህንን ተመልክቻለሁ፡፡ የጠቅላይ ፍ/ቤት የፍርዶች መጸሐፍ ቅጽ 1 የ1990 በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በህግ መጽሐፍ ለማስተማሪያ ታትሞ በማስረጃነት የተቀመጠ ታሪክ ነው፡፡ እንዲሁም በሌላ መልኩ የኢትዮጵያ ህዝብ ደግ ህዝብ ነው፡፡ የተራበውን የሚያበላ፣ የተጠማውን የሚያጠጣ፣ የተቸገረውን የሚረዳ፣ለህግ አክባሪነቱ ወደር የለሌው፣ ለፍትህ ፍለጋ የሚተጋ ከየትኛውም አገር ህዝብ የተሻለ ህዝብ ነው፡፡

ስለዚህ በኢትዮጵያ ለ27 ዓመት ለተከሰተው ኃጢያት ተጠያቂ የሆኑትን በጉያቸው ይዘው ለውጥ ቢሉ ፌዝ ይመስላል፡፡ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ ያሳለፉት አንድ አመት ጉዞን በአደገኛ ስጋትና ፍርሃት፣ በሥርዓት አልበኝነት አሳልፈናል፡፡ የመንግሥት ጉዞ እውነትና ፍትህ እንዳይደለ የተረዳው ሁሉ እርሳቸው የማን ልጅ ናቸው? የወያኔ ወይስ የህዝብ ልጅ? የሚለው ጥርጣሬ ጎልቶ ስለወጣ በሃቅ መሥራት አልቻሉም፡፡ ቢሆንም በዚህ በአንድ አመት የተሰራው ሥራና ውጤቱ የአንድ ሰው (የእርሳቸው) ውጤት ነው፡፡ ሁሉም እንደ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ቢሠሩ ኖሮ ውጤቱ የተሻለ ይሆን ነበር ቢባል ለነገ የተሻለ ይሆናል ብለን ገምተናል፡፡ ስለዚህ 30% ተሠርቷል፡፡

ብሄራዊ ዕርቅና ሰላም የመንግሥት ተልዕኮ አይደለም፡፡ የብሄራዊ ዕርቅና ሰላም የህዝብ ጥያቄና፣ በራሱ በህዝብ የሚካሄድ መሆን አለበት፤ የፖለቲካና የመንግሥት እጅ መኖር የለበትም፡፡ ኢህአዴግ የሌላውን ፕሮጀክት (Project Copy) ኮፒ ማድረግ ልማዱ ነው፡፡ሌሎች ያዘጋጁትን ፕሮጀክት ወስዶ የራሱ አስመስሎ እንደገና ራሱ ኮሚሽን አቋቁሞ እንደገናም ራሱ አስወስኖ ዕርቅ ተካሄዷል ለማለት ከተፈለገ፤ ያለፈውን አመት በስኬት እንውሰደውና የያዝነውን ዓመት በፈተና እናሳልፋለን፡፡ በእነዚህና በመሳሰሉት ፈተና ላይ ያሳለፉት እርሳቸው ተጠልፈውና ጉሮሮአቸውን ተይዘው በአገርና በህዝብ ጉዳይ ላይ ሰላም ሳያመጡ፣ የአገር ኢኮኖሚ ወድቆ፤ እጥፍ ድርብ ችግር ተጭኖ ያሳለፉበት አመት ስለሆነ 70% አልተሳካም፡፡

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሳካሁት ብለው ከተናገሩት ነገር ውስጥ እጅግ የገረመኝ ነገር ቢኖር $ 13 billion USD. (የ13፣. ቢሊዮን ዶላር) ጉዳይ ነው፡፡ ክቡር ጠቅላይ ሚኒስትር ነገሩ ሁሉ ግራ ነው፡፡ በኢትዮጵያ ውስጥ የተካሄደው ለውጥ እንደ ሌሎቹ ለውጦች በመፈንቅለ መንግሥት አይደለም፡፡ እርሳቸው ሥልጣንን የተረከቡት ከአቶ ኃይለማሪያም ደሳለኝ በሰላማዊ መንገድ ነው፡፡ አቶ ኃይለማሪያም በነበሩበት ጊዜ ለኢትዮጵያ የውጭ ምንዛሬ ገንዘብ ምንም የለም ማለት እንደሆነ ያ ሁሉ ከውጭ የገባው የውጭ ምንዛሬ የትነው የገባው?. እርሳቸው ምን ይዘው ነበር የተቀመጡት? ምን ጉድ ነው የሚሰማው? እሺ እንበል ደርግ ከአፄኃይሌ ሥላሴ ሥልጣን ሲረከብ ባዶ ካዝና ነው የተረከብኩት አለ፡፡ ወያኔ ከደርግ የሥልጣን ቦታ ሲወስድ ባዶ ካዝና አገኘሁ አለ፡፡ ጠ/ሚ/ር ዐቢይም ይህንኑ ደገሙልን፡፡ በደርግ ጊዜ እኔን ጨምሮ የመንግሥት መ/ቤቶች ሠራተኛ በሙሉ የሶስትና የሁለት ወራት ደሞዛችንን መንግሥት መክፈል አቅቶት የሠራንበትን ሳንቀበል ወያኔ መጥቶ ቀርቶብናል፡፡ ግን ግን አቶ ኃይለማሪያም ከመለስ ሞት በኃላ ሥልጣን ሲረከቡ እንዴት ነበር? ካዝናው ባዶ ነበር ወይስ ሙሉ? የኢትዮጵያ ህዝብ ይህንን ማወቅ ይገባዋል፡፡ ማንን ነው የምንጠይቀው?

ድፍረት አይሁንብኝና በቅርቡ የኢትዮጵያ መንግሥት ያመነውን የብድር አሃዝ እንመልከት፤ የኢትዮጵያ ብድርና ዕዳ $ 50, U.S.A. Billion Doller) ቢሊዮን ዶላር ነው) ከዚህ ውስጥ $26. Billion የተበደረችው ከአለም ባንክ ነው፡፡ (ቀሪውን 24. ቢሊዮን የተበደረችው ከአገር ቤት አበዳሪዎች ነው) ከቻይና እና ከአውሮጳ ኅብረት የተበደረችው አልተገለፀም፡፡ እሺ እሱንም እንተወውና ኢትዮጵያ በየአመቱ ከአለም ባንክ፣ ከአውሮጳ ኅብረት፣ ከአሜሪካ መንግሥት፣ ከቻይና መንግሥት፣ ከለጋሾች ከመሳሰሉት በየአመቱ ለ27 አመት ያገኘችው ገንዘብ ምን በላው? ይህንን የኢትዮጵያን ህዝብ ሐብት የዘረፉት እነ-ማናቸው? የት ነው ያሉት? ኧረ የፍትህ ያለ፤ እርስዎ ለፍትህ ለማቅረብ በእውኑ አቅምና ጉልበት አጥተው ነው? መንግሥት በህግና ፍትህ ጉዳይ ላይ በእጅጉ አልሠራም፡፡ ስለዚህ እርስዎ 13 ቢሊዮን ዶላር በልመናና በብድር እንዳመጡ ተናግረዋል፡፡ እሺ እነዚህ ሰዎች ኢትዮጵያን ለቁማር አሲይዘው ሲጫወቱ ሌሎቹ የት ነበሩ? በህግ አምላክ!! የበፊቱ ለመማሪያ እንዲሆን ህግና ፍትህ ይከበር፡፡ እንደዚህ ካልሆነ የጠ/ሚ/ር ዐቢይ አህመድ የአንድ አመት ሥራ የተሳካ ሥራ ነው ለማለት አያስደፍርም፡፡ በህግ አምላክ ተናገሩ፡፡ እውነቱ ይውጣ፡፡

## ምልከታ፡ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይን የሚጠብቃቸዉ ፈተና፡

(ሀ) ለክቡር ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አህመድ ሰላምና ጤና እመኛለሁ፡፡ አምላክ ከአለ መጪውን አንድ አመት በአሁኑ ላይ የመደመር ፍልስፍና እናስተምራለን፤ ደጉ ፈጣሪ ለአመት በሰላም ያድርሰን፡፡ ከፊታችን ባለው አንድ አመት ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ እንዲራሩና እንዲጨክኑ ይገባል፡፡ ጭካኔ እንደ ቃየል እንዳይሆን፣ እንደ አቤል ለህዝብ ይታዘዙ፡፡ እንደ አብርሃም እግዚአብሔርን ይፍሩ፡፡ እንደ ሙሴ ወገንን ይታደጉ፡፡ እንደ ክርስቶስ ኢየሱስ ህዝብንና አገርን ያድኑልን፡፡ ፍርድ ጎደለ፤ ደሃ ተበደለ ወደ ተባለበት ቦታ ይድረሱልን፡፡ በኢትዮጵያ ዮርዳኖስ የለም፡፡ ለጥ፣ ሰጥ ያለ ሜዳ ነው፡፡ አሁን እያጋደለ ያለውን ህገ-መንግሥት ያፍርሱ፡፡ በፌደራል ሥርዓት ጉዳይ ላይ እንወያይበት፡፡

(ለ).ፌደራሊዝም ይፍረስ አንድ አገር አንድ ህዝብ ብለው እርስዎ ያውጁ፡፡ ወጣቱ የነገ አገር ተረካቢ ትውልድ በሱስ የተበከለው በወያኔ ሥርዓት መርዝ ነው፡፡ በጉቦና በሌብነት፣ በማጭበርበርና በውሸት የተበከለው አገር ተረካቢ ዜጋን በሥነ-ምግባር የታነጸ መንግሥት ስላልነበረ ነው፡፡ የኢትዮጵያን አንድነትና አገሩን የሚወድ ዜጋ እርስዎ ከቻሉ ይፍጠሩ፡፡ የዘቀጠ ትውልድ፣ ሥነ-ምግባር የጎደለውን ወጣት ለአገር ማብቃት አስቸጋሪ ነው፡፡ ይህንን የሚያስተካክሉ ከሆነ እኛም ከእርስዎ ጎን ልክ እንደ ካሌብና እንደ ኢያሱ እንቆማለን፡፡ ችግሩን ወደ ደስታ እንለውጣለን፡፡ ንጉሥ ሆይ ሺህ አመት ንገሥ፡፡ ኢትዮጵያ አንድ ናት፡፡ በአንድነቷ የሚያምን ትውልድ መፍጠር የሁሉም ዜጎች ድርሻ ነው፡፡ የኢትዮጵያ ብሄራዊ ዕርቅና ሰላም በመንግሥት ወሳኝነት ወይም መልካም ፈቃድ መካሄድ የለበትም፡፡ ለአገር ሰላም ሲባል፣ ብሄራዊ ዕርቅና ሰላም መከናወን ያለበት በገለልተኛ ቡድንና ድርጅት በግለሰቦች ነው፡፡ በኦሮምኛ ክርስቲና በዳሳ ሕንታኡ ሙጫዩ ላማታካሣ፣ እንዳሉት ሁሉ ኮሚሽኑ ይፍረስ እንደገና ይዋቀር፡፡

(ሐ) ከሁሉም በላይ የህግና የፍትህ ጉዳይ ቅድሚያን መያዝ ይገባዋል፡፡ ሁሉም ሰው ከህግ በታች መሆኑን ማንኛችንም መረዳት አለብን፡፡ ሰው ከማኅበረ-እንስሳ የሚለየው ሰው በመሆኑ ብቻ ሳይሆን የማሰቢያ ህሊና ስላለውም ነው፡፡ በዘር በተከፋፈለ ማህበረሰብ ውስጥ የቡድን ክፍፍል ይኖራል፤ ቡድን በቡድን በመሆን ጦርነት ይከፈትና በሁለት ቡድን መካከል ያለው ጦርነት በአንዱ ቡድን ጊዜያዊ አሸናፊነት ጋብ ሲል እንደገና በቡድን ውስጥ ባሉ ቤተሰቦች መካከል ጦርነት ይነሳል፡፡ ያ ጋብ ሲል በእያንዳንዱ ቤተሰብ መካከል ሌላ ጦርነት ይነሳል፡፡ ሲከፋ ወገንና ጠላት ያልለየ፤ ሁሉም ከሁሉ ጋር ጦርነት ውስጥ ይገባል፡፡ እንዲህ አይነቱ ሁኔታ ህገ-አራዊት ይባላል፡፡ ፍትህ በሌለበት አገር የሰው ልጆች ወደ ህገ-አራዊትነት ማሽቆልቆሉ የማይቀር እውነታ ነው፡፡ ዛሬ ላይ በወሎ ከሚሴና በሰሜን ሸዋ የተካሄደው የእርስ በርስ ጦርነት በቂ ማሳያ ነው፡፡ ስለዚህ እባከዎ እንደገና ያስቡበት፡፡ ለሰላምና ፍትህ ቅድሚያን ይስጡ፡፡ ንጉሥ ሆይ አሁንም ሺህ አመት ይንገሡ፤ ግን፣ ግን ፍትህንና ሰላምን ለማስፈን በሩን ይክፈቱ፡፡

(መ) የክቡር ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ የአንድ አመት ዕድሜ ንግግራቸውን ወድጄዋለሁ፡፡ በንግራቸው ውስጥ ያስደመሙኝና አንጀቴን የበላኝ ነገር ቢኖር በዕውቀት ማነስ ምክንያት የበደልኩት ሰው ካለ፣ ይቅርታ ይደረግልኝና ለወደፊት አገሬንና ህዝብን በታማኝነት አገለግላለሁ በማለት በቅንነትና በትህትና ይቅርታን መጠየቃቸውን እኔም በትህትና አስታውሳለሁ፡፡ እንዲህ አይነት ይቅርታ የጠየቀ ከፍተኛ የመንግሥት ባለሥልጣን፤ ጠቅላይ ሚኒስትር ቀርቶ ተሳስቻለሁ የሚል ይቅርታ የሚጠይቅ የቀበሌ ሊቀመንበር በዘመኔ ሰምቼ አላውቅም፡፡ የጠቅላይ ሚኒስትሩ ትህትና ከሁሉም በላይ ማርኮኛል፡፡

አምላክ የነገውን መልካም ያሳየን፡፡



ጃፋር ስዩም

# አኖሌ ፈርሷል!!

የኢትዮጵያችን ታሪክ በአወዛጋቢነቱ ቀጥሏል:: የኦሮሞ ዲሞክራሲያዊ ፓርቲ (ኦዲፒ) ጽሕፈት ቤት ኃላፊ የሆኑት አቶ አዲሱ አረጋ "የቡርቃ ዝምታ" በተሰኘው የደራሲ ተስፋዬ ገ/አብ መጽሃፍ ላይ የሰጡት አስተያየት የሳምንቱን ትኩረት ከሳቡ አጀንዳዎች ውስጥ ግንባር ቀደሙ ነው ብል ማጋነን አይሆንብኝም:: አቶ አዲሱ አረጋ ታሪክ ስማቸውን በደማቅ የወርቅ ቀለም እንደሚጽፈው ምንም ጥርጥር የለኝም:: አምቦ ላይ በተዘጋጀው የኦሮማራ መድረክ ላይ አቶ አዲሱ ቃል በቃል እንዲህ አሉ፦ "አንዱን በዳይ ሌላውን ተበዳይ አድርጎ ለማቅረብም በርካታ ገንዘብ ወጥቶ በጀት ተመድቦ ሆን ተብሎ ሁለቱን ህዝቦች ከፋፍሎ ለመብታቸው በአንድነት እንዳይቆሙና በጽናት እንዳይታገሉ ለማድረግም በርካታ ስራዎች ሲሰሩ ነበር:: ለአብነትም "የቡርቃ ዝምታ" የሚለውን የተስፋዬ ገ/አብን መጽሃፍ ማንሳት ይቻላል" በማለት እውነታውን በግልጽና በማያወላዳ አማርኛ ቁጭ አድርገውታል:: ከጥቂት ሳምንታት በፊት የአሁኑ መከላከያ ሚንስትር ለማ መገርሳ ከኦሮሚያ ባለሀብቶች ጋር ባደረጉት ውይይት ወቅት በምሬት ጠረጴዛ እየደበደቡ ሲናገሩ "ጡት ቆርጧል የሚል የሀሰት የጥላቻ ንግግርን እየተናገሩ በድሆች መካከል መጨራረስን የሚፈልጉ ሰዎች አሉ" የሚል አንድምታ ያለው ንግግር በማድረግ በዚ የጥላቻ ሀውልት ላይ ከርቀት ድንጋይ ወርውረውበት የነበረ ሲሆን፤ የኦሮሞ ዲሞክራሲያዊ ፓርቲ (ኦዲፒ) ጽሕፈት ቤት ኃላፊ የሆኑት አቶ አዲሱ አረጋ ግን "የቡርቃ ዝምታን" ድርስት አምርረው በመተቸት አኖሌን አፍርሰውታል:: ይህን ማለታቸውን ተከትሎ በርካታ የወቀሳ እና የድጋፍ ሃሳቦችም ተሰንዝረዋል፡፡ በጣት በሚቆጠሩ የኦሮሚያ ከተሞች ላይ እሳቸውን የሚቃወሙ ሰልፎችንም ተመልክተናል:: እሳቸው ግን አንዴ ታሪካዊ ሀላፊነታቸውን ተወጥተዋል::

## የአርሲው ጦርነት፥ 1879

አጼ ምኒልክ ሀገር ለማስፋፋት ካደረጓቸው ዘመቻዎች ውስጥ ትልቁ ጦርነት የተካሄደው አርሲ ላይ ነው:: አርሲዎች "ለዳግማዊ ምኒልክ አልገብርም" በማለት ከፍተኛ ትግል አድርገው በአጼ ምኒልክ ላይ ተከታታይ ድልን ተጎናጽፈውም ነበር:: ዳግማዊ ምኒልክም በአርሲዎች ክንድ ተከታታይ ሽንፈትን ከቀመሱ በኋላ በመጨረሻም በመስከረም 1879 በእልህ አስጨራሽ ዘመቻ አማካኝነት አሸንፈው አርሲን ወደ ግዛታቸው ቀላቀሉት:: ከዚህ ጦርነት 2 አመታት በፊት ነበር እነ ወለጋ በሰላም እጃቸውን የሰጡት:: የጅማው ንጉስ አባጅፋርም እንዲሁ:: አርሲ ግን ለረጅም ጊዜ አልቀበልም ብሎ ስለነበር ብዙ ተከታታይ ጦርነቶች ተካሂደውበታል:: በጦርነቱ ከአስገባሪውም ሆነ ከገባሪውም ወገን አያሌ ወታደሮች አልቀዋል:: በሺዎች የሚቆጠሩ ሰዎች ከ2ቱም ወገን ሞተዋል:: የንጉሱ ወታደሮች ነፍጥ ሲታጠቁ አርሲዎች ደግሞ ከጦርና ጋሻ ፈረስ ውጪ ምንም መሳሪያ ስላልነበራቸው ከተከላካዩ ወገን ያለቀው በቁጥር እንደሚልቅ እሙን ነው:: የፖለቲካና የታሪክ ምሁሩ ዶ/ር ነጋሶ ጊዳዳ የሟቾች ቁጥር 12ሺ እንደሚደርስ ከአመታት በፊት አስነብበውናል::

ጦርነቱ በራስ ወልደ ገብርኤልና ራስ አንዳርጌ የተመራ የነበረ ሲሆን አንዳንድ የታሪክ ድርሳናት በወቅቱ ንጉሱ እንጦጦ በሚገኘው ቤተ መንግስታቸው እንደነበሩ ያስረዳሉ:: የአርሲ ጦርነት ከተካሄደ ከጥቂት አመታት በኋላ ወደ አካባቢው የደረሰው ደ ሳልቪያክ የተባለ የፈረንሳይ ሀዋርያ በሰሜን አርሲ(ደደአ) እና በደቡብ አርሲ(ባሌ) ተገኝቶ ከአርሲዎች በሰበሰበው መረጃ ተመስርቶ እንደጻፈው ጦርነቱን እየመራ የነበረው ራስ ወልደ ገብርኤል የአርሲዎችን አይበገሬነት ለመስበር በአንድ ቀን ብቻ የአራት መቶ አንጋፋ አርሲዎችን ክንድ አስቆርጠዋል:: ክንዳቸውን ካጡት ትላልቅ ሠዎች ጥቂቶቹን በአይኔ በብረቱ አይቻለሁ በማለት በአያሌው ካኖ ከፈረንሳይኛ ወደ እንግሊዘኛ በተተረጎመው "The Ancient people great African Nation" መጽሃፍ ላይ ጽፏል::

ይህ ታሪክ ነው እንግዲህ በዘመናችን በ2 ጽንፍ የሚጎተተው:: የመጀመርያው ወገን የጦርነቱን ባህሪ ግምት ውስጥ ባለማስገባት ክስተቱን "አይደረግም" ብሎ ሙሉ ለሙሉ ምንም እንዳልተፈጠረ መካድ ሲሆን፤ በተቃራኒው ወገን ያለው ወገን ደግሞ ታሪኩን ከልክ በላይ በማጋነንና በማራገብ እንዲሁም ጥላቻን በመስበክ የፖለቲካ ትርፍ ለማጋበስ ይሯሯጡበታል::

አርሲ ከላይ እንደጠቀስኳቸው ወለጋና ጅማ በሠላም ወደ ምኒልክ የተቀላቀለች ግዛት አይደለችም:: በርካታ ሀገሮች ላይ እንደተደረገው የግዛት ማስፋፋት መንገድ ሁሉ አርሲም በጉልበት ነው ለምኒልክ የገበረችው:: ይህ ሲሆን ደግሞ በርካታ የሠብዓዊ መብት ጥሠቶች እንደሚፈጠሩ መካድ ከእውነታ መራቅ ነውና አስፈላጊ አይደለም::

ሆኖም ይህንን የታሪካችንን አካል እንደ "መልካም ዕድል" በመቁጠር ከልክ በላይ አጋንኖ የወታደር እጅ ተቆረጠ ሲባል የሠላማዊ ሴቶች ጡት ተቆረጠ፣ አባገዳዎች ተኮላሹ ከዚያ ከፍ ሲልም ጦርነቱ በአማራ ወራሪነትና በኦሮሞ መካከል እንደተደረገ አስመስሎ እስከማቅረብ መደረሱ በእውነትም ያሳዝናል::

የቡርቃ ዝምታ የተባለው የተስፋዬ ገ/አብ መጽሃፍም ሆነ እሱ ከተጠቀማቸው ገጸ ባህሪዎች ውስጥ ተወስዶ የተገነባው የአኖሌ ሀውልትም በዚህ ከልክ በላይ በተጋነነ ታሪክ ላይ ተመስርቶና በ2 ህዝቦች መካከል ጦርነት እንደተደረገ በማስመሰል ህዝብ ላይ ጥላቻን ለመትከል ተግቶ ይሰራል:: ይህንን መጽሃፍ ነው አቶ አዲሱ በህወሃት በጀት የተጻፈ ያሉት::

## ጸሐፊው ምን ይላል?

የመጽሐፉ ደራሲ ተስፋዬ ገብረዓብ አቶ አዲሱ የተናገሩት ስህተት ነው ይላል፡፡ ለቢቢሲ አማርኛ የተለመደች የተደጋገመች ከአመክንዮ በብዙ ሺ ማይሎች የራቀች አረፍተ ነገሩን እንዲህ በማለት ደግሞታል፦ "በኦሮሞ እና በአማራ ሕዝብ መካከል ግጭት ካለ የግጭቱ መንስዔ 'የቡርቃ ዝምታ' ሊሆን አይችልም" ካለ በኋላ "ችግር ካለ የችግሩ መንስኤ እኔ ልሆን አልችልም፡፡ ችግሩ ምንድነው? የሚለውን አጣርቶ መፍትሄ መስጠት እንጂ፤ እንዲህ አይነት ማጭበርበር ወንዝ አያሻግርም" ብሏል፡፡

አቶ አዲሱ ከቢቢሲ ጋር በነበራቸው ቆይታ፤ ደራሲው መጽሐፉን ሲጽፍ የኢህአዴግ አመራር ነበር ብለው" መጽሐፉ በኢህዴአግ ውስጥ እጅጉን ይወደስ ነበር፡፡ መጽሐፉ ይወደስ የነበረው ደግሞ ለኦሮሞ ህዝብ ተቆርቋሪ በመሆን እንዳልሆነ አውቃለሁ" ይላሉ፡፡ መጽሐፉ በስፋት እንዲሰራጭ የሚፈልጉ ግለሰቦች የገንዘብ ወጪ ሲሸፍኑ ማለትም 'ስፖንሰር' ሲያደርጉ እንደነበርም አውቃለሁ ሲሉም አቶ አዲሱ ተናግረዋል፡፡

## ተስፋዬ ገ/አብ ግን ማነው?

ደራሲ ስብሃት ገ/እግዚአብሄር "መልክዓ ስብሃት" በተሰኘ በተለያዩ ጸሀፍት ስለ ጋሽ ስብሃት በተጻፈ መጽሃፉ ላይ ለጋዜጠኛ ጌታቸው ወርቁ ስለ ቀድሞ አለቃው ተስፋዬ ገ/አብ እንዲህ ብሎታል፦ "ተስፋዬ መጀመርያ ለኔም፣ ለአንተም፣ ለእርሱም እውነት የሆነን ነገር ይነግርሃል፥ ትቀበለዋለህ:: ከዚያም ትንሽ ይቆይና ለአንተና ለእሱ ብቻ እውነት የሆነን ነገር ይነግርሃል(ለኔ እውነት ያልሆነ) ትቀበለዋለህ:: በመጨረሻም የሱ ብቻ የሆነ እውነት ይነግርሃል (ለኔና ላንተ እውነት ያልሆነ) ከመቀበል ውጪ አማራጭ የለህም::"

ተስፋዬ የሱ ብቻ የሆኑ በርካታ "እውነቶች" አሉት:: እነዚህ "እውነቶች" በታሪክ ድርሳናት ያልተደገፉ፣ በመጀመርያ፣ሁለተኛና ሶስተኛ ደረጃ የታሪክ ምንጮች ያልተረጋገጡ የርሱ ብቻ "እውነቶች" ናቸው፡፡ "የቡርቃ ዝምታ" አንዱ ነው፡፡ አንዱን ህዝብ ባንዱ ላይ ለማነሳሳትና ህዝቦች በጥላቻ እንዲተያዩ ለማድረግ ታልሞ ታሪክን ወደጠርዝ ጎትቶና ከልክ በላይ አጋኖ የፃፈው መፅሀፍ ነው፡፡ አቶ አዲሱ አልተቀበሉትም! እኔም አልቀበለውም! አንተም የሱን በሀገር ህልውና ላይ አደጋ ሊጋርጥ የሚችለውን፣ ኢትዮጵያዊ ወንድምህን በጥላቻ እንድታይ የሚያደርግህን የሱ ብቻ የሆነውን "እውነት" ባለመቀበልና ልክ እንደ አቶ አዲሱ በማጋለጥም ጭምር የፈረሰውን አኖሌን ወደ መቃብር ልትከተው ትችላለህ! በፅሁፌ መግቢያ እንዳብራራሁት አኖሌን አለመቀበል ታሪክን መካድ አይደለም! ከልክ በላይ የተጋነነን በህዝቦች መካከል የተገነባን የጥላቻ ሀውልት መቃወም እንጂ! ታሪክን ሚዛናዊ በሆነ መልኩ ተረድተን ዕውቅናን በማጎናፀፍ ጥላቻን አሸንፈንና ከስህተታችን ተምረን የተሻለ ሀገር በመገንባት ሁላችንም ማሸነፍ እንችላለን፡፡ ከዚህ ውጪ ባለው መንገድ ግን ራሳችንን ለብሄር ነጋዴዎች አሳልፈን በመስጠት ኢትዮጵያችንን ሀገር አልባ ከማድረግ የዘለለ ውጤት አይኖረውም ባይ ነኝ፡፡

# ለቅሶአችንን አልቅሳችኋል...

ከገጽ 3 የዞረ

ዙሪያዬን መቃኘቴን ቀጥያለሁ:: እኛ ካለንበት ሁለት ጠረጴዛዎች ራቅ ብሎ እነጀማል ዲሪዬ ይታዩኛል:: የሶማሌ ክልልን በዕውቀትና እውነት ለመምራት ከተለያዩ የዓለም ሀገራት የተሰባሰቡት እነ ጀማል በኢሳት የታሪክ ድርሳን ውስጥ ስማቸው በጉልህ የሚስፍርላቸው ድንቅ ኢትዮጵያውያን ናቸው:: የአቶ ሙስጠፋ መሀመድ አመራር የሶማሌ ክልል ላይ ያመጣው ለውጥ በእነዚህ አስተዋይና ብልህ ሰዎች የታጀበ ለመሆኑ የቅርብ ምስክር መሆን እችላለሁ:: በኢትዮጵያ በነበረኝ ቆይታ የታዘብኩት ከክልሎች እንደሶማሌ ክልል የተረጋጋና ለውጡም በትክክል የሚታይበት ሌላ አከባቢ አለመኖሩ ነው:: ወንድም ሙስጠፋን ለክልሉ መሪነት ከመብቃቱ በፊት እንተዋወቃለን:: "እኛ ሙሉ ኢትዮጵያዊ ነን:: የሶማሌ ኢትዮጵያ የሚለው አገላለጽ አይገባንም:: የኦሮሞ ኢትዮጵያ፡ የአማራ ኢትዮጵያ፡ የሚባል እስከሌለ ድረስ የሶማሌ ኢትዮጵያ ሊኖር አይችልም:: ኢትዮጵያዊ ነን-በቃ" ይህን አገላለጽ ለመጀመሪያ ጊዜ የሰማሁት ከአቶ ሙስጠፋ ነው:: መቼም ኢትዮጵያ የሚሏት ሀገር ተአምረኛ ናት:: ወደቀች ሲሏት የምትነሳ፡ ጠላቶቿን ደፍቃ በክብር ከፍ ብላ የምትታይ ሀገር ናት:: ዘረኝነት ነፍሷን ሲጥ ሊያደርግ በደረሰበት በዚህ ዘመን የአቶ ሙስጠፋ አይነት ኢትዮጵያዊ ብቅ ይልና ታሪክ ይሰራል::

አቶ ሙስጠፋ በዙሪያው የሰበሰባቸው ምሁራን ክልሉ በእውቀት የሚመራ እንዲሆን አድርጎታል:: አብዲ ዒሌ በሚባል ከእውቀትም ከእውነትም የተጣላ ሰው በቆየበት ወንበር ላይ እነሙስጠፋ ሲመጡ ለውጡን የሰማይና የምድር ያህል እንዲሆን ማድረጋቸው የሚጠበቅ ነበር:: ሙስጠፋና አማካሪዎቹ ዋጋ ከፍለዋል:: ላለፉት 10 ዓመታት የአብዲ ዒሌን አሰቃቂ የጭቆና ዘመን በማጋለጥ ለትግሉ ከፍተኛ አስተዋጽኦ አድርገዋል:: በተለይ ሁለቱ አማካሪዎቹ ከእኛም ጋር በቅርበት የሚሰሩ በመሆናቸው በትግሉ የነበራቸውን ድርሻ በቅርበት አውቀዋለሁ:: ጀማል ዲሪዬና አብዱላሂ ሁሴን የኢሳት ቤተሰብ ሆነው መረጃ እያነፈነፉ፡ የዜናና የፕሮግራም ቋታችንን ሲሞሉልን ቆይተዋል:: ህወሀት በሶማሌ ክልል የዘረጋውን የአፋናና የዘረፋ መረብ እግር በእግር እየተከታተሉ እርቃኑን አደባባይ ሲያጋልጡ አብረውን የዘለቁ ለመሆናቸው የኢሳት ታዳሚዎች የሚያውቁት ታሪክ ነው:: ከየብሄሩ አዳዲስ ብሄርተኛ ብቅ እያለ የዘረኝነት አጀንዳ ሽክፎ በህውሀት የተተከለውን የጎሳ ፖለቲካን በማራገብ ለኢትዮጵያ የጎን ውጋት በሆነበት በዚህን ወቅት የአንድነቱን መንገድ መርጠው፡ ከኢትዮጵያዊነት ውጪ ያለው አካሄድ አጥፊ መሆኑን ተገንዝበው፤ በኢትዮጵያዊነት ከፍ ብለው መታየትን የምርጫ ሳይሆን የህልውና ጉዳይ አድርገው ወደፊት ብቅ ያሉት አቶ ሙስጠፋና አማካሪዎቹ በአጭር ጊዜ ውስጥ ለሶማሌ ክልል ተስፋ መስጠት የሚያስችል ውጤት አስመዝግበዋል:: ኢትዮጵያውያን አቶ ሙስጠፋ ቀጣዩ ጠቅላይ ሚኒስትር እንዲሆን ከወዲሁ ምኞቱን ሲገልጽ እየሰማሁ ነው:: ይገባዋል::

በነገራችን ላይ ኢሳት ውስጥ በቆየሁባቸው ዓመታት ውጤታማ ስራ ሰርተናል ብዬ ከምጠቅሳቸው አንዱ ይህን በሶማሌ ክልል ተስፋ የሆነውን አመራር ለመቀልበስና የቀድሞውን የአብዲ ዒሌን አስተዳደር በሌላ ቅርጽ ለመትከል የተደረገውን ሴራ የበጣጠስንበትን ዘገባ ነው:: የጠ/ሚር አብይ አህመድ እግር ከሀገር መውጣቱን ጠብቆ የአቶ ሙስጠፋን አመራር በመፈንቅለ መንግስት ለማስወገድ ከጫፍ ደርሶ የነበረውን የአህመድ ሼዶና የህወሀት ስውር እንቅስቃሴ በፍጥነት በማጋለጥ ኢሳት ወሳኝ ዘገባ አስተላልፏል:: አህመድ ሽዴ ቱርክ ኢስታንቡልና ሶማሌላንድ ሀርጌሳ የመሸጉትንና በዶላር ላይ ተኝተው ከርቀት የፈለጋቸውን ማደረግ የሚችሉትን የቀድሞ የአብዲ ዒሌ ካቢኔ አባላትን ከጀርባው አሰልፎ የክልሉ ፓርቲን ጠቅላላ ጉባዔ በመጥራት አቶ ሙስጠፋ ከስልጣናቸው እንዲነሱ የመጨረሻው ምዕራፍ ላይ ደርሶ ነበር:: ምናልባት ሁለት ቀናት ቢሰጠው አህመድ ሽዴ ያሰበው ይሳካለት ነበር:: ኢሳት ነገሩን አጋልጦ አንገቱን ባያስደፋው ኖሮ አብዲ ዒሌን ከእስር ቤት አስወጥቶ፡ ዳግም የሶማሌ ክልል መንበር ላይ እንዲቀመጥ ያደርገው ነበር:: ለዚህ ደግሞ ትንታጎቹ የአቶ ሙስጠፋ አማካሪዎች ጀማልና አብዱላሂ የተጫወቱት ሚና የአንበሳውን ድርሻ የሚይዝ ነው:: እንግዲህ እነዚህ ድንቅ ኢትዮጵያውያን ናቸው የኢሳት የደስታ ቀን ተከፋይ ለመሆን ከጂጂጋ መጥተው ከሚሌኒየም አዳራሽ የታደሙት::

በስተግራዬ ወደሚገኘው ጠረጴዛም ተመለከትኩ:: የደቡቡ አፍሪካው ጀግና ኢትዮጵያዊ የገዛኸኝ ገብረመስቀል(ነብሮ) ወላጅ እናት ይታዩኛል:: ከፐ/ር ብርሃኑ ነጋ እናትና ከሌሎች እንግዶች ጋር በአንድ ጠረጴዛ ዙሪያ ተቀምጠዋል:: የዚያ ብርቱ፣ ቆፍጣና፣ የሀገር ባለውለታ በደቡብ አፍሪካ ላሉ ኢትዮጵያውያን አድባር ሆኖ የቆየ፤ ኢትዮጵያን ብሎ ኖሮ ኢትዮጵያን እንዳለ የተገደለ ውድ ኢትዮጵያዊ ገዛኸኝ ገብረመስቀል መቼም የሚረሳ አይደለም:: የለፋበትን ትግል ውጤቱን ለማየት ዋዜማው ላይ በጨካኞች እጅ ህይወቱ ማለፉ አሁን ድረስ እንደትኩስ መርዶ የሚያንገበግበን ጉዳይ ነው:: ይሄን ጀግና ኢትዮጵያዊ አምጠው የወለዱት እናት በደስታችን ቀን ተካፋይ ለመሆን ተገኝተዋል:: ተንደርድሬ ሄጄ አቀፍኳቸው:: ነብሮን በሞት ካጣነው አንድ ዓመት ሊሞላው ነው:: እናት አሁንም ሀዘን ያጠቆረው ገጽታቸው አብሮአቸው አለ:: ማቅ እንደለበሱ ናቸው:: ከዓይኖቻቸው ውስጥ የሚነበበው የልጃቸው ሞት ምን ያህል እንደጎዳቸው ነው:: የእናት አንጀት አይችልም:: ስብር ብለዋል:: ማጽናናት ከባድ ነው:: ከእቅፋቸው ውስጥ ሆኜ ሲቃ በተናነቀው ድምጽ የቻልኩትን ላጽናናቸው ሞከርኩ:: "ነብሮ የእርሶ ልጅ ብቻ አይደለም:: የኢትዮጵያውያን እናቶች በሙሉ አምጠው የወለዱት ልጃቸው ነው:: ነብሮ እኮ የሞተው የማይቀረውን ሞት ነው:: ከንቱ ሞት ግን አይደለም:: ለኢትዮጵያ የተከፈለ ዋጋ ነው::" ብዙ መናገር አልቻልኩም:: ወደ መቀመጫዬ ተመለስኩ::

መድረኩ ቀልጧል:: ጭፈራው ደምቋል:: ከሰገነቱ ላይ ሆነን ታዳሚውን ቁልቁል እየተመለከትን በደስታ ባህር እየዋኘን ነው:: አከባቢዬን መቃኘቴ አላቆምኩም:: በኢትዮጵያ የቅርብ ጌዜ ትግል ውስጥ በአንድም ይሁን በሌላ ዋጋ የከፈሉ፡ በእስር ቤት ስቃይ መከራ ያዩ፡ ልጆቻቸውን በግፍ የተነጠቁ፡ በፖለቲካውም ሆነ በጋዜጠኝነቱ መድረኮች የህወሀትን አገዛዝ አንገት ለአንገት እየተናነቁ ለዚህ ለውጥ ያበቁ ሰዎች የኢሳት በዓል እድምተኞች ሆነው ተገኝተዋል:: የኢሳት ባለውለታዎች ናቸው:: ኢሳት የእነዚህ የታፈኑ ወገኖች ድምጽ ሆኖ ቆይቷል:: ስለበደላቸው ስቃይ መከራቸው ያልጮኸበት ጊዜ የለም:: ለኢሳት ያላቸው ስስት እኛኑ መልሶ ያስደንቀናል:: "ለቅሶአችንን አልቅሳችኋል፡ ህመማችንን ታማችኋል፡ የእናንተን ውለታ የሰው ልጅ ከፍሎ የሚጨርሰው አይደለም፡ የኢትዮጵያ አምላክ ብድራችሁን ይክፈላችሁ" የሚለውን ምርቃት መስማት እድሜን አንድ ቀን ይቀጥላል::

ከሰገነቱ ላይ ያሉትን ታዳሚዎች በመቃኘት ተጠምጄ የመድረኩን ትዕይንት ዘንግቼዋለሁ:: ባልደረቦቼ ከመቀመጫቸው ተነስተው ከሰገነቱ መስታወት ጋ ተጠግተው አየኋቸው:: ይጨፍራሉ:: ከመድረኩ የአንጋፋው ድምጻዊ ጥላሁን ገሰሰ "ኢትዮጵያ" የተሰኘው ሙዚቃ በህበረት እየቀረበ ነው:: ህዝቡ ሰንደቅ ዓላማችንን ከፍ አድርጎ በልዩ ስሜት አብሮ ይዘፍናል:: ባልደረቦቼም ይህን ትዕይንት ለመካፈል ነበር ወደ ፊት የተጠጉት:: ተቀላቀልኳቸው:: ይህ የጥላሁን ዘፈን የህዝብ መዝሙራችን እንዲሆን ከምመኛቸው ዘፈኖቹ አንዱ ነው:: ስለኢትዮጵያ ስሜቴን በሚገባ ይገልጽልኛል:: "እናት ሀገር ኢትዮጵያ፡ የእኛ መመኪያ":: የነዋይ ደበበ "የዜማ የቅኔ" የተሰኘው ዜማም እንዲሁ ውስጤን ፈንቅሎ በሚወጣ የሀገር ፍቅር ስሜት የሚያጦዘኝ ነው:: የጂጂ "እማማ ኢትዮጵያን" በሰማሁ ቁጥር ኢትዮጵያዬ እናቴ የምር ታሳዝነኛለች:: አንዳንዴም የሚረብሸኝ ዘፈን ነው:: "…..በጎጆ አያልቅም ሙሽርነቷ" የሚለው ቦታ ላይ ስደርስ ሁል ጊዜ ወደውስጥ በሀሳብ እሰምጣለሁ:: የሀገር ፍቅር ልክፍት:: የቴዲ አፍሮ አዲሱ ዓልበም ላይ "ኢትዮጵያ" የሚለው ዘፈንም እንዲሁ ለህዝብ መዝሙርነት ካጨኋቸው የሚጠቀስ ነው:: "ኢትዮጵያ ሐገሬ፡ ባንቺ አይደለም ወይ ክብሬ":: የሀይልዬ ታደሰ 'የኢትዮጵያ አምላክ' የተሰኘው ዘፈን ደግሞ ተስፋና ወኔ ይሰጠኛል:: የኢትዮጵያ ጠላቶች መጨረሻቸው ሁሌም ውድቀት መሆኑን የሃይልዬ ዘፈን ሁሌም ይነግረኝና "አዎን ኢትዮጵያ አትጠፋም፡ ጠላቶቿም በእግሯ ስር ይንበረከካሉ" ብዬ አብሬ እፎክራለሁ:: ባዶ ፉከራ አይደለም:: የሚገርመው አሁን የጠቀስኳቸው ዘፈኖች በዲጄና በተጋባዥ ድምጻውያን አማካኝነት ከመድረኩ ተደምጠዋል::

በኢሳት ታሪክ ጉልህ ስፍራ የሚይዘው የሚሌኒየም አዳራሹ ትዕይነት እንደቀጠለ ነው:: የኢሳት ጋዜጠኞች በየተራ ንግግር እያደረጉ ነው:: እኔ ያዘጋጀኋት አጭር መልዕክት በምስጋና የተሞላች ነበረች:: በስምንት ዓመት ጉዞአችን አብረውን የዘለቁ፡ አጋሮቻችንን አመሰገንኩ:: የሌሎች ባልደረቦቼ ንግግርም ከዚያው ያለፈ አልነበረም:: አልፎ አልፎ በስልኬ አማካኝነት በማህበራዊ ሚዲያዎች የኢሳትን በዓል በተመለከተ ህዝቡ እንዴት እየተከታተለው እንዳለ እመለከት ነበር:: እዚያም ደምቋል:: በሚሌኒየም አዳራሹ ለኢሳት የተሰጠው ክብር ፌስቡኩን ተቆጣጥሮታል:: ስሜቱ ልዩ ነው:: ለኢሳት መቼም የማይረሳ ቀን:: በፈንጠዚያ የታጀበ ዕለት:: ኢትዮጵያዊነትን ሲመቱት ይበልጥ የሚጠብቅ ማንነት መሆኑ ለወዳጅም ለጠላትም ዳግም የተመሰከረበት አጋጣሚ:: ህዝባችን የበለጠ ሃላፊነት በመሰጠት ወደፊታችን በርካታ ስራዎች እንደሚጠብቁን የነገረን መድረክ:: ከባድ ነው:: ካለፈው ይልቅ የወደፊቱ ሃላፊነት ይከብዳል:: ትከሻችን የሚፈተንበት ጊዜው ደርሷል:: ኢትዮጵያ ከምን ጊዜውም በላይ የምትፈልገን አሁን ነው:: ፈጣሪ አምላክ ይርዳን:: በዓሉ ተጠናቋል:: የአዲስ አበባው የኢሳት ቀን በደመቀ ሁኔታ ተጀምሮ እንዳማረበት አብቅቷል::

ድክም ብሎኛል:: ሰውነቴ ዝሏል:: በክብር የተቀበለን ወገናችን በክብር ሸኘን:: ወደሆቴላችን ስናመራ መንገድ ዳርና ዳር ያለው የህዝቡ ስሜት ድካም የሚያስረሳ ነው:: ክብር ሰጥቶን ሊጠግብ አልቻለም:: የዚህን ህዝብ ውለታ ግን እንደምን መክፈል ይቻል ይሆን?

"የወሰንና የማንነት ኮሚሽኑን በሚመለከት፣ ከአገር ውስጥም ከአገር ውጭም፣ በስልክም በሜሴንጀርና በሌሎች የመገናኛ ዘዴዎች ምን ላይ እንደደረስን፣ ምን ምን እየሠራን እንደሆነ ይጠይቁኛል። አሁን አሁን ጥያቄዎቹ ስለበዙ ለእያንዳንዱ ሰው ምላሽ ከምሰጥ በጥቅሉ ለሁሉም መስጠት ሳይሻል አይቀርም በማለት ምን ላይ እንደደረስን ልናገር። ያው የሚጠይቁኝ የኮሚሽኑ አባል መሆኔን የሚያውቁ ይመስሉኛል። በአጭሩ የወሰንና የማንነት ኮሚሽን አባላቱ ፓርላማ ቀርበን ቃለ መሃላ ፈጽመናል። ከዚያም አንድ ቀን ትውውቅ አድርገናል። ከዚህ ውጭ ምንም የሠራነው ነገር የለም። ሰብሳቢና ምክትልም አልተሾመም። እኔ የማውቀው ይሄንኑ፣ የደረስንበትም እዚህ ላይ ነው። ይሄው ነው። አመሰግናለሁ!"

ዉብሸት ሙላት

## "ሕማማተ_ሐኪም"

ሰሞኑን የአንድ ትልቅ ህንጻ ግንባታ ያለበት ቦታ ሄጄ ነበር። ኮንትራክተሩ «እነዚህ ግንበኞች በቀን 500 ብር እየበሉምኮ አይሰሩም። የቀን ሠራተኞቹማ 250 እየተቀበሉ እንዴት እንደሚያለምጡ ብታይ" አለኝ። በቀን ለ8 ሰዓታት ብቻ (ከጠዋቱ 2:00-6:00 ፣ ለ7:30-11:30) እየሰሩ መሆኑን ሲነግረኝ ደግሞ ጆሮዬን ማመን አልቻልኩም። ይሄኔ ነበር የሀገሬ ሐኪም ትዝ ያለኝ። አንድ ግንበኛ በቀን 500 (በወር 15.000) ይከፈለዋል። ወዳጄ ይህ የወር ደሞዝ የዕጩ ዶክተሩን ደሞዝ በ3 እና 4 ዕጥፍ እንደሚበልጥ ታውቃለህ? ድንጋይ የሚሸከመው፣ ጭቃ የሚያቦካው የቀን ሠራተኛ በቀን 250 (በወር 7500) ይቀበላል። ይህስ ከጠቅላላ ሓኪሙ ደሞዝ እንደሚሻል ታስተውላለህ?

በወሊድ ችግር ደሟ የሚፈሰው፣ HIV ያለባትን እናት ሕይወት ለማዳን ሲፋጠኑ ደሟ በነካው መርፌ ጣታቸውን ወግተው ሽልማት ሳይሆን የማይድን በሽታን ሲቀበሉ የሚችሉ ሓኪሞች ያሉባት ሀገር (በዚህ ምክንያት ለHIV እና Hep B የተጋለጡ 3 ሓኪሞችና 2 ነርሶችን አውቃለሁ) 36 ሰዓታት በቀጥታ እየሰራ የአንድ ግንበኛን ደሞዝ የሚመኝ፣ የቀን ሠራተኛ ክፍያ የሚያስቀናው ሐኪም ከፈጠረች፣ ሀገሪትዋ እየሞተች ለመሆንዋ መርዶ ነጋሪ አያሻም።

ሕይወትን_የሚጠብቅ_ሕይወቱ_ይጠበቅለት

©Binyam ZeChristos ሚያዝያ 15 - 2011



በፊልምና ጋዜጠኝነት ሞያ ላበረከተው አስተዋጽኦ ተሸለመ

ታዋቂው የፊልም ዳይሬክተርና የቴሌቪዥን ሥራ አስፈፃሚ መኮንን ሚካኤል ከናይጀሪያ ኢባዳን ዩንቨርሲቲ ለብዙ ዓመት በፊልምና ጋዜጠኝነት ሞያ ላበረከተው አስተዋጽኦ፤ በጆርናሊዝም እና ቢዝነስ ኢኮኖሚ ባለፈው ቅዳሜ የክብር ዶክትሬት ተሰጥቶታል።

መኮንን ከዚህም ባለፉ በተለያዩ የፊልም ፌስቲቫሎች ላይ በዶክመንተሪ ሥራዎቹ፣ በርካታ አዋርዶችን ያሸነፈ ሲሆን በቬነስ ፊልም ፌስቲቫል የተሰጠው ቤስት አፍሪካን ዳይሬክተር አዋርድ የቅርብ ጊዜ ትዝታችን ነው ።

"የሀገራችንን ሥም በማስጠራትህ ከልብ እናመሰግናለን"

ጌጡ ተመስገን



## እህት ሜሮንና ልጇ ከኳታር ወደ ሀገሯ ተሸኙ !

የእህት ሜሮን መኮንን ታሪክ አረብ ሀገር የምንገኝ ዜጎች የሁላችንም ታሪክ ነው። ሜሮን መኮንን አንድ ልጇን በተሻለ ሁኔታ ለማሳደግና ቤተሰቧን ለመቀየር ከአመታት በፊት ወደ ሀገረ ኳታር የተሰደደች እህት ነበረች። ስራዋን ተግታ በምትሰራበት፣ የአሰሪዎቿ ቤት ባጋጠማት የከሰል ጭስ መታፈን አደጋ የጤና መታወክ ጠልፎ የአልጋ ቁራኛ አደረጋት። ብርቱዋን እናት ሽብርኮ የጣላት ደዌ ካለፉት ስምንት ዓመታት ጀምሮ እስካሁን ሆስፒታል አውሏታል። በረዥም ጊዜ ህክምናዋ የተደረገላት ከፍተኛ የህክምና ድጋፍ ግን ከአልጋዋ ሊያስነሳት ቀርቶ ሊያነቃት አልቻለም።

ዶ/ር ዐቢይ አህመድ ከወር በፊት ወርሃ መጋቢት ኳታር ለጉብኝት ሲገቡ ተስፋ ሰነቅን ። ዶ/ር ዐቢይ ኳታር ደርሰው ጊዜ ሳያባክኑ ወደ ታማሚዋ ጎራ ብለው፣ የመሪ ተስፋቸውን ሰጡን፣ ቃል ገቡ። ወዲያውኑ የዜጋቸውን ጉዳይ ለከፍተኛ የኳታር መንግስት ባለስልጣናት አሳውቀው መፍትሔ አበጁለት።

የኳታር መንግስት ለዶ/ር ዐቢይ ጥያቄ በሰጠው ምላሽ እህት ሜሮን ወደ አገሯ ገብታ ሕክምናዋን እንድትከታተል የሚያስችላትን አስፈላጊውን የሕክምና ቁሳቁስና የአንድ ዓመት የሕክምና ወጪ በአፋጣኝ በማሟላት ወደ አገሯ ለመላክ ቃል ገባ። እነሆ ቀኑ ሚያዝያ 09 ቀን 2011 ዓ.ም ደረሰ፤ ከዚህ ቀደም ዜጋው ወደ ሀገር ለመላክ ያልቻለው የኤምባሲው ዲፕሎማቶች፣ የኢትዮጵያ ኮሚኒቲ አመራሮች፣ በኳታር የሚገኙ ታዋቂ ግለሰቦችና የኃይማኖት አባቶች በተገኙበት እህት ሜሮን "አተርፍ ባይ አጉዳይ" ሆናም ቢሆን ከነልጇ በክብር ወደ ቅድስት ሀገሯ ተሸኝታለች ።

(ነብዩ ሲራክ)

## ጀግና ሀገሩን ያስጠራል!

## ኢትዮጵያዊው ኢንጂነር ሲራክ ስዩም

የአለማችን ረጅሙን የሄቨረስት ተራራን በመውጣት የመጀመሪያው ኢትዮጵያዊ ሆኗል፤ኢንጂነር ሲራክ ስዩም። ይህ የኤሌክትሪካል ኢንጅነሪንግ ምሩቅ የሆነው ሰው፤ኑሮውን በሰን ፍራንሲስኮ ያደረገው ኢትዮጵያዊ በአለማችን በረጅሙ በኤቨረስት አናት ላይ በመውጣት የኢትዮጵያን ሰንደቅ አላማ ከፍ አድርጎ አውለብልቦታል።

© tadias magazin newyork

# ክፍት የስራ ቦታ ማስታወቂያ

የኤጀንሲው ስም - አወጋን በውጭ ሀገር ስራና ሰራተኛ አገናኝ ኀላ.የተ የግ.ማህበር

የኤጀንሲው ፍቃድ ቁጥር- **PEA/204 A/2019**

ኤጀንሲው ፍቃድ ያገኘበት ሀገር- **ሳውዲአረቢያ**

1. የተገኘው ክፍት የስራ መደብ: **የቤት ውስጥ አያያዝ**
   a. የሚፈለገው ብዛት - **1000**
   b. ተፈላጊ ችሎታ
      I. ስምንተኛ ክፍል ያጠናቀቀ
      II. የሙያ ብቃት ማረጋገጫ ማስረጃ ያላት
      III. እድሜ ከ21-45
      IV. ፆታ- ሴት
   c. መነሻ ደመወዝ -**1000 ሪያል**
   d. የቅጥር ቆይታ ጊዜ - **2 ዓመት**
   e. ስራው የተገኘበት ቦታ- **ሳውዲአረቢያ ፡ ደማም ከተማ**
   f. ሌሎች አስፈላጊ መረጃዎች
      I. ስልክ አቅርቦት ይመቻቻል
      II. ደመወዝ በየወሩ ይከፈላል

2. የተገኘው ክፍት የስራ መደብ :**ሹፌር**
   a. የሚፈለገው ብዛት - **200**
   b. ተፈላጊ ችሎታ
      I. ስምንተኛ ክፍል ያጠናቀቀ
      II. የሙያ ብቃት ማረጋገጫ ማስረጃ ያለው (**አለም አቀፍ መንጃ ፍቃድ ያለው**)
      III. እድሜ ከ23-40
      IV. ፆታ- ወንድ
   c. መነሻ ደመወዝ- **1500 ሪያል**
   d. የቅጥር ቆይታ ጊዜ- **2 ዓመት**
   e. ስራው የተገኘበት ሀገር- **ሳውዲ አረቢያ፡ ደማም ከተማ**
   f. ሌሎች አስፈላጊ መረጃዎች
      I. ስልክ አቅርቦት ይመቻቻል
      II. ደመወዝ በየወሩ ይከፈላል

3. የተገኘው ክፍት የስራ መደብ : **የቤት ውስጥ እንክብካቤ (ነርስ )**
   a. የሚፈለገው ብዛት - **200**
   b. ተፈላጊ ችሎታ
      I. የሙያ ብቃት ማረጋገጫ ማስረጃ ያለው
      II. እድሜ ከ21-45
      III. ፆታ- ሴት/ ወንድ
   c. መነሻ ደመወዝ - **1500 ሪያል**
   d. የቅጥር ቆይታ ጊዜ - **2 ዓመት**
   e. ስራው የተገኘበት ሀገር- **ሳውዲአረቢያ፡ ደማም ከተማ**
   f. ሌሎች አስፈላጊ መረጃዎች
      I. ስልክ አቅርቦት ይመቻቻል
      II. ደመወዝ በየወሩ ይከፈላል

- ወቅቱ ያላለፈበት የቀበሌ መታወቂያ ያለው/ ያላት
- ኤጀንሲው የሚሰጠው ማንኛውም አገልግሎት ሰራተኛው ምንም አይነት የአገልግሎት ክፍያ የማያስከፍል መሆኑን እንገልፃለን፡፡
- አመልካቾች ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ባሉት ጊዜያት በኤጀንሲው ቢሮ የትምህርትና የስራ ልምድ ማስረጃችሁን ዋናውንና ፎቶ ኮፒውን በመያዝ በግንባር ቀርበው መመዝገብ ይችላሉ

❖ አድራሻ ፡- ሰባተኛ ሸንኮራ በረንዳ ከፍ ብሎ የሎግያ የገበያ መአከል አራተኛ ፎቅ ቢሮ ቁጥር 403

**ስልክቁጥር፡ 0118 273086 ወይም 0910118283 /0940203030**

ኢሜይል -aweganat3084@gmail.com

---

# ማዮን መጽሔት

**ኢትዮ ሀበሻ የሕትመትና ማስታወቂያ ኃ/የተ/የግ/ማኅበር**

## ክፍት የስራ ማስታወቂያ

| | |
|---|---|
| ኤዲተር፣ -<br>አዘጋጅ፣ -<br>ከፍተኛ ሪፖርተር | በመጽሔትና ጋዜጣ ላይ የረጅም ጊዜ የስራ ልምድ ያለው/ያላት<br>በፕሬስ ውስጥ ተሳትፎ ያደረጉ ቢሆኑ ይመረጣል፡፡ |

**የማስታወቂያ ባለሙያ፣-** በተለያዩ ጋዜጣ ፣ መጽሔት ፣ የማስታወቂያ ድርጅት ውስጥ በማስታወቂያ ሠራተኝነት የሰራ/የሰራች

**ደሞዝ በስምምነት የስራ ልምድ በስራ ሰዓት ማስገባት ይቻላል**

አድራሻ፣- አራት ኪሎ ግንፍሌ ድልድይ አጠገብ
አምባቸው ሕንፃ 2ኛ ፎቅ ቢሮ ቁጥር 207

+251 912 165606
+251 118 122333